ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

# በኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና

በ

ቡልቱ አበየዚድ

በአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት

ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የተዘጋጀ ጥናት

ሰኔ 2015 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

# በኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና

በ

ቡልቱ አበየዚድ

ዋና አማካሪ፡ ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የተዘጋጀ ጥናት

ሰኔ 2015ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

## የማረጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ

**የጥናቱ ርዕስ፡-** በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና (በዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

**ማረጋገጫ፡-**

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው ይህ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች አንዱን ለማሟላት የተዘጋጀ ጥናት የራሴ የጥናት ውጤት የሆነ፣ ከዚህ ቀደም በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ለመመረቂያ ጽሁፍነት ያልቀረበ፣ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ምንጮች ሁሉ በተገቢው መንገድ እውቅና ተሰጥቷቸው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

ቡልቱ አበየዚድ ፊርማ ________________ ቀን ________________

**የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ**

**የጥናቱ አማካሪ**

ስም ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) ፊርማ ________________ቀን ________________

ስም ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር) ፊርማ ________________ ቀን ________________

**የጥናቱ ገምጋሚዎች**

ስም________________ ፊርማ ________________

ቀን________________

ስም ________________ ፊርማ ________________

ቀን________________

# ምስጋና

በቅድሚያ ለዚህ እንድበቃ የረዳኝን አላህን ለማመስገን እወዳለሁ፡፡

በመቀጠል ይህን ጥናት በተሳካ ሁኔታ ከዳር እንዲደርስ የጥናት አቅጣጫ በማሳየት፣ ስህተቶቼን በየጊዜው በማቃናትና በስራው እንድበረታታ በማድረግ የጥናት አማካሪዎቼ ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ እና ዶ/ር ምህረት ሳዳሞ ላደረጉልኝ ድጋፍ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ይህን ጥናት በማካሂድበት ወቅት ጥናቱ የሚጠይቀውን መረጃ ለመሰብሰብ እንድችል ትብብር ያደረጉልኝን የዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራን እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሁም በመረጃ አሰጣጡ ሂደት ንቁ ተሳትፎ ያደረጉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድጋፋቸው ሳይለየኝ ለዚህ ያበቁኝ ባለቤቴና ቤተሰቦቼን

ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ትኩረት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው የአጠናን ዘዴ ተንታኝ (analytiical) ጥናታዊ ዘዴ ነው፡፡ ጥናቱ በአመቺ ንሞና ዘዴ በተመረጡት ዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ አተኩሯል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ የተደረጉት በ2015ዓ.ም. የትምህርት ዘመን በሁለቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በስምንት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ 481 ተማሪዎች መካከል በቀላል የእጣ ንሞና መሰረት 30% የሚሆኑትን 145 /አንድ መቶ አርባ አምስት/ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ማለትም ሁለት ጊዜ የቀረበ የአንቀጽ መጻፍ ፈተና እና በጠቅላላው 20 ጥያቄዎች የቀረቡበት የጽሁፍ መጠይቅ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች እርስ በርስ ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ የተማሪዎቹን የአንቀጽ መጻፍ ስህተት አይነቶች፣ ብዛትና ተጠኚዎቹ አንቀጽ በመጻፍ ያሉባቸውን ችግሮች አመላክተዋል፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱት የዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ በርካታ ስህተቶችን የሚፈጽሙ መሆናቸውን የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ተጠኚዎቹ በሁለቱ ዙሮች ከፈጸሟቸው 4558 ስህተቶች መካከል በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 2446 (53.66%) በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 2112 (46.34%) ስህተቶች ተመዝግበዋል፡፡ ተማሪዎቹ በድግግሞሽ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ጉልህነት አንጻር በቅደም ተከተል ሰዋሰዋዊ አገባብ አለመጠበቅ፣ የፊደላት አጻጻፍ ስህተት፣ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ስህተት፣ የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተትና የሀሳብ አንድነት ያለመጠበቅ ስህተት መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ተማሪዎቹ አንቀጽ ሲጽፉ ለሚያጋጥሟቸው ስህተቶች ዋንኛ ምክንያቶች የግንዛቤ ማነስ /ስነልቦናዊ ችግሮች/፣ ከማስተማሪያ ዘዴ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዳሉባቸው ቃኝቷል፡፡ በመጨረሻም የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ስህተት ለመቀነስ የሚረዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመው ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

## የማጋገጫና የጥናቱ አጽዳቂዎች ውሳኔ መስጫ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ........ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 .የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3. የጥናቱ ዓላማ........ 4

1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5

1.5.የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.6.የጥናቱ ውስንነት........ 6

1.7. የቁልፍ ቃላት አውዳዊ ፍቺ........ 6

ምዕራፍ ሁለት........ 8

ክለሳ ድርሳናት........ 8

2.1. ጽንሰ-ሃሳባዊ ቅኝት........ 8

2.1.1. የመጻፍ ክሂል ምንነት እና አስፈላጊነት........ 8

2.1.2. የመጻፍ ክሂልን ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስብስብ የሚያደርጉ ምክንያቶች........ 9

2.1 .3 .የስህተት ምንነት ........ 11

2.1.4. የስህተት ትንተና ምንነትና ባህርያት ........ 12

2.1.5. የስህተት ትንተና አስፈላጊነት ........ 15

2.1.6. በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የስህተት ጉልህነት ላይ የማትኮር አላማ ........ 15

2.1.7. የጽሁፍ ስህተት አይነቶች........ 16

2.1.7 .2 . የስነ-ምዕላድ ስህተት ........ 18

2.1.7.3. የስነ-አገባብ ስህተት........ 18

2.1.8. አንቀጽ ........ 19

2.1.9. የስህተት ትንተና መርሆዎች........ 20

2.1.10. የNorrish የስህተት ትንተና ሞዴል ........ 22

2.2 .የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 23

ምዕራፍ ሶስት ........ 27

የአጠናን ዘዴ ........ 27

3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 27

3.2.የጥናቱ አካላይ ........ 27

3.3. የንሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 27

3.3.1. የትምህርት ቤት ንሙና አመራረጥ ........ 27

3.3.2.. የክፍል ደረጃ ንሙና አመራረጥ ........ 28

3.3.3. የተጠኚዎች አመራረጥ ........ 28

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 29

3.4.1. የአንቀጽ ፈተና ........ 29

3.4.1.1. የአንቀጽ ፈተና አዘገጃጀት ........ 29

3.4.1.2. የአንቀጽ ፈተና አስተራረም ........ 30

3.4.2. የጽሁፍ መጠይቅ ........ 31

3.5. የመረጃ ትንተና ዘዴ ........ 31

የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ ........ 33

4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና ........ 33

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 61

የጥናቱ ማጠቃለ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች ጥቆማ ........ 70

5.1.የጥናቱ ማጠቃለያ ........ 70

5.2.መደምደሚያ ........ 71

5.3. የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ ........ 71

አባሪ አንድ ........ 77

አባሪ ሁለት ........ 78

አባሪ ሶስት ........ 82

አባሪ አራት ........ 84

## የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ 1፡- በተማሪዎቹ አንቀጾች ውስጥ የተፈጸሙ ስህተቶች ስርጭት አጠቃላይ ገጽታ....................34

ሰንጠረዥ 2፡- በሁለቱ አንቀጾች ውስጥ የስህተት አይነት ምድቦችና የስህተት ስርጭት...35

ሰንጠረዥ 3፡- ስዋስዋዊ አገባብ ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች....................39

ሰንጠረዥ 4፡- የስነድምጽ (ሆሄያት) አጻጻፍን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች.............43

ሰንጠረዥ 5፡- በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የተፈጸሙ ስህተቶች....................47

ሰንጠረዥ 6፡- በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የተፈጸሙ ስህተቶች....................51

ሰንጠረዥ 7፡- የሀሳብ አንድነትን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች....................53

ሰንጠረዥ 8፡- በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በመጻፍ ረገድ ከተማሪዎቹ የተያያዙ ችግሮች....56

ሰንጠረዥ 9፡- የመጻፍ ክሂልን ለመማር ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተገናኙ ችግሮች መረጃ ትንተና 58

ሰንጠረዥ 10፡- በአንቀጽ መጻፍ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች መረጃ ትንተና....................60

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

መጻፍ አመንጪ ክሂል እንደመሆኑ መጠን የሀሳብ አቀነባበርን፣ የሀሳብ ፍሰትን፣ የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ የመጻፍ ትምህርት ለበርካታ ተማሪዎች ውስብስብ የሚሆንበት ምክንያት ለዘመናት የብዙ አጥኚዎችን ትኩረት የሳበ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል (Alhaisoni, 2012፣ Sarfraz, 2011)፡፡ መጻፍን በቋንቋ መማሪያ አውድ ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር የሚያስፈልግባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛው ምክንያት መጻፍ ተማሪዎቹ የሚማሩትን ትምህርት አጣርተው እንዲማሩ ለማድረግ ይረዳል፡፡ በሌላም በኩል ተማሪዎቹ ያላቸውን ተፈጥሯዊ ችሎታ በመጠቀም ሀሳባቸውን አቀናጅተውና አደራጅተው እንዲያቀርቡ አቅጣጫ ያስይዛቸዋል፡፡ ከዚህም ጋር ከአዳዲስ ቃላት፣ መዋቅሮችና ሰዋስው ጋር በሚገባ እንዲተዋወቁ ያደርጋቸዋል (Sarfraz, 2011)፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የመጻፍ ክሂልን መማር ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት፣ መዋቅርና ሰዋስው በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችላቸው መሆኑን ነው፡፡

የመጻፍ ክሂልን በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ለተማሪዎች ከፍተኛ ችግር ከመሆኑም በላይ፣ የክሂሉ ባለቤት ለመሆን የሚበቁት ተማሪዎች በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ ይነገራል፡፡ በእርግጥም ጥሩ ድርሰትን መጻፍ መቻል ከባድ፣ አዝጋሚ ሂደት የሚታይበት፣ ብዙ ተማሪዎችን የሚያስጨንቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው በማለት Alhaisoni (2012) Richards (1990) እና Davies እና Widdowsen (2004) በመጥቀስ አብራርተዋል፡፡

ከላይ ምሁራኑ የገለጹት ሀሳብ የመጻፍ ክሂል ከባድና ረጅም ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ለማመልከት ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ Richards እና Renandya (2002) ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋውን በሚገባ ተጠቅመው፣ ሀሳብ አሰባስበውና አዳብረው ለመፃፍ እንደሚከብዳቸው የማያጠራጥር ሀቅ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል Abiy (2013፣58) "ጽህፈትን በሁለተኛ ቋንቋ ለማዳበር የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመጻፍ ክሂል ትልቅ አስተዋጽኦ አለው" በማለት ያብራራሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር

በቀጣይ በሁለተኛ ቋንቋና በውጭ ቋንቋ ለሚማሩት የጽህፈት ትምህርት መማርን ቀላል እንደሚያደርግላቸው ለማሳየት ነው፡፡

በመሆኑም ጥሩ የመጻፍ ክሂል ለስነትምህርታዊ ብቃትና ለተሳካ ውጤት፣ ለተለያዩ ስራዎችና ሙያዎች እጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ አስፈላጊና ጠቃሚ ክሂል በአማርኛ ቋንቋ ረገድ በአሁኑ ጊዜ ምን ይመስላል? ብለን ስንጠይቅ ክሂሉ በከፍተኛ ደረጃ የደከመ መሆኑን በውል ከምናስተውለው በተጨማሪ የተለየዩ ጥናቶችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ፡፡ የመጻፍ ክሂል በተማሪዎች ዘንድ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ በጣም አስቸጋሪ እና ከስህተት ያልጸዳ መሆኑን ባየ (1987) ገልጸዋል፡፡ መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣ የሀሳብ ፍሰትን ፣የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ Richards እና Renandya (2002) ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጹ፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የአንቀፅ አገነባብ፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ለመፃፍ ክሂል ወሳኝ ነገሮች መሆናቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚገኙበት ወይም የሚበለፅጉት በትምህርትና አዘውትሮ በመፃፍ ነው፡፡ ትምህርቱ እየፃፉ መማርን የሚጠይቅ በመሆኑ በትምህርት ቤት ትኩረት ተሰጥቶት ሁልጊዜ ሊለማመዱት እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡

የመጻፍ ክሂል ብዙ ልምምድን ስለሚጠይቅ በልምምድ ሒደት ከፊደላት ቅርጽ ጀምሮ እስከ ቃላት አጠቃቀም ድረስ የተለያዩ ስህተቶች ይፈጠራሉ፡፡ አንድ ህጻን አፍ መፍቻ ቋንቋውን ሲለምድ ሳይኮላተፍ እንደማይሳካለት ሁሉ ተማሪዎችም የጽሕፈትን ክሂል ለመለማመድ መደናቀፋቸው አይቀርም ሲሉ LittleWood (2006) ያስረዳሉ፡፡ Norrish (1993፡12-15) ስህተቶች ለትምህርት ከሚቀርቡት ነገሮች ምርጫ፣ ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ በተወሰነ ቅደም ተከተል ከሚቀርበው የማስተማር ትኩረት፣ በቋንቋው ትምህርት ከሚሰጡ ምሳሌዎች፣ በምሳሌዎች አማካይነት ከሚደረገው የልምምድ ውጤት ወይም ተማሪዎቹ እነዚህን የትምህርት መረጃዎች ሲጠቀሙ ከሚኖራቸው የአጠቃቀም ሂደት ሊመጡ ይችላሉ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

Littlewood (2006) እና Norrish (1993) እንደሚሉት ስህተት የመማር ሂደት አንዱ አካል እና ትምርቱንም በንቃት ለማካሄድ ጠቃሚ ምልክት ነው፡፡ ስህተት ቀደም ሲል በልማዳዊ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች ቃላትን በማጥበቅ፣ በንቃት ባለመከታተል ወይም በእውቀት ማነስ ከትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ማፈንገጥ እንደሆነ እና በተማሪዎች ዘንድ እንደ ውድቀት የሚቆጠር፣ በመምህራኑ ችሎታ ላይም ጥያቄን

የሚፈጥር እንደነበረ ይነገራል፡፡ ሆኖም ግን እንደ LittleWood (2006) ገለጻ፣ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ በተካሄደ ምልከታዊ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከታላሚው ቋንቋ አገባብ አለማፈንገጥም ስህተት ላለመፈጸም ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ በእያንዳንዱ የቋንቋ ተማሪ የሚፈጸሙ ስህተቶችም የተማሪው የቋንቋ እድገት አመልካቾች እንደሆኑ ተደርገው መቆጠር ያለባቸው ናቸው ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

አጥኚዋ የተለያዩ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በስህተት ትንተና ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ስትፈትሽም አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች እና በአፍ-ፈቶች ላይ የተሰሩ ጥናቶችን ቃኝታለች፡፡ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ምህረት (1998)፣ ደበበ (1990)፣ ተገኝ (2000)፣ መሰረት(2003) ፣የአምላክስራ (2008)፣ ተካቡ (2011)፡፡ እነዚህ ጥናታዊ ጽሑፎች በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን በፈቱና የአማርኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ጽሕፈት ላይ የሚገኙትን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች አጥንተዋል፡፡ የተካቡ ጥናት በአማርኛአፍ ፈት ተማሪዎች አንቀጽ ስህተት ላይ ያተኮረ ሲሆን፣የመሰረት ጥናት የኦሮምኛአፍ ፈት ተማሪዎች በኦሮምኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ላይ ያተኮሩ ሲሆን በኦሮምኛ አፍ ፈት ተማሪዎች አንቀጽ መጻፍ ስህተቶች ላይ አላተኮሩም፡፡ ከሁለተኛ ቋንቋ መማር ጋር የተካሄዱ የመጻፍ ክሂል ስህተት ጥናቶች ውሱንነትም አለ፡፡በዚሁ መሰረት ይህ ጥናት የህን ክፍተት ለመሙላት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመለየት የተካሄደ ነው፡፡

## 1.2 .የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ጥናቶች እንዳመላከቱት ባለፉት ሶስት አስርት አመታት በስህተት ትንተና ፈጣን እድገት የተስተዋለበት ወቅት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በየጊዜው የቀረቡ የጥናት ውጤቶች እንደሚያሳዩት ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ለክፍል ደረጃቸው የሚመጥን የመጻፍ ክሂል ግንዛቤ አለመጨበጣቸው በበርካታ አጥኚዎች ይጠቀሳል፡፡ ለምሳሌ፡- Presada & Badea (2014) መምህራን የጽህፈት እርማትን አስፈላጊነት ከመጻፍ ትምህርት አላማ ጋር በሚገባ ባለማቆራኘታቸውና ወሳኝ በሆኑና በተማሪዎች በተደጋጋሚ በሚፈጸሙ የመጻፍ ክሂል ስህተቶች ላይ አትኩረው የመጻፍ ክንዋኔን በምጋቤ ምላሽ ስልቶች አስደግፈው ለማረም ጉልህ ጥረት አለማድረጋቸው ተማሪዎች የትኛውን ማሻሻል እንደሚጠበቅባቸው እንዲረዱ እንዳላስቻላቸው ይሞግታሉ፡፡

የመጻፍ ክሂል ለበርካታ ተማሪዎች ውስብስብ ሂደት ከሚሆንባቸው ምክንያቶች ዋነኛው በጽሁፍ ስህተቶች የተነሳ እንደሆነ አጥኚዋ በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የማስተማር ቆይታዋ በስፋት ያጤነችው ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች በነዲ ጊቤ ወረዳ በዲምቱ ቁጥር አንድ እና በዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ፤ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ ሆሄያትንና ቃላትን አስተካክለው ካለመጻፍ ጀምሮ ልዩ ልዩ የጽሁፍ ስህተቶችን የሚፈጽሙ መሆናቸውን አጥኚዋ በማስተማር ቆይታዋ ደጋግማ የተመለከተችው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽን አስተካክሎ የመጻፍ ችግሮች በጥናት በተደገፈ መልኩ ለይቶና ተንትኖ ማቅረቡ ለችግሮቹ መቃለል የሚረዱ ተገቢ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለመተለም አስተዋጽኦ እንዳለው በማሰብ ይህን የመጻፍ ክሂል ስህተት ትንተና ለማካሄድ ተነሳስታለች፡፡

አጥኚዋ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የተለያዩ ስህተቶች እንደሚፈጽሙ ለመለየት ችላለች፡፡ በዚህም ምክንያት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን የአንቀጽ መጻፍ ስህተቶች አስመልክቶ የተካሄደ የምርምር ስራ እንዳለና እንደሌለ ለመለየት በጅማና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቀረቡ የቅድመ ምረቃ እና የድህረ ምረቃ ጥናቶችን በተቻላት አቅም ለመፈተሽ ሞክራለች፡፡ በዚህ ሂደት በተለይ በአማርኛ ጽሁፍ ዙሪያ የተሰሩትን ጥናቶች በስፋት ፈትሻለች፡፡

በተገኘውም መረጃ ጥናቶቹ ተማሪዎች በተለያዩ አገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን ፈተው በአማርኛ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች የዳሰሱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ አንቀጽ ጽሁፍ ላይ የሚፈፅሙዋቸው ስህተቶችን አስመልክቶ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች ውሱን ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለማጥናት አነሳስቷታል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 3.3.1.የጥናቱ ዋና ዓላማ

ይህ ጥናት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈፅሙዋቸው ስህተቶችን በተመለከተ የስህተት ትንተና ዘዴን ተጠቅሞ ለመመርመር ሞክሯል፡፡

### 1.3.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ምንነት መለየት፤
- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ ለሚያጋጥሟቸው ስህተቶች ምንጮቹ ምን ምን እንደሆኑ መዳሰስ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል፡፡

1. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?
2. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ ለሚያጋጥሟቸው ስህተቶች ምንጮቹ ምንድናቸው?

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ታስቧል፡፡ ኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በጽሁፍ ጊዜ የሚፈጽሙትን ስህተት በመረጃ በተደገፈ ሁኔታ አጥንቶ የሚያቀርብ በመሆኑ፣ ተማሪዎቹ በየትኛው የቋንቋ ስርዓት እና/ወይም ቅርጽ ላይ ድክመት እንዳለባቸው ለማወቅ ይረዳል፡፡ ይህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል የማስተማሪያ ስልቶችን በማሻሻል እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን በየትኛው አቅጣጫ መርዳት እንደሚገባ ፍንጭ ለማግኘት ይረዳል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የጽሁፍ ስህተቶች በማረምና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ክንዋኔ አጽንኦት ሊሰጡ ስለሚገባቸው ዝርዝር ጉዳዮች መረጃ ያቀርባል፡፡ ይህም የተማሪዎቹን አጠቃላይ የመጻፍ ክንዋኔ በየጊዜው በመቆጣጠር በመጻፍ ሂደት መሻሻል እንዲያሳዩ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች በአብዛኛው የሚፈጽሙዋቸውን የመጻፍ ክሂል ስህተት አይነቶች እንዲያውቁ ለማድረግ ያግዛል፡፡
3. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሚፈጽሟቸው የአንቀጽ ስህተቶች ዙሪያ ጥናቱ ከሚያቀርበው ውጤት በመነሳት መምህራን አካባቢያዊ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ወቅታዊ ችሎታ እንዲስማሙ አድርጎ በማዘጋጀት የመጻፍ ክሂልን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው ፍንጭ ይጠቁማል፡፡

4. ሌሎች በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ወደፊት ጥናት ለማካሄድ ለሚነሱ ተመራማሪዎች መነሻ ሊሆን ይችላሉ፡፡

### 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ነዲ ጊቤ ወረዳ ዉስጥ በሚገኙት ዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2015 የትምህርት ዘመን በ9ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በሚከታተሉ ተማሪዎች ላይ አትኩሯል፡፡ ጥናቱ ከዚህ ውጪ የሌሎች ትምህርት ቤቶችን ወይም የክፍል ደረጃዎችን ጉዳይ አልተመለከተም፡፡ በእርግጥ የጽህፈት ስህተት ትንተናን በየትኛውም የክፍል ደረጃ ላይ መስራት ይቻላል፡፡ በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ማተኮር የተፈለገበት ምክንያት አጥኚዋ በዚህ የክፍል ደረጃ በማስተማር ላይ የምትገኝ በመሆኑ የመረጃ አሰ ባሰቡን ሂደት ለማቀላጠፍ እንደሚረዳት በማሰብ የተደረገ ምርጫ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋንኛ ትኩረት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ ምን አይነት የአንቀጽ ስህተቶችን እንደሚፈጽሙ፣ እንዲሁም በአንቀጽ መጻፍ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ምክንያቶቹ ምን እንደሆኑ መመርመር ላይ አትኩሯል፡፡ ተጠኚዎቹ በአንቀጽ ጽሁፎቻቸው ውስጥ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በአይነት በመለየት ከሰዋስው፣ ከቃላት፣ ስርአተ-ነጥብ፣ አያያዥ ቃላት ስህተቶች አንጻር በመተንተን ላይ አትኩሯል፡፡

## 1.6.የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት በኦሮምኛ አፍ -ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡በጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ወቅት በአንቀጽ ፈተናው በንሞና ከተመረጡት 145 ተማሪዎች 13ቱ በተለያዩ ምክንያቶች መሳተፍ አለመቻላቸው የመረጃውን አሰባሰብ ሙሉ እንዳይሆን ያደረገ ነበር፡፡

## 1.7. የቁልፍ ቃላት አውዳዊ ፍቺ

**ኢ-አፍ ፈት፡-** አማርኛ ቋንቋ የአፍ መፍቻ /የመጀመሪያ/ ቋንቋቸው ያልሆኑና በሌላ ቋንቋ አፍ ፈትተው አማርኛ ቋንቋን እንደ አንድ የትምህርት አይነት በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን ያመለክታል፡፡

**የመጻፍ ስህተት**፡- የአማርኛ ቋንቋ መደበኛ የአጻጻፍ ስርአትና ህግጋትን ባለማወቅ ወይም ባለመማር ተማሪዎች በሚያቀርቧቸው ጽሁፎች ውስጥ የሚጠቀሟቸው የተሳሳቱ ቅርጾች፣ አገላለጾችና የተዛነፉ የቃላት፣ የስዋስው አቀራረቦችን ያመለክታል፡፡

**የስህተት ትንተና**፡- የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣ የታዩት ስህተቶች የሚተነተኑበትና የተተነተኑትም የስህተት አይነቶች በተለያዩ ምድብ አይነቶች የሚቀመጡበት ዘዴ ነው (Brown 1994) ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ጽንሰ-ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1. የመጻፍ ክሂል ምንነት እና አስፈላጊነት

ቋንቋን መጠቀም ማለት የቋንቋ ክሂሎችን በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚዎች ቋንቋውን በመጠቀም ሒደት ውስጥ የተለያዩ ክሂሎችን ይተገብራሉ፡፡ ቋንቋውን ያዳምጣሉ፣ ይናገሩበታል፣ ያነቡታል፣ ብሎም ይጽፉበታል፡፡ ቋንቋ በባህሪው የሚለመድ መግባቢያ ስለመሆኑ ሁሉንም ያግባባል፡፡ ይሁንና ግን የማንበብ እና የመጻፍ ክሂሎች በትምህርት ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡ መጻፍ ውስጣዊ ሀሳብን በወረቀት በማስፈር ለመረጃ ልውውጥ እና ለመግባበት የሚውል በተለይም ካለንበት ዘመን አንጻር ሲታይ እጅግ የላቀ ጠቀሜታ ያለው ክሂል ነው፡፡ መጻፍ በስሜት ሕዋሳት ንቁ ቅንጅት የሚከናወን አዕምሯዊ ተግባር ነው (Harmer, 1991)፡፡

LittleWood (2006) እንደገለጹት፣ የመጻፍ ክሂል በስርአት የሚታወቁ ፊደላትና ምልክቶች በመጠቀም ሃሳብ ስርአት ባለው መንገድ የሚገለጽበት፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ቀጥተኛ ወይም ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ተግባቦት ለማካሄድ የሚረዳ በንቁ አእምሮ መከናወን ያለበት የቋንቋ አመንጪ ክሂል ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው መጻፍ ከአመንጪ ክሂሎች አንዱና ሃሳብን ስርአት ባለውና በተደራጀ መልኩ የምንገልጽበት የንግግር ወኪል መሆኑን ነው፡፡ Chen & Huang (2003) እና Collins (2002) በየበኩላቸው እንደገለጹት፤ መጻፍ የታላሚውን ቋንቋ መሰረታዊ የአጻጻፍ ህግጋት በመከተል በበርካታ ተግባቦታዊ አላማዎች ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ከሌላው ሰው ጋር ተግባቦት ለማካሄድ (ለምሳሌ፡- ደብዳቤ)፣ ከበርካታ ሰዎች ጋር ተግባቦት ለማካሄድ ወይም ሃሳብ ለሃሳብ ለመለዋወጥ (ለምሳሌ፡- ጋዜጣ) እንዲሁም ለሌሎች ክንውኖች መጻፍ ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው፡፡ ግለሰባዊ ደስታ ለማግኘት፣ ሀሳብን፣ ፍላጎትን፣ አመለካከትንና እምነትን ለሌላው ሰው ለማጋራት፣ ማስታወሻ ለመያዝ፣ መረጃ ለማስተላለፍ፣ ለማሳመን፣ ወዘተ ሰፊ አገልግሎት አለው ብለዋል፡፡ በዚህ መሰረት የመጻፍ ክሂል በግል ለሚከናወኑ ተግባራትም ሆነ በተመረጡ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ

ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በጥሩ ሁኔታ ተግባቦት ለማካሄድ የሚረዳ መሳሪያ ነው፡፡ ባለንበት ወቅት ወጣቶች በበርካታ ማህበራዊ ትስስር ገጾች ለምሳሌ ቴሌግራም፣ ፌስቡክ፣ ኢሜይል፣ ወዘተ ሃሳባቸውን ስርአት ባለው መልኩ መግለጽ እንዲችሉ የመጻፍ ክሂል ሰፊ ጠቀሜታ አለው፡፡ በዚህም የተነሳ ተገቢውን የአጻጻፍ መንገድ መማርና ሃሳብን በሚገባ አደራጅቶ ማቅረብ ትኩረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡

### 2.1.2. የመጻፍ ክሂልን ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስብስብ የሚያደርጉ ምክንያቶች

የመጻፍ ክሂል በሁለተኛ ቋንቋ ይቅርና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ደረጃም ቢሆን ከባድ አእምሯዊ ክንዋኔ ነው፡፡ በርካታ ጥናቶች እንደጠቆሙት በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ሂደት ውስብስብነት የተመላበት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ ገብነት /ተጽዕኖ ጋር መታገል ጎልቶ ይታይባቸዋል (Brown, 1994፣ Cheng, 2001፣ Darus & Subramaniam, 2009):: በሁለተኛ ቋንቋ መጻፍ አብዛኛውን ጊዜ በሁሉም የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች አዳጋችነት ያለበት ሲሆን፣ በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ሂደት የተማሪዎች የቋንቋ እውቀት ዳራ ዝቅተኛነት፣ የመጻፍ ተጋልጦ ማነስ፣ የስህተት ፍርሃት፣ ከማስተማሪያ ዘዴና ከማስተማሪያ መሳሪያ በተወረሱ ጉድለቶች እንዲሁም በተማሪዎቹ የመጻፍ ተነሳሽነትና አመለካከት ጋር በተያያዙ ችግሮች የተነሳ ለበርካታ ተማሪዎች አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል (Presada & Badea, 2014፣ Heydari & Bagheri, 2012)፡፡

መጻፍ በመደበኛ መንገድ የምንማረው፣ የራሱ ህግና ሥርዓት ያለው መግባቢያ ነው፡፡ የቋንቋውን የጽሕፈት ህግ (የፊደላት አጠቃቀም) በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል፡፡ የቋንቋው የጽሕፈት ህግ ብቻ ሳይሆን ሀሳባችንን በጽሑፍ እንዴት መግለጽ እንዳለብንና ከአንባቢያችን ጋር ያለምንም ችግር እንዴት መግባባት እንደምንችል ማወቅ ያስፈልጋል ሲሉ የመጻፍን ክሂል አስቸጋሪ የሚያደርገውን ምክንያት Kavaliauskiene (2009) ይገልጻሉ፡፡

የመጻፍ ክሂል በአጠቃላይ መልኩና ለብዙ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አስቸጋሪ ወይም አዳጋች የሚሆንበትን ምክንያት Khansir (2012)፣ Sarfraz (2011) በተጨማሪ ጠቁመዋል፡፡ ይህም በርካታ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋቸው ውስጥ ያሉ የቃላት፣ የሰዋሰው ህግጋትን ጠንቅቀው ባለመረዳትና እነዚህን ህግጋትና ደንቦች በጽሁፍ ለመጠቀም ሰፊ ተጋልጦና ቀጣይነት ያለው የልምምድ እድል ማግኘት ባለመቻላቸው የሚከሰት ችግር መሆኑን ያመለከተ ነው፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሙት ምሁራን አክለው

እንደገለጹት አብዛኛውን ጊዜ በርከት ያሉ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላትን፣ ሃረጋትንና አረፍተ ነገሮችን ትርጉምና አገባብ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመፈለግ ይጠመዳሉ፡፡ በውጤቱም የሚያቀርቧቸው ጽሁፎች በቃላት፣ በሰዋሰው፣ አገባብና የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች የተመሉ ይሆናሉ፡፡ የቋንቋ መምህራን ትልቁ ችግርም ከመጻፍ ክሂል ጋር ለሚታገሉ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን የሚረዱ ትርጉም ያላቸው የማስተማሪያ ስልቶችንና ግብአቶችን በመጠቀም ለተሻለ የጽህፈት ክንዋኔ ማነሳሳት፣ ብሎም የተማሪዎቻቸውን ብቃት በማሳደግ ረገድ የተለመዱ የጽህፈት ስህተቶችን እንዳይፈጽሙ ማድረግ አለመቻል ነው፡፡

ከፍ ሲል ከቀረቡት ገለጻዎች በመነሳት ማጠቃለል እንደሚቻለው በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ጽህፈትን መተግበር ለአብዛኞቹ ተማሪዎች አስቸጋሪ ጉዳይ መሆኑን ሲሆን፤ ችግሩን ጉልህ የሚያደርጉ ከተማሪዎቹ የሚነሱ -- (1) የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት /ተጽዕኖ፣ (2) የታላሚው ቋንቋ ዳራ እውቀት ዝቅተኛነት፣ (3) መሰረታዊ ህግጋትን ለይቶ አለማወቅ፣ (4) የመጻፍ ልምምድ ማነስ፣ (5) የስህተት ፍርሃት እንዲሁም (6) በራስ ተነሳሽነትና ኃላፊነት በመውሰድ ለማወቅ ተነሳሽነትና አዎንታዊ አመለካከት ማጣት ተጠቃሽ ችግሮች ሲሆኑ፤ ከመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ (ለምሳሌ፡- መጻፍን ሂደታዊ በሆነ ስልት ከማቅረብ ይልቅ ውጤት ላይ ማትኮርና ተማሪዎቹ የመጻፍ ሂደቱን እንዲቆጣጠሩት አለማድረግ) እና ከማስተማሪ መሳሪያ የሚነሱ ወይም የሚወረሱ ችግሮች (በመማሪያ መጽሐፉ ህትመት ጊዜ የሚከሰቱ የፊደላትና የቃላት ስህተቶች፣ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ማህበረ-ባህላዊና የቋንቋ እውቀት ዳራ ያገናዘቡ ልምምዶችን መርጦ አለማቅረብ) የመጻፍ ክሂልን ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስብስብ የሚያደርጉ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የመጻፍ ክሂልን ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስብስብ የሚያደርጉ ምክንያቶች በአንዳንድ ምሁራን ተጠቁመዋል፡፡ Nonkokhetkong (2013) እንደገለጹት፣ መጻፍ ከንግግር የበለጠ ሥነልቦናዊ ጫና ያሳድራል፡፡ በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ስንናገር ስህተት ብንፈጽም ከአድማጭ እርማት እናገኛለን፤ ሀሳባችንን በጽሑፍ ስንገልጽ ግን ያለ ማንም እገዛና ያለምንም ማስተካከያ በራሳችን የምንወጣው ተግባር ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የስነልቦና ጫና ስለሚያሳድር መጻፍን አስቸጋሪ ያደርገዋል ብለዋል፡፡ እንደ Nonkokhetkong (2013) ገለጻ፣ በንግግር ወቅት ገለጻ ስናደርግ አድማጭ ንግግራችን እንዲቀጥል ያግዘናል ወይም ‹እንዲህ ማለት ፈልገህ ይሆን?› ሲል ጣልቃ በመግባት ሊያርመን ይችላል፡፡ ንግግራችን ላይ ችግር (ስህተት) ቢፈጠር

እየደገምን ወደኋላ እየተመለስን ‹እንዲህ ማለት ፈልጌ እኮ ነው› እያልን አስተካክለን ለመቀጠል የንግግር አውዱ ፈቃድ አይከለክለንም፡፡

በመጻፍ ጊዜ ግን እነዚህ ሁሉ እድሎች አብዛኛውን ጊዜ አይኖሩም፡፡ ተግባቦታችን በራሳችን ችሎታና እውቀት ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡ በራሳችን የቃላት ምርጫ፣ በራሳችን የቃላት መዋቅር፣ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ ሂደት በኋላ የጻፍነው ጽሑፍ በአንባቢ ወይም በአራሚ ይተረጎማል፡፡ በዚሁ መሰረት የጽህፈት ተግባር አብዛኛውን ጊዜ በፈጣን አውዳዊ እርምት የመደገፍ እድሉ ውሱን መሆን ለጽሁፍ ስህተቶች መከሰትና መደጋገም መንስኤ ይሆናል፡፡ ችግሩ በኢ-አፍ ፈቶች የሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ ባለመነቃቃት፣ በአእምሮ አለመረጋጋት፣ ባለማስተዋል፣ በድካም፣ በዘፈቀደ በመሳሰሉት ምክንያቶች የሚከሰት ‹‹ግድፈት›› ባለመሆኑ ተማሪዎቹ ራሳቸው ስህተቶቻቸውን ለማረም የማይችሉት ስልታዊ ስህተት በመሆኑ ነው፡፡ ሊታረም የሚችለውም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በቋንቋ መምህሩ አማካኝነት ይሆናል፡፡ የቋንቋ መምህሩ ስህተቱን በወቅቱ በማጤን ሊያርመው ካልቻለ የጽሁፍ ስህተቱ በመደጋገም ወደ ስህተት ልምድነት የሚያመራ ይሆናል፡፡

## 2.1 .3 .የስህተት ምንነት

ተማሪዎች በፅሁፍ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት አፋቸውን በታላሚው ቋንቋ የፈቱትም ሆነ ኢ-አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶች ይፈፅማሉ፡፡ ነገር ግን ስህተቶቹ ለተማሪዎች የቋንቋ እድገት አስተዋፆ የሚያደርጉ እንጂ የውድቀት ምልክት እንዳልሆኑ Dulay et al (2002) እና LittleWood (2006) ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም Norrish (1993) ፅሁፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ የሚታዩ ስህተቶች ከመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም በቋንቋው የፅህፈት ህግ ተቀባይነት የሌላቸውን የሆሄያት፣ የቃላትና የዐረፍተ-ነገር መዋቅር እንደሆነ ስህተቶች የሚፈፀሙት ከድምፅ፣ ከምዕላድ፣ ከቃላት ወይም ከአጠቃላይ የቋንቋ አጠቃቀም አንፃር ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ከስነ-ድምጻዊ ባህሪያት አንፃር የሚመነጩ የስህተት ዓይነቶች አስፈላጊ የሆኑ ድምፆችን በመግደፍና አላስፈላጊ የሆኑ ድምፆችን በመጨመር ስህተቶች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡  እንደ ስነ-ድምፃዊ ስህተቶች ሁሉ ሰነ-ምዕላዳዊና የቃላት ስህተቶችም አስፈላጊ የሆኑ ድምፆችን በመግደፍና አላስፈላጊ የሆኑ ድምፆችን በመጨመር ስህተቶች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡

### 2.1.4. የስህተት ትንተና ምንነትና ባህርያት

የስህተት ትንተና የተግባራዊ ስነ-ልሳን አንዱ ዘርፍ ሲሆን ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የስህተት ትንተና ተማሪዎች ቋንቋን እንዴት እየተማሩ እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ ነው፡፡ የስህተት ትንተና በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚፈፅሙትን ስህተት ለመተንተን ወይም ለማጥናት የሚከናወን ሂደት ሲሆን ከንውኑም አንድ ሰው ቋንቋን እንዴት መልመድና መማር እንደሚችል ለመገንዘብና በቋንቋ ትምህርት የጋራ የሆኑ ችግሮችን በመፈለግ ለማስተማሪያ ዘዴዎችና ለመርጃ መሳሪያ ዝግጅት ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን ለመሰንዘር ይካሄዳል (Erdogan, 2005)፡፡

የስህተት ትንተና ዘዴ በ1967 Corder በተባሉ ምሁር እንደተጀመረ ድርሳናት ይገልጻሉ፡፡ ንጽጽራዊ ትንተና የጥናት ዘዴ በቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ የሚከሰተው ስህተት ምንጩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አሉታዊ ሽግግር ብቻ እንደሆነ የሚገልጽ የጥናት መስክ ነበር፡፡ ይህ የጥናት ዘዴ ሌሎቹን የስህተት ምንጮች ለማጥናት ባለማስቻሉ የስህተት ትንተና ይህንን አብይ ክፍተት ለመሙላት ብሎም ለማስወገድ ብቅ ያለ የጥናት መስክ ነው፡፡

የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣ የታዩት ስህተቶች የሚተነተኑበትና የተተነተኑትም የስህተት አይነቶች በተለያዩ ምድብ አይነቶች የሚቀመጡበት ዘዴ ነው (Brown 1994)፡፡

Ellis (2003) Corder (1967)ን ጠቅሰው እንዳቀረቡት፤ የስህተት ትንተና ስህተትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከፋፍሎ በማጥናት የስህተት ምንጮችን ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ስለስህተት ያለውን አሉታዊ አመለካከት በማስቀረት ስህተትን እንደ አንድ የትምህርት ሂደት ይቆጥራል፡፡ ከዚህም በመነሳት ለሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት እንዲሁም ተማሪዎች ያሉበትን የእውቀት ደረጃ ለማመልከት ያገለግላል፡፡ በአሰራሩም የቋንቋ ተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በናሙናነት በመውሰድ ስህተቶችን ለይቶ ያወጣል፤ የስህተቶቹንም አይነት ምንጫቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መላ ይመታል፡፡

የስህተት ትንተና በሁለተኛ ቋንቋ ቅበላ ከፍ ያለ አዎንታዊ ተጽእኖ ለመፍጠር ከቻሉ የቋንቋ ትምህርት ንድፈ-ሃሳቦች መካከል አንዱና ዋንኛው ሲሆን፤ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን የስህተት አይነቶች ከታላሚው ቋንቋ መሰረታዊ ህግጋት ጋር በማነጻጸር በተፈጸሙት ስህተቶች ዙሪያ ትንተና የሚያቀርብ ነው (Brown, 1994)፡፡ በ Crystal (1999) መሰረት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የስህተት ትንተና ታላሚውን ቋንቋ በመማር ሂደት በተማሪዎች የሚፈጸሙ ተቀባይነት የሌላቸው ቅርጾች ጥናት ነው፡፡ በJames (2001) መሰረት የስህተት ትንተና የስነቋንቋ ቅርጾችና መዋቅሮች አለማወቅን ለመመርመር የሚያስችል መስክ ሲሆን ተማሪዎች ምን ምን እንደማያውቁና ከነዚህ ያለማወቅ ችግሮች ጋር በምን መልኩ ተቋቁመው ታላሚውን ቋንቋ እንደሚማሩ ለይቶ ለማወቅ የሚረዳ ነው፡፡

Ridha (2012) ስለ ስህተት ትንተና ምንነት በበኩላቸው ባቀረቡት ብያኔ፣ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ በተማሪዎች ጽሁፎችና ዲስኩሮች ውስጥ የሚገለጹ ከመደበኛው የቋንቋው ስርአት አፈንጋጭነት ባህርያትን የማጤን፣ የመተንተን፣ የመፈረጅ ሂደት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የስህተት ትንተና አቢይ ትኩረት በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚፈጸሙ በውል የሚታወቁ የቋንቋውን መሰረታዊ ህግጋትና ደንቦች አለመከተል ችግሮችን በመረጃዎች በተደገፈ ሁኔታ መፈተሽ ሲሆን ታላሚውን ቋንቋ ለመማር ተማሪዎቹ የተከተሉት ማፈንገጥ ምን እንደሚመስል መቃኘትንም ያካትታል፡፡

Abi-Samara (2003) በበኩላቸው የስህተት ትንተናን የስነቋንቋ ትንተና አይነት እንደሆነ በመግለጽ በተማሪዎች በሚፈጸሙ ስህተቶች ላይ እንደሚያተኩር ይገልጻሉ፡፡ Nonkokhetkong (2013) Corder (1967)ን በመጥቀስ እንደጠቆሙት፣ የስህተት ትንተና መረጃ ሶስት ጥቅሞች አሉት፡፡ ለመምህራን ስለተማሪዎቻቸው የትምህርት አቀባበል እርምጃ በጣም ጠቃሚ መረጃዎች ያቀብላቸዋል፡፡ ለተመራማሪዎች ስለ ተማሪዎች የቋንቋ አቀባበል ወይም የመማር ሂደት ማስረጃዎች ያቀርብላቸዋል፡፡ ለተማሪዎቹ ለራሳቸው ደግሞ ታላሚውን ቋንቋ ለመማር የሚያስችሉ ግብአቶች (resources) ይሆኗቸዋል፡፡

የጽህፈት ስህተትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ውጤታማ ስልቶችን ለመቀየስ የሚረዳው አንዱ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መምህራንና አጥኚዎች ተማሪዎች የጽህፈት ስህተቶችን የሚፈጽሙባቸውን ምክንያቶች ለይቶ ማወቅ ነው፡፡ በሚጽፉበት ቋንቋና ተማሪዎቹ ባሉባቸው መሰረታዊ የጽህፈት ችግሮች መካከል ጽኑ ቁርኝት እንዳለ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ዝርዝር የጽህፈት ስህተት ችግሮች ከዝርዝር የስህተት ምንጮች (specific sources) ይወረሳሉ፡፡ የአንድ ተማሪን አንድ ጽሁፍ ወስደን በአንድ ገጽ ላይ የፈጸማቸውን ተመሳሳይነት ያላቸው የጽህፈት ስህተቶች በመመልከት እንደ ፀሐፊው ሁኔታ የተለያየ የስህተት ምንጭ ሊኖራቸው እንደሚችል ያላቸውን ግምት (Linnea-Ehri, 2000) አመላክተዋል፡፡

የስህተት ትንተና ለመምህራን በጣም አስፈላጊ የሆነ የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ በተማሪዎቹ የሚፈጸሙ ስህተቶችን ነቅሶ በማውጣት እርማት ለመስጠትና የማስተማሪያ ስልትንም ለማሻሻል ያገለግላል፡፡ የስህተት ትንተና የቋንቋ ትንተና ዘርፍ ሆኖ ትኩረት የሚያደርገውም ተማሪዎቹ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ ነው፡፡ ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ከቋንቋው ስርዓት ጋር ያነጻጽራል ወይም ያወዳድራል፡፡ Corder የስህተት ትንተና ‹‹አባት››፣ የስህተት ትንተናን በአዲስ አተያይ በተመለከቱበት መጽሐፋቸው “The significance of Learner Errors” (1967)፣ ስህተትን ለተማሪዎቹ ለራሳቸው እንደ አንድ አስፈላጊ የመማሪያ መንገድ ጠቅሰውታል፡፡

የስህተት ትንተና እና ተገቢ የሆኑ ስህተቶችን የመቃኛ ብልሃቶች ትግበራ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ ተማሪዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ የአመንጪነት ክሂሎችን እንዲማሩ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በርካታ ልዩ ልዩ ስህተቶችን በጽሁፍ ውስጥ ስለሚፈጽሙ፣ Fang & Jiang (2007) ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እንዴት ያሉ ናቸው? ምን ያህል ይደጋገማሉ? ስህተቶቹን የሚፈጽሙበት ምክንያት ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር በምን መልኩ ይያያዛል? ተማሪዎቹ ምን ቢደረግላቸው ስህተቶቹን በመቀነስ ትክክለኛ ቅርጾችን በጽሁፎቻቸው ውስጥ ሊያሳዩ ይችላሉ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን በበቂ ሁኔታ ለመመለስ የሚቻለው የስህተቶችን ባህርያትና መንስኤ ምክንያቶች ለመተንተን በሚደረግ ጥረት ነው፡፡

## 2.1.5. የስህተት ትንተና አስፈላጊነት

የስህተት ትንተና መምህራን የተማሪዎቻቸውን ስህተቶች እንዴት መተንተን እንደሚችሉ ስልቶችን በማቅረብ በኩል ጠቀሜታ ያለው ተግባር መሆኑን Lott (2003) ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚፈጸሙ ስህተቶችን በስህተት ትንተና ዘዴ በመመርመር ለመምህራን የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ተማሪዎች ለምንና በምን ምክንያት የተነሳ ስህተቶችን እንደሚፈፅሙ ለማወቅና ተገቢ የሆነ ምላሽ እንዲሰጡ ለማድረግ ይረዳል፡፡ መምህራን በስህተት ትንተና ዘዴ ተጠቅመው ተማሪዎቻቸው የሚፈፅሙዋቸውን ስህተቶችና ተደጋጋሚ የሆኑ የስህተት አይነቶች በማጥናት እነዚህ ስህተቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በማስተማር ስልት ወይም ደግሞ በታላሚው ቋንቋ የተፈጠሩ ስህተቶች ይሁኑ አለዚያም ተማሪው በራሱ የፈጠራቸው ስህተቶችን በመለየት በክፍል ውስጥ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር ይረዳል፡፡ የስህተት ትንተና በማስተማር ሂደት ውስጥ የችግሮቹ መንስኤ የት እንደሆኑ ለመምህራን፣ ለመርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍት አዘጋጆች ስልሚያመለክቱና አንፃራዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ስለሚያስችሉ ነው፡፡

LittleWood (2006) እንደገለጹት፣ ስህተትን መረዳት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የደረሱበትን ደረጃ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ የስህተት ትንተና ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የተማሪዎች ሰዋስው እውቀት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ለመገመት ያስችላል፤ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ለሚፈፅሙዋቸው ስህተቶች ትኩረት ለመስጠት ያስችላል፤ ለሚፈፀሙ ስህተቶችም የመፍትሄ ሀሳብ ለመፈለግ ያስችላል፤ እንደዚሁም የተማሪዎችን ግላዊ የመማር ችግሮችን ለመረዳት ይጠቅማል፡፡

በአጠቃላይ በቋንቋ መማርና ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶች በየትኛው የቋንቋ ክፍሎች ውስጥ በብዛት እንደሚከሰቱ፣ የትኞቹ የስህተት አይነቶች የተማሪዎችን ተግባቦት ችሎታ እነደሚያደናቅፉ ለመገንዘብ ጉልህ ፋይዳ አለው፡፡

## 2.1.6. በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የስህተት ጉልህነት ላይ የማትኮር አላማ

በርካታ በስህተት ትንተና ላይ ያተኮሩ ንድፈ-ሀሳቦች አቅራቢዎች በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ስህተቶች ላይ ማትኮር አስፈላጊ የሚሆንበትን ምክንያት አቅርበዋል፡፡

Nonkokhetkong (2013) Corder (1967)ን ጠቅሰው እንደጠቆሙት፣ ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ስህተቶች ጉልህ ያደርጓቸዋል፡፡ አንደኛ ምክንያት መምህራን ለተማሪዎቻቸው በቋንቋ ትምህርቱ ዓላማዎች ተመርኩዘው ምን መማርና ማወቅ እንዳለባቸው፣ በቋንቋ መርሃ-ትምህርቱ መሰረት ምን ያህል ወደፊት እንደተራመዱና ምን ምን ማከናወን እንደሚቀራቸው መረጃና ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሁለተኛ በቋንቋ ትምህርትና በስህተት ትንተና በተደገፉ ተጨባጭ ጥናታዊ ግኝቶች ላይ በመደገፍ ተማሪዎች እንዴት የቋንቋ መማር ወይም ቅበላ ሂደት እንደሚሳካ፣ ምን አይነት ብልሃቶችንና አካሄዶችን በመከተል የቋንቋ መማር ሂደትን መቆጣጠር እንደሚያስፈልግ መጠቆም ያስፈልጋል፡፡ ሶስተኛ መምህራኑ ራሳቸው ለተማሪዎቹ የቋንቋ መማር ልምምድ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ማወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ስህተት በመስራታቸው ከስህተቱ የመማር እድል ያስገኝላቸዋል እንጂ ተጎጂ እንደማያደርጋቸው በስህተት ትንተና ላይ ያተኩሩ ንድፈ-ሀሳቦች ይጠቁማሉ፡፡

Darus & Subramaniam (2009) እንዳቀረቡት፤ በተግባር የተፈተኑ ጥናቶች ያረጋገጡት በተማሪዎች የመጻፍ ስህተት ትንተና ላይ አጽንኦት ማድረግ ተማሪዎች የጽሁፍ ትክክለኛነትን እንዲያሻሽሉ በጣም ውጤታማ መንገድ መሆኑን ነው፡፡ አክለውም ስለ ሰዋሰው አጠቃቀም ይበልጥ ማወቅ የሰዋሰው ትክክለኛ እና ስህተት አጠቃቀሞችን ለይቶ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ የጽሁፍ ስህተቶችን የጉልህነት ደረጃ እና የስህተቶቹን አፈጣጠር መለየት ይገባቸዋል፡፡ ይህም የሁለተኛ ቋንቋ መምህራኑን ስህተቶችን የመለየት ንቁ ትኩረት የሚጠይቅ፣ የተማሪዎቹን የሰዋሰው ችግሮች ለይቶ ማወቅን ግድ የሚል ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ተማሪዎቹ በታላሚው ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ ስለሚማሩት ቋንቋ ባህሪና የጽህፈት ስህተቶች ለምን እንደሚፈጸሙ የተሻለ መረዳት ካላቸው ስህተቶቻቸውን ለማረም የግል ተነሳሽነታቸው ከፍ ይላል፤ የስህተቶችን ጉልህነት በመቀነስ መጻፍ እንዲሞክሩ ያደርጋቸዋል፡፡

## 2.1.7. የጽሁፍ ስህተት አይነቶች

የሰዋስው ስህተት የሚባለው የቃላት እርባታና አገባብ፣ የሀረግ፣ የዓረፍተ-ነገር፣ የአንቀፅ ወዘተ በአንድ ላይ የሚያደርጉት ጥምረት ትክክል ባልሆነ መንገድ ሲዋቀሩ የሚያሳዩት ክፍተት ነው፡፡ Raimes (2003) እንደገለጹት፣ የቃላት እርባታ ስህተቶች የሚባሉት፣ የስም፣ የግስ፣ የተውሳከ ግስና የመስተዋድድ አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው፡፡ የአገባብ

ስህተቶች የሚባሉት የቃል፣ የሀረግ፣ የአንቀፅና በድርሰቶች ውስጥ ያሉ ስህተቶችን ይመለከታል፡፡ Norrish (1993) እንዳብራሩት፣ ሰዋስው ፊደሎች፣ ቀለሞችና ዓረፍተ-ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያስተምር ነው፡፡ የንግግርና የፅሁፈት ቋንቋ ስርዓትና ህግ ተከትሎ ለመጻፍ በቂ የሰዋስው እውቀት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ተማሪዎች በየትኛውም ቋንቋ በሚፅፉበት ጊዜ የሰዋስው ስህተት ይፈፅማሉ፡፡ የሰዋስው ስህተቶችም ስነ-ድምፃዊ፣ ስነ-ምዕላዳዊና ስነ-አገባባዊ ተብለው ይከፈላሉ፡፡

## 2.1.7.1. የስነ-ድምፅ ስህተት

ድምፅ በንግግር ጊዜ በአንደበት የሚፈጠረው ሲሆን ለማንኛውም ቋንቋ መሰረት ነው፡፡ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪም መልዕክት የሚያስተላልፈው የቋንቋውን ድምፆች በስርዓት አቀናጅቶ ቃላትን፣ ቃላትን አቀናጅቶ ሀረግ፣ ሀረግን አቀናጅቶ ደግሞ ዓረፍተ-ነገርን በመፍጠር ነው (ጌታሁን 1990)፡፡

ድምፅ ለንግግርም ሆነ ለጽሁፍ ቋንቋ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ ድምፆች ሲፈጠሩ ሃሳብን ለማስተላለፍ ስርዓት ባለው መንገድ አየር በአንደበት ክፍሎች እየታገደና እየተለቀቀ የሚፈጠር ሲሆን እያንዳንዱ ድምጽ ሲፈጠር የመፈጠሪያ ቦታውም ሆነ የአፈጣጠር ሁኔታው የተለያየ ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የለመዷቸው ድምፆች ጣልቃ በመግባት ወይም የቃል አመሰራረት ስርዓትን በማፋለስ ስህተት እንዲፈፅሙ ያደርጓቸዋል፡፡ ስህተቶችም የታላሚውን ቋንቋ ድምፆች ጠንቅቆ ካለማወቅና ስርዓታቸውን ካለመገንዘብ የሚከሰቱ ይሆናሉ፡፡

የስነ-ድምፅ ስህተቶች አድማጭና አንባቢን የማደናቀፍ ሀይላቸው በቀላሉ የሚገመት ላይሆን ይችላል፡፡ ሀይሉም እንደ ስህተቶች ብዛትና ስርጭት ይለያያል፡፡ በተጨማሪም የስህተቶች መጠን የሚበረክተው በአፍ መፍቻ ቋንቋና በሁለተኛ ቋንቋ መካከል ባሉት ድምፆች ልዩነት ነው፡፡ አንድ የቋንቋ ተማሪ ለቋንቋው መሰረት የሆኑ ድምጾችን በትክክል መለየት ካልቻለ በቋንቋው ተጠቅሞ ሀሳቡን በጽሁፍ ማስፈር አይችልም፡፡ ስነ-ድምጽን በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ ባህሪው የሚፈቅዳቸው ምስለት፣ ግድፈት፣ ቅየራ፣ ስርገት፣ ጥብቀት፣ ኢ. ምስለት የሚባሉ ስነ-ድምፃው ሂደቶች አሉ፡፡ የቋንቋው የሰዋስዋዊ ህግ ከሚፈቅደው ውጭ ሂደቶቹ ከታዩ ሰዋስዋዊ ስህተት ሊከሰት ይችላል ማለት ነው፡፡

## 2.1.7 .2 . የስነ-ምዕላድ ስህተት

ድምፆች በተናጠል ትርጉም አልባ ሲሆኑ እነዚህ ትርጉም አልባ ድምፆች ስርዓት ባለው መንገድ ተቀናጅተው ትርጉም ያለው አሃድ ያስገኛሉ፡፡ በዚህ መንገድ የሚገኙ አሃዶች ምዕላዶች ይባላሉ፡፡ እነዚህ ምእላዶችም ነፃ ምዕላድና ጥገኛ ምዕላድ በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ የምዕላዶች ቅንጅት ቃላት ይመሰርታል፡፡ ይህ የቃላት ውስጣዊ መዋቅር የሚጠናበት የስነ-ልሳን ዘርፍ ስነ-ምዕላድ ይባላል (ባየ፣ 1987)፡፡

ድምፆች ስርዓት ባለው መልኩ ተቀናጅተው ምዕላድን የሚያስገኙ ቢሆኑም ነገር ግን ቅንጅታቸው የተዛባ ከሆነ ስነ-ምዕላዳዊ ስህተት ሊፈጸም ይችላል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በጽህፈት ወቅት ምዕላዳዊ ስህተት ጎልቶ ይታይባቸዋል፡፡ በተለይ የቅጥያ ምእላዶችን በትክክለኛ ቦታቸው የማስቀመጥ ችግር፣ ምዕላዶችን የመግደፍና አላስፈላጊ ምዕላዶችን የመጨመር ችግር ይታይባቸዋል፡፡ እንደ Selinker (2000) በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚታየው ስህተት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ምእላዶች ጠንቅቀው ባለማወቅና ምእላዶች እንዴት ተቀናጅተው ቃላት ሊመሰርቱ እንደሚችሉ ባለመገንዘባቸው ሲጽፉ ስህተት ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ ስህተቶችም የምዕላድ መገደፍ፣ ካለቦታው በማስገባት ቅደም ተከተሉን በማዛባትና ከሌሎች ምዕላዶች ጋር አመሳስሎ በመጠቀም ወዘተ ይከሰታሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ የምንረዳው ምዕላዶች የቋንቋው ህግ በሚፈቅደው መሰረት ተቀናጅተው ካልቀረቡ የሰዋስዋዊ ስህተቶችን ሊያስከትሉ መቻላቸውን ነው፡፡

## 2.1.7.3. የስነ-አገባብ ስህተት

ምዕላዶች ወይም ቃላት ስርዓት ባለው መልኩ ተቀናጅተው የሚመሰረቱበት ሀረግ ወይም ዓረፍተ-ነገር ውስጣዊ አደረጃጀት የሚጠናበት የስነ-ልሳን ዘርፍ ስነ-አገባብ ነው፡፡ ጌታሁን (1990፡123) እንዳብራሩት፣ የአንድ ቋንቋ ድምፆች ወይም ምዕላዶች በስርዓት ተዋቅረው ቃልን ይመሰርታሉ፡፡ ቃላትም በስርዓት ተዋቅረው ከቃላት በላይ የሆነ የሀረግ መዋቅር ይመሰርታሉ፡፡ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሁፎች ውስጥ ያሉ ቃላት፣ ሀረጋት፣ ዓረፍተ-ነገርና አንቀጾች ውስጥ የተቀናጁ ቃላት አገባባዊ ስርዓታቸውን በመመልከት ትክክለኛ ስርዓቱን ጠብቀው መቀናጀት አለመቀናጀታቸውን የሚመለከት ክፍል ስነ-አገባብ ነው፡፡

### 2.1.8. አንቀጽ

አንቀጽ አንድ ነጠላ ሐሳብን ለመግለጽ ሲባል በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሐሳብ ተዛምዷቸውን የጠበቁ አረፍተነገሮች የሰፈሩበት የድርሰት ቅርጽ ነው፡፡ አንቀጽ ብዙውን ጊዜ አንድ ኃይለ ቃል ወይም መንደርደሪያ አረፍተነገር እና ከአንድ በላይ መዘርዝር አረፍተነገሮችን ሊይዝ ይችላል (ደመላሽና ሳህሉ፣ 2004)፡፡

በጥሩ ሁኔታ የተጻፉ አንቀጾች ሁሉ ኃይለ ቃል አላቸው፡፡ ኃይለ ቃል የአንቀጹን ማእከላዊ ሀሳብ የያዘና አብዛኛውን ጊዜ በአንቀጹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ አረፍተነገር ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን እንደ ጸሃፊዎች ምርጫ ኃይለ ቃሉ በአንቀጹ መሃል ወይም መጨረሻ ላይም ሊመጣ ይችላል፡፡ ኃይለ ቃል፣ ርእሳዊ አረፍተነገር፣ መሪ አረፍተነገር፣ መንደርደሪያ አረፍተነገር የሚሉ ስያሜዎች ይሰጡታል፡፡ አልፎ አልፎ የአንቀጹን ርዝማኔ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ኃይለ ቃሉን በአንቀጽ ውስጥ ሁለት ጊዜ ማቅረብ የሚቻልበትም መንገድ አለ፡፡ ሆኖም ሁለቱ ኃይለ ቃሎች በተለያየ መልክ /አባባል/ መቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአንቀጽ ቅርጾችም በኃይለ ቃሉ መገኛ ቦታ ይወሰናሉ (ደመላሽና ሳህሉ፣ 2004)፡፡

ከፍ ሲል በቀረበው ገለጻ እንደተመለከተው አንቀጽ በአንድ ዋንኛ ሀሳብ ላይ ተመርኩዞ የሚቀርብና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ዘርዛሪ ሀሳቦች የተገነባ የድርሰት ቅርጽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተጠኚዎቹ የሚጽፉት የአንቀጽ ኃይለ ቃልን እና መዘርዝሮችን ያሟላ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ከዚህ አኳያ ተጠኚዎቹ የሚጽፏቸውን አንቀጾች ለመገምገም /ለማረም/ የሚረዱ መቃኛ ነጥቦችን ማዘጋጀት ተገቢ ይሆናል፡፡

በአንቀጽ ውስጥ የሚገኑ ስህተቶችን ለማረም የሚረዱ መስፈርቶችን ማዘጋጀት ተገቢ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ጥናት የሚከተሉት የደመላሽና ሳህሉ (2004፣ 116) የጥሩ አንቀጽ መቃኛ መስፈርቶች ተጠቁመዋል፡፡

1) ርእስ ጠብቆ መጻፍ፣
2) የአንቀጹን ዋና ሐሳብ በግልጽ ማሳየት፣
3) ዋናውን ሐሳብ በተገቢ መዘርዝሮች መግለጽ፣
4) ሀሳብን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
5) ቃላትን በአግባቡ መጠቀም፣
6) የተሟላ አረፍተነገር መጠቀም፣
7) ተገቢ ስርአተነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀም፣

8) የሃሳብ አንድነትና ግጥምጥምነት ያለው አንቀጽ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 2.1.9. የስህተት ትንተና መርሆዎች

Ellis & Barkhuizen (2005) Corder (1974) ን ጠቅሰው ባቀረቡት ገለጻ የስህተት ትንተና በአምስት ደረጃዎች ተከፍሎ የሚካሄድ ክንውን ነው፡፡

1. **ስለ ተማሪዎቹ የቋንቋ መማር ሁኔታ ናሙና መረጃ መሰብሰብ፡-** በተማሪዎች የቋንቋ መማር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ መረጃ ለማግኘት የስህተት ትንተና አጥኚው ናሙና የስህተት መረጃዎችን መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ደረጃ አጥኚው የተጠኚዎቹን የስህተት ባህርያት በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው የተጠኚዎቹን መጠንና ባህሪ ገድቦ መግለጽ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡ ይህን አይነቱን ናሙና መረጃ አጥኚው ተማሪዎቹ ከሚጽፉት ድርሰት ወይም ፈተና በቀጥታ ማግኘት ይችላል (ገጽ 57)፡፡

2. **ስህተቶችን መለየት፡-** የስህተት ልየታ ተማሪዎቹ የሚያመነጯቸውን ጽሁፎች በመውሰድ በተመሳሳይ አውድ በታላሚው ቋንቋ መዋቅራዊ ስርአት ወይም የቋንቋው ባለቤቶች ከሚጠቀሙበት መንገድ ጋር የማወዳደር ሂደት ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጥኚው የትኞቹ የተማሪዎቹ የጽሁፍ ክፍሎች በታላሚው ቋንቋ መዋቅራዊ ወይም ሰዋሰዋዊ ስርአት የተለዩ ወይም ያፈነገጡ መሆናቸውን ለይቶ ለማወቅ ይችላል (ገጽ 58)፡፡ ስህተት ልየታ ለስህተቱ አይነት ማለትም ከትክለኛው አጻጻፍ የማፈንገጥ ደረጃ፣ ያልተለመደ የግስ አደራደር፣ ተገቢ ያልሆነ ቅጽል፣ መስተዋድድ ወይም መስተፀምር አጠቃቀም በአጠቃላይ ሰዋሰዋዊ አደረጃጀቶችን ሁሉ የሚቃኝ ይሆናል፡፡

3. **ስህተቶችን መግለጽ፡-** በስህተቶች ገለጻ ደረጃ አጥኚው በተለምዶ ስነቋንቋዊ ምደባ (linguistic taxonomy) የቋንቋውን መዋቅራዊ ስርአት ገጽታ መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን የአረፍተ ነገር አጠቃቀም ከቋንቋው ተናጋሪዎች /ባለቤቶች/ መደበኛ የአረፍተ ነገር አጠቃቀም ጋር የሚገለጽ ይሆናል፡፡ ስህተቶች የሚገለጹበት መንገድ በስህተት አይነቶች በመከፈል ሲሆን፤ የስምምነት ስህተቶች (errors of agreement)፣ የግስ ቅርጾች (verb forms)፣ አያያዥ ቃላት እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

4. **ስህተቶችን መተንተን፡-** በስህተት ትንተና ደረጃ የሚተኮርበት ጉዳይ ስህተቶቹ ከምን ሊነሱ እንደቻሉ ማብራራት ነው፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው ተማሪዎች ስህተቶችን የሚፈጽሙት ሁለተኛ ቋንቋን ለመማርና ተግባቦት ለማካሄድ ባሉባቸው ችግሮች ነው፡፡ በስህተት ትንተና ጊዜ አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባው ሌላው ጉዳይ የስህተቶቹ አይነቶች አንጻራዊ የድግግሞሽ መጠን (relative frequency) የመግለጽ አስፈላጊነት ነው፡፡

5. **የስህተት ግምገማ፡-** የስህተት ግምገማ ተጨማሪ የስህተት ትንተና ዘርፍ ሲሆን የተለያዩ የስህተት አይነቶችን የጉልህነት ደረጃ ለይቶ በማወቅ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹን በየትኞቹ ላይ አጽንኦት ሰጥቶ ማስተማር እንደሚያስፈልግ ለመወሰን የሚረዳ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ አጥኚው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹን የተባባሱ የመጻፍ ችግሮች ለማቃለል የሚያስችሉ የልምምድ ማትኮሪያዎች (remedial drills) አብሮ ማቅረቡ የስህተት ትንተናውን ጠቀሜታ ከፍ ያደርገዋል (Ellis & Barkhuizen, 2005)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ Ellis & Barkhuizen (2005) አረፍተ ነገሮች ከትክክለኛው አወቃቀር እንዴት ሊያፈነግጡና ተማሪዎቹ በአረፍተ ነገር ደረጃ ስህተት ሊፈጽሙ እንደሚችሉ አራት መክፈያዎችን አበጅተዋል፡፡ እነዚህ መክፈያዎችም፡-

**ጭመራ (Addition)፡-** ጭመራ የሚያመለክተው ተማሪዎች በሚጽፉት አረፍተ ነገር ውስጥ አላስፈላጊ የሆኑና ከዋናው ሃሳብ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ጉዳዮች መኖር ነው፡፡ እነዚህ አላስፈላጊ የሚባሉ በተማሪዎች አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚከሰቱ ቃላት ከዋናው አረፍተ ነገር ጋር ፈጽሞ ህብረያ ወይም ግንኙነት የሌላቸው ናቸው፡፡ ተማሪዎች ይህን የአላስፈላጊ ቃላት ጭመራ ለማድረግ ምክንያት የሚሆናቸው የተወሰኑ ሰዋሰዋዊ ህግጋትን በታላሚው ቋንቋ ሲጽፉ አብዝተው በመጠቀማቸው ነው (Ellis & Barkhuizen, 2005)፡፡

**መተው (Omission)፡-** ይህ የስህተት አይነት የሚያመለክተው በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የግድ መኖር የሚገባውን ቃል ሳያስገቡ በመቅረት ነው፡፡ ይህ አይነቱ ስህተት የሚፈጸመው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የመጀመሪያ እርከኖች ላይ ነው (Ellis & Barkhuizen, 2005)፡፡

**የተሳሳተ አወቃቀር መከተል (Misformation)፡-** የተሳሳተ ውቅር የሚገለጸው ትክክለኛ ያልሆኑ የቃላት እርባታ ወይም መዋቅርን በመጠቀም ነው፡፡ ይህም የመደብ፣ የጾታ፣ የቁጥር አለመስማማትን ይጨምራል (Ellis & Barkhuizen, 2005)፡፡

**የተሳሳተ አደራደር መከተል (Misordering)፡-** የተሳሳተ አደራደር ቃላትን ያለ ቦታቸው አስገብቶ መደርደርን ይመለከታል፡፡ ይህም በታላሚው ቋንቋ የአረፍተ ነገር አደራደር ስርአትን ካለመከተል ይመነጫል (Ellis & Barkhuizen, 2005)፡፡

በእነ Ellis & Barkhuizen (2005) የስህተቶች መፈረጃ መስፈርቶች ላይ James (2001) አንድ ተጨማሪ የስህተት መፈረጃ አቅርበዋል፡፡ ይህም ቅየጣ ወይም መደባለቅ (Blends) የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል፡፡ የቅየጣ ወይም መደባለቅ ስህተት

የሚያመለክተው ተመሳሳይ ተግባር ያላቸውን ሁለት ቃላት በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ አንድ ቦታ ላይ በማስገባት የሚፈጠር ስህተት ነው፡፡

ከፍ ሲል በEllis & Barkhuizen የተጠቀሱት በአረፍተ ነገሮች ውስጥ አላስፈላጊ ጭመራ ማድረግ፣ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የግድ መኖር የሚገባውን ቃል ሳያስገቡ መቅረት፣ የተሳሳተ የአረፍተ ነገር ውቅርና አደራደር መከተል በዚህ ጥናት ተተኳሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ገጽታና የስህተቶቹን የጉልህነት ደረጃ ለመመርመር የሚያስችሉ በመሆናቸው በዚህ ጥናት ይተኮርባቸዋል፡፡

## 2.1.10. የNorrish የስህተት ትንተና ሞዴል

ለዚህ ጥናት የሚስማማ የስህተት መተንተኛ (መቁጠሪያ) ብልሃት መምረጥ አስፈላጊ በመሆኑ Norrish (1993) ስህተቶችን በአይነት ለመመደብ ፣ ለመቁጠርና ድግግሞሻቸውን ለማወቅ ያቀረቡት የስህተት አተናተን ስልት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ Norrish የስህተት ቆጠራን ለማከናወን መሰረት ያደረጉት የድርሰት ጽሁፍን መነሻ አድርገው ሲሆን በዚህ ጥናትም ለአንቀጽ ፈተና እንዲስማማ አድርጎ ለማቅረብ ይሞከራል፡፡ በ Norrish መሰረት፡-

- ድርሰቶቹ የተጻፉበት የቃላት ብዛት እንዲደመር ማድረግ፡፡
- ስህተቶቹ አስቀድሞ በተመደበላቸው ምድብ እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ በእያንዳንዱ የስህተት አይነት የተፈጸሙ የስህተት ብዛቶች መለየት፡፡
- ድርሰቶቹ የተጻፉበትን ቃላት መጠን ለድርሰቶቹ ቁጥር በማካፈል በአንድ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው አማካይ የቃላት ብዛት ማወቅ፡፡
- የስህተቶቹን መጠን ለድርሰቶቹ በማካፈል በአማካይ በአንድ ድርሰት ውስጥ ምን ያህል ስህተቶች እንደሚገኙ ማወቅ፡፡
- አጠቃላይ የቃላቱን ብዛት ለአጠቃላይ የስህተት ብዛት በማካፈል አንድ ስህተት በምን ያህል ቃላት ውስጥ እንደሚገኝ መተንበይ፡፡
- የስህተቶቹን መጠን በመቶ በማባዛት እና የተገኘውን ውጤት ድርሰቶቹ በተጻፉበት የቃል ብዛት በማካፈል በመቶ ቃላት ምን ያህል የስህተት ድግግሞሽ እንዳለ ማወቅ፡፡

## 2.2 .የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ በአማርኛ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በፅሕፈት ጊዜ በሚፈፅሟቸው ስህተቶች ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ የተለያዩ ጥናቶችን ለመፈተሽ ሞክራለች፡፡ ከነዚህ ጥናቶች መካከልም አብዛኞቹ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ናቸው፡፡

ሁሴን (2009) በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፈ-ፈትና ኢ-አፈ-ፈት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማም በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፈ-ፈትና ኢ-አፈ-ፈት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድም ቅይጥ የምርምር ዘዴን ስራ ላይ አውሏል፡፡ በተገኘው ውጤትም በቃላት አጠቃቀምና ምርጫ፣ በሰዋስው አጠቃቀም፣ በአንቀጽ አደረጃጀት፣ በፊደል ቅርጽ አጣጣልና አጠቃቀም አማርኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች ከኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎች የተሻለ ሆነው መገኘታቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ደግሞ አማርኛ ኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች ከአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ተገኝ (2000) አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ
መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ዓላማውም አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች መተንተን ሲሆን ቅይጥ የምርምር ዘዴን ተጠቅመዋል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት ስህተቶቹ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ሲሆኑ፤ የስህተቶቹ ምንጭደግሞ በውስጠ ቋንቋ፣ በመማር ማስተማር ሂደትና በመማሪያ መሳሪያዎች እንዲሁም በስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታ መሆኑ ተገልጿል፡፡

አሰጋሽ (2013) በሸከኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር እና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም መሆናቸውን ለይተዋል፡፡ ተካቡ (2011) ባቀረቡት ጥናት የአማርኛ አፍ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋሰዋዊ

ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚለው ጥናታቸው በድምፅ፣ በምዕላድ፣ በቃላት ድግግሞሽ እና ያልተለዩ ስህተቶች እንደፈጸሙ ለመለየት ችለዋል፡፡

የአምላክሥራ (2008) የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና፤ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ ዋና ዓላማዋም አማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ጽሑፍ በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች የስህተት ትንተና ዘዴን በመጠቀም መተንተን ሲሆን የጥናቱ ዘዴን በተመለከተም ቅይጥ የምርምር ሂደትን ተጠቅማለች፡፡ በጥናቷ ግኝትም ከድርሰት እርማት በተገኘው መረጃ መሰረት ጠቅላላ የስህተቶች ብዛት 1066 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 44.84% የቋንቋ አጠቃቀም፣ 43.73% የቋንቋ አወቃቀር እንዲሁም 11.44% የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች እንዲሁም በተማሪዎችና በመምህራን ከተሞሉ መጠይቆች በተገኙ መረጃዎች መሰረት የስህተቶቹ ምንጮች የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅትና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት እና የስነልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለማቃለል የማስተማሪያ መሳሪየዎችን አዘገጃጀት እና የማስተማሪያ ዘዴወችን ማሻሻል፤ እንዲሁም ተማሪዎች ትምህርቱን በፍላጎት እንዲማሩ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚሉ መፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

ደብሬ (1990)፣የአምላክስራ (2008)፣ መሰረት (2003) እንዲሁም ተካቡ (2011) ይገኙበታል፡፡ በተካቡጥናት ‹‹የአማርኛ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋሰዋዊ ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና” በሚለው ጥናታቸው በድምፅ፣ በምዕላድ፣ በቃላት ድግግሞሽ እና ያልተለዩ ስህተቶች እንደፈጸሙ ለመለየት ችለዋል፡፡ ደብሬ (1990 “በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና” በሚል ጥናታቸው ውስጥ በተማሪዎች የተፈጸሙ ስህተቶችን ለይተው አሳይተዋል፡፡ ስህተቶቹም የቋንቋ አጠቃቀም፣ አወቃቀር እና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ነበሩ፡፡ መሰረት (2003) አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የለዩአቸውን በተማሪዎቹ የተፈጸሙ ስህተቶች ለይተው አቅርበዋል፡፡

አንደ መሰረት ገለጻ ችግሮቹ ተማሪዎቹ የፈጸሙት የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች ነበሩ፡፡

አጥኚዎቹ በጥናታቸው እንዳሰፈሩት በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ

ተማሪዎችም የጽህፈት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ የዚህ ችግር ምክንያት የቋንቋ ትምህርት በሀገሪቱ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ባለመካተቱ የመነጨ አይደለም፡፡ የክሂሉ የትምህርት አሰጣጥ የተዳከመና በተለይም ከአንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትኩረት የተነፈገው ከመሆኑ ጋር እንደሚያያዝ ይጠቁማሉ፡፡

የመጻፍ ክሂል ትምህርት አሰጣጥ የራሱ ህግ ያለው ቢሆንም ተማሪዎች ሲጽፉ ከህጉ ውጪ የተለዩ ስህተቶችን ይፈጽማሉ፡፡ የተጠቀሱት ጥናቶች ትኩረት ያደረጉት የስህተት ትንተና ላይ ነው::

የመሰረትና የደብሬ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በኦሮምኛ አፊ ፊት ተማሪዎች በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ሲሆን ፣ልዩነታቸው የመሰረትና የደብሬ በድርሰት አጻጻፍ ላይ ሲካሄድ፣ ይህ ጥናት በአንቀጽ አጻጻፍ ላይ መሆኑ ነው፡፡ በሚካሄድበት ቦታም ልዩነት አላቸው፡፡

የተካቡ ጥናት አማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሙት ሰዋሰዋዊ ስህተትን የሚያሳይ ነው፡፡በአንቀጽ ትንተና ላይ መካሄዱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ በሚካሄደው ቋንቋና በሚካሄድበት ቦታ ይለያያሉ፡፡

ከተጠቀሱት ጥናቶች በተለየ አፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ሳይለይ የተማሪዎች ጽሑፍ ላይ የተሰሩ የተወሰኑ የሀገር ውስጥ ጥናቶችም ይገኛሉ፡በአጠቃላይ ከላይ የተዳሰሱት ጥናታዊ ጽሑፎች በተለያዩ አገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ እና አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተለይቶ ያልታወቀ ተማሪዎጥናቶቹ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዋና ጉዳይ የስህተት ትንተና (Error Analysis) ጥናት ማድረጋቸው ሲሆን ለጥናቱም መነሻ በመሆን የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ሁሉም ጥናቶች በአማርኛ ኢ-አፍ-ፈት እና አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ባልተለየ ተማሪዎች ላይ የተሰሩ ቢሆኑም በኦሮምኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ በሚፈጽሙት ስህተትቶች የተሰሩ ጥናቶች ውሱን ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም ይህን ክፍተት በማየት

**በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲፅፉየሚፈፅሟቸውንስህተቶችናየስህተትምንጮችየፈተሸነው፡**

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት የሚከተለው የአጠናን ዘዴ ተንታኝ (analytiical) ጥናታዊ ዘዴ ነው፡ምክንያቱም በዚህ ዘዴ በመታገዝ ‹‹ምን ተደረገ?›› ‹‹እንዴት ተደረገ?›› የሚሉ ጉዳዮችን ወደ ችግሩ ተጠግቶ በመተንተን ማወቅ ስለሚቻል ነው (Singh, Howell & Rhoads, 1990)፡፡ ዘዴው ችግሮችን ከመግለጽ ባለፈ ‹‹ምን?›› እና ‹‹እንዴት ሊሆን ቻለ?›› የሚሉ ጉዳዮችን በማንሳት በሁኔታዎች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን አስሶና መዝኖ ለማቅረብ ይረዳል፡፡ ይህ ጥናት በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአንቀጽ ጽሑፋቸው ላይ የፈጸሟቸውን ስህተቶች አይነት፣ ብዛትና የስህተት ምክንያት ለመተንተን የተከተለው መጠናዊ ስልት ነው፡፡

### 3.2.የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት የተካሄደው በጅማ ዞን በነዲ ጊቤ ወረዳ ዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

### 3.3. የንሙና አመራረጥ ዘዴ

#### 3.3.1. የትምህርት ቤት ንሙና አመራረጥ

በነዲ ጊቤ ወረዳ ውስጥ ስድስት (ዲምቱ ቁጥር አንድ፣ ዲምቱ ቁጥር ሁለት፣ አኮ፣ ገበራ፣ ራጋ እና ጌሼ) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል በአመቺ የንሞና ዘዴ ዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለጥናቱ [ተመርጠዋል፡፡ ዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበት ምክንያት ጥናቱ ተማሪዎች አንቀጽ ሲፅፉ የሚፈጽሙዋቸውን ስህተቶች መተንተን እንደመሆኑ መጠን የትምህርት ቤትን ልዩ ትብብር እና ሌሎች ድጋፍ የሚያስፈልጉ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚጠይቅ በመሆኑ እና ተመራማሪዋም እነዚህን ድጋፎች በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ በቅርበትና በተቀላጠፈ ሁኔታ እንደምታገኝ ማሰብ በመቻሏ ነው፡፡ ሌሎቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተራራቀ አካባቢ የሚገኙ በመሆናቸው የአንቀጽ መፃፍ መረጃዎችን በቶሎ ለመሰብሰብ አዳጋች ሁኔታ መኖሩ የአጥኚዋ ስጋት በመሆኑ ቀርተዋል፡፡

### 3.3.2.. የክፍል ደረጃ ንሙና አመራረጥ

በስህተት ትንተናን በየትኛውም የክፍል ደረጃ ላይ ተመርኩዞ ማካሄድ ይቻላል፡፡ በተተኳሪው ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ማተኮር የተፈለገበት ዋነኛ ምክንያት አጥኚዋ ከሌሎች ክፍሎች በበለጠ የክፍለ ጊዜ ስርጭ ያለው ክፍል በመሆኑና ተማሪዎቹን በተሻለ ሁኔታ ፈቃደኛ ይሆናሉ በሚል እምነት የመረጃ አሰባሰቡን ሂደት እንደሚያቀላጥፍላት በማሰቧ የተደረገ ምርጫ ነው፡፡ ሌላው ምክንያት እነዚህ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ጀማሪ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ደረጃ ገብተው ከታች ክፍል ምን የተለየ ለውጥ አመጡ የሚለውን ለማየት እና ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የሚጠቅም በመሆኑ ለጥናቱ ተመራጭ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል የሁለተኛ ደረጃ መጀመሪያ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት በአንጻራዊነት የጽህፈት መልመጃዎች ሰፋ ያለ ሽፋን የሚያገኙትና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍትም በአገር አቀፍ ደረጃ በተመሳሳይ አቀራረብ መዘጋጀት የሚጀምርበት የክፍል ደረጃ ከመሆኑ አንጻር የጥናቱን ወካይነት ሊያሰፋው ይችላል በሚል እሳቤ ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ተተኳሪዎች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ የክፍል ደረጃ የተመረጠው በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ነው፡፡

### 3.3.3. የተጠኚዎች አመራረጥ

የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት በ2015ዓ.ም የትምህርት ዘመን በዲምቱ ቁጥር አንድ ሁለተኛ ደረጃ በአምስት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ 337 (ወንድ 135፣ ሴት 202) ተማሪዎች እንዲሁም በዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሦስት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ 144 (ወንድ 54፣ ሴት 90) የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ስምንት መማሪያ ክፍሎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛት 481 ሲሆን ሁሉም የኦሮምኛ አፍ- ፈት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ተማሪዎች መካከል 30% የሚሆኑትን በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ (Simple Random Sampling) በመጠቀም በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት በዲምቱ ቁጥር 1 ሁለተኛ ደረጃ በአምስት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ 337 ተማሪዎች መካከል በ30% 101 ተማሪዎች በተጠኚነት የተወሰዱ ሲሆን፣ በዲምቱ ቁጥር 2 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚማሩ 144 ተማሪዎች መካከል በ30% 44 ተማሪዎች በተጠኚነት ተመርጠዋል፡፡

ከሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት ተጠኚዎች አጠቃላይ ድምር 145 ነው፡፡ ቀጣዩ ተግባር በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ የተሳታፊዎቹን ማንነት መወሰን ሲሆን ከየክፍሉ ስም መጥሪያ በመውሰድ በእጣ በተበየኑ ቁጥሮች መሰረት በተወሰነ ርቀት (fixed interval) ተመዝግበው የሚገኙ ተማሪዎች ተሳታፊ ተደርገዋል፡፡ በእጣ ከተመረጡት ተማሪዎች የሚሰበሰበው መረጃ ለጥናት ስራ ብቻ የሚውል መሆኑ ተገልጾና በጥናቱ ለመሳተፍ ፈቃደኝነታቸው ተጠይቆ ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው በጥናቱ ተሳታፊ ተደርገዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህ ጥናት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በስራ ላይ አውሏል፡፡ እነሱም የአንቀጽ ፈተና እና በተማሪዎቹ የተሞላ መጠይቅ ናቸው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት ከተጠኚዎቹ ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡

### 3.4.1. የአንቀጽ ፈተና

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በአንቀጽ መጻፍ ስህተት ላይ ነው፡፡ በአንቀጽ መጻፍ ፈተናው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ የቋንቋ ልምድና ባህል መሰረት ያደረገ የአንቀጽ መጻፊያ ርዕስ ቀርቦላቸዋል፡፡ ተጠኚዎቹ በተመረጠው ርእስ አንቀጽ የጻፉት ሁለት ጊዜ ነው፡፡ ይህም  የተደረገበት ምክንያት አንድ ጊዜ ብቻ የተጻፈን አንቀጽ መሰረት በማድረግ ትንታኔ ከማካሄድ እና ወደ ማጠቃለያ ከማምራት ይልቅ ሁለት ጊዜ ማስጻፉ የስህተቶችን መፈጸም ለማረጋገጥ ይበልጥ ይረዳል ተብሎ በተመራማሪዋ በመታመኑ ነው፡፡

ለተጠኚዎቹ ሁለት ጊዜ የቀረቡላቸው የአንቀጽ መጻፊያ ትእዛዛት ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይህም አንድ አይነት ይዘትን ደጋግሞ በመፈተን (test--retest) ዘዴን በመከተል ተጠኚዎቹ በሚጽፏቸው አንቀጾች ውስጥ የፈጸሟቸውን ስህተቶች በችኮላና ባለመረጋጋት ጫናዎች ከሚፈጸመው ‹‹ግድፈት›› ለመለየት /ለማጣራት/ እንደሚረዳ በማሰብ እንዲሁም ደግሞ በመፈተን ስልት የትኞቹ የመጻፍ ክሂል ስህተቶች ወጥ በሆነ መልኩ ተደጋግመው የተፈጸሙ እንደሆኑ ለመለየት ነው፡፡

#### 3.4.1.1. የአንቀጽ ፈተና አዘገጃጀት

የአንቀጽ መጻፍ ፈተና አዘገጃጀትን በተመለከተ በቅድሚያ አጥኚዋ አምስት የአንቀጽ መጻፊያ ርእሶችን አዘጋጅታለች፡፡ አንቀጹን ለመጻፍ በአጥኚዋ የተዘጋጁና በሶስት የአማርኛ መምህራን የተገመገሙ፤ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ባህልና አኗኗር ዘይቤ

መሰረት ያደረጉ አምስት ሀይለ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎቹ ከቀረቡት ርዕሶች ውስጥ አንድ ርዕስ መርጠው ተዘጋጅተውበት አንቀጽ እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ የአንቀጹ መጻፍ ትኩረት በጥናቱ ዓላማ መሰረት በተማሪዎች ጽሑፍ ውስጥ የሚታዩ የስህተት አይነቶች መለየት እና በእያንዳንዱ ጽሑፍ የሚገኘውን የስህተት መጠን መፈተሽ የሚያስችሉ መረጃዎችን ማስገኘት ነበር፡፡

### 3.4.1.2. የአንቀጽ ፈተና አስተራረም

ለተጠኚዎቹ የቀረቡላቸው የአንቀጽ መጻፍ ፈተናዎች በአጥኚዋና በሌሎች ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥንቃቄ እንዲታረሙ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የአንድ ተጠኚ የጽህፈት ስህተት በሦስት መምህራን የመታረም እድል አግኝቷል፡፡ አንዱ አራሚ በሌላው አራሚ እርማት ሂደት ተደግፎ እርማቱን አላከናወነም፡፡ ስለ እርማቱ አሰራር አጥኚዋ ከሁለቱ ተባባሪ አራሚዎች ጋር ከእርማቱ በፊት ምክክር በማካሄድ የእርማቱን አላማና አካሄድ አስጨብጣለች፡፡ በዚሁ መሰረት በኦሮምኛ አፍ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች በሁለት ዙር የአንቀጽ ጽሁፎችና እና በሦስት አራሚዎች የመቃኘት እድል አግኝቷል፡፡

ስህተቶችን በአይነት ለመመደብ ፣ ለመቁጠርና ድግግሞሻቸውን ለማወቅ የNorrish (1993፣103-104) የስህተት አተናተን ስልት ተግባራዊ ተደረቸጓል፡፡

1. አንቀጾቹ የተጻፉበት የቃላት ብዛት እንዲደመር ተደርጓል፡፡ በእያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች ይደመራሉ፡፡

2. ስህተቶቹ አስቀድሞ በተመደበላቸው ምድብ እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ በእያንዳንዱ የስህተት አይነት የተፈጸሙ የስህተቶች ብዛት ይታወቃል፡፡

3. አንቀጾቹ የተጻፉበትን ቃላት መጠን ለአንቀጾቹ ቁጥር በማካፈል በአንድ አንቀጽ ውስጥ የሚገኘው አማካይ የቃላት ብዛት ይታወቃል፡፡

4. የስህተቶቹን መጠን ለአንቀጾቹ በማካፈል በአማካይ በአንድ አንቀጽ ውሥጥ ምን ያህል ስህተቶች እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡

5. አጠቃላይ የቃላቱን ብዛት ለአጠቃላይ የስህተት ብዛት በማካፈል አንድ ስህተት በምን ያህል ቃላት ውስጥ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

6. የስህተቶቹን መጠን በመቶ በማባዛት እና የተገኘውን ውጤት አንቀጾቹ በተጻፉበት የቃል ብዛት በማካፈል በመቶ ቃላት ምን ያህል የስህተት ድግግሞሽ እንዳለ ለማወቅ ይቻላል፡፡

### 3.4.2. የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ የተጠኚዎቹን ጉልህ የአንቀጽ ጽህፈት ችግሮች የሚመለከቱ መረጃዎች በመሰብሰብ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹን የተባባሱ የመጻፍ ችግሮች ለማቃለል የሚያስችሉ የልምምድ ማትኮሪያዎች መተንተንን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ የቀረበላቸው ለ144ቱ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ለተጠኚዎቹ የቀረበላቸው መጠይቅ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ የመጻፍ ክሂልን ለመማር በሚያጋጥሟቸው ልዩ ልዩ ችግሮች ላይ ያተኮሩ 20 የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎቹ ሙሉ በሙሉ በዝግ መጠይቅ የአቀራረብ ስልትና በሊከርት ስኬል የጥያቄዎች አቀራረብ ዘዴ በመመርኮዝ ከዝቅተኛ 1 = ‹‹ሙሉ በሙሉ አልስማማም››፣ 2 = ‹‹አልስማማም››፣ 3 = ‹‹አቋም አልያዝኩም››፣ 4 = ‹‹እስማማለሁ›› እስከ ከፍተኛ 5 = ‹‹ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ›› ባለ አምስት የመልስ አማራጮችን አካትቶ ቀርቧል፡፡

የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎችን አስተማማኝነት ለመጠበቅ ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ጥናት በስራ ላይ ውሎ መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገለ የጽሁፍ መጠይቅ ላይ መመርኮዝ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የአምላክሥራ (2008) ለአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች የተገለገለችበትን መጠይቅ አጥኚዋ ለዚህ ጥናት እንዲስማማ (adopt) አድርጋ እና የመጠይቅ ጥያቄዎችን ቁጥር መጥና በማቅረብ መረጃ ሰብስባለች፡፡

## 3.5. የመረጃ ትንተና ዘዴ

ይህ ጥናት በሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመደገፍ የቀረቡ መረጃዎችን እንደሚከተለው ተንትኗል፡፡ በቅድሚያ ስህተቶችን በአይነት ለመመደብ፣ ለመቁጠርና ድግግሞሻቸውን ለማወቅ የNorrish (1983) የስህተት አተናተን ስልት /ሞዴል/ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ከተጠኚዎቹ በፈተና የተሰበሰቡ የአንቀጽ ስህተት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የቃላት ስህተት፣ ስዋስዋዊ አግባብ ያልጠበቁ (መደብ፣ ቁጥርና ጾታ፣ መስተዋድዶች፣ ባለቤትና ተሳቢ አጠቃቀም)፣ ሆሄያትን በሌላ ሆሄ መተካት፣ የስርአተ ነጥብ ስህተት ከተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ዝርዝር መግለጫ (አስረጂዎች) ጋር በሰንጠረዥ፣ በቁጥር፣ በመቶኛ፣ በአማካይ፣ በድግግሞሽ አማካይና በትክክለኛነት ተዛማጅነት እየተሰሉ ከማብራሪያ ጋር ቀርበዋል፡፡

ቀጥሎም ከተጠኚዎቹ በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ትንተናና ማብራሪያ ቀርቦበታል፡፡ በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው የመረጃ ክፍል የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹን የተባባሱ የመጻፍ ክሂል ችግሮች ለይቶ በማወቅ ለመፍትሄ የሚሆኑ የልምምድ ማትኮሪያዎች መጠቆምን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ከዝቅተኛ 1 = ‹‹ሙሉ በሙሉ አልስማማም›› እስከ ከፍተኛ 5 = ‹‹ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ›› ባለ አምስት የመልስ አማራጮችን በSPSS version 2021 ስታቲስቲክ ማስያ ቋት ውስጥ በማስገባት ምላሾቹ በአማካይ ውጤትና በመደበኛ ልይይት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም በስህተት ትንተናው አበይት ግኝቶች ላይ በማትኮር ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

ይህ ትንተና የተመሰረተው በአንቀጽ ጽህፈት ስህተት ላይ ነው፡፡ በዚህ ምእራፍ ከተጠኚዎቹ በሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ ቀርቧል፡፡ በጥናቱ በፈቃደኝነት 145 ተማሪዎች ተሳታፊ እንደሚሆኑ ተጠብቆ ወደ አንቀጽ መጻፉ አውድ በፈቃደኛነት የመጡት ተሳታፊዎች 132 ተማሪዎች ናቸው፡፡ የተቀሩት 13 ተማሪዎች በራሳቸው ልዩ ልዩ ምክንያቶች መረጃ አልሰጡም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት 132 ተሳታፊዎች በሁለት ዙሮች 264 አንቀጾች ጽፈው የጽህፈት ስህተት ትንተናው በእነዚሁ አንቀጾች ላይ ተመርኩዟል፡፡ የአንቀጽ ጽህፈት ስህተት ትንተናው ቀደም ሲል በምዕራፍ ሦስት በቀረቡ የስህተት መለያዎች ማለትም የቃላት ስህተት፣ ሰዋስዋዊ አገባብ ያልጠበቁ (መደብ፣ ቁጥርና ጾታ፣ መስተዋድዶች፣ ባለቤትና ተሳቢ አጠቃቀም)፣ የአናባቢ ድምጽ ለውጥ ስህተት፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ከተፈፀሙ የስህተት አይነቶች አንጻር ተለይተው በስህተቶች ብዛት፣ መቶኛ ስሌት፣ አማካይ ስህተት፣ እየተሰሉ በአንቀጽ አንድ፣ በአንቀጽ ሁለትና በአንቀጽ አንድና ሁለት አጠቃላይ ድምር እየተተነተኑ ቀርበዋል፡፡ ቀጥሎም ከተጠኚዎቹ በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰበው ተጠኚዎቹ በመጻፍ ክሂል ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮችና ምክንያቶች የሰጧቸው ምላሾች መረጃዎች በመቶኛ፣ በአማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በሰንጠረዦች ከትንተናና ማብራሪያ ጋር ቀርበዋል፡፡

### 4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና

የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ ምን አይነት ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ይፈጽማሉ?›› የሚል ሲሆን፣ ለዚህ ጥያቄ በቂ ምላሽ ለማግኘት ተጠኚዎቹ በተመረጠው የአንቀጽ መጻፊያ ርእስ ሁለት ጊዜ በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የፈጸሟቸው ስህተቶች ተለይተው የተገኘው መረጃ በገላጭ ስታቲስቲክስ ከዚህ በታች ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡- በተማሪዎቹ አንቀጾች ውስጥ የተፈጸሙ ስህተቶች ስርጭት አጠቃላይ ገጽታ

| | የአንቀጽ ብዛት | የተጻፉበት ቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ አንድ | 132 | 5282 | 40.02 | 2446 | 46.31 | 18.53* |
| አንቀጽ ሁለት | 132 | 5116 | 38.76 | 2112 | 41.28 | 16.0 |
| አንቀጽ አንድና ሁለት | 264 | 10398 | 78.78 | 4558 | 43.83 | 34.53 |

*አማካይ ስህተት = አጠቃላይ የስህተት ብዛት / አጠቃላይ የአንቀጽ ብዛት

ከፍ ሲል በሰንጠረዥ 1 የቀረበው መጠናዊ መረጃ የሚያሳየው በተጠኚዎቹ አንቀጾች ውስጥ የታዩ አጠቃላይ ስህተቶች ብዛት ሲሆን፣ ተጠኚዎቹ በጻፏቸው አንቀጾች መሰረት የአንቀጽ ብዛት፣ አንቀጾቹ የተጻፉበት የቃላት ብዛት፣ አማካይ የቃላት ብዛት፣ የስህተት ብዛት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው በአንቀጽ አንድና ሁለት በተጠኚዎቹ አንቀጾች ውስጥ የቀረቡ አጠቃላይ ቃላት ብዛት 10398 ሲሆን፣ በአንቀጽ አንድ 5282 በአንቀጽ ሁለት 5116 ቃላት ተጠቅመው አንቀጾቻቸውን ጽፈዋል፡፡ በሁለቱ አንቀጾች ውስጥ ተጠኚዎቹ የተጠቀሙባቸው አማካይ የቃላት ብዛት 78.78 ሲሆን በመጀመሪያው የአንቀጽ ጽሁፎቻቸው የተጠቀሙባቸው አማካይ ቃላት 40.02፣ በሁለተኛው ዙር የአንቀጽ ጽሁፎቻቸው የተጠቀሙባቸው አማካይ ቃላት 38.76 መሆናቸው ተሰልቷል፡፡

ተጠኚዎቹ በሁለቱ አንቀጾች ውስጥ የፈጸሟቸው ስህተቶች አጠቃላይ ብዛት 4558 ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ 2446፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ 2112 የአጻጻፍ ስህተቶችን ፈጽመዋል፡፡ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ የፈጸሟቸው ስህተቶች መቶኛ ስሌት 46.31 በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ ከፈጸሟቸው የአጻጻፍ

ስህተቶች 41.28 በ5.03 መቶኛ በልጦ የሚገኝ መሆኑን የስህተት ትንተና መረጃው አመልክቷል፡፡

አጠቃላይ የስህተት ብዛት ለአጠቃላይ የተጠኚዎቹ ብዛት በማካፈልም አማካይ ስህተቶችን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሰረት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ አማካይ የስህተት መጠን 18.53፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ አማካይ የስህተቶች መጠን 16.0 ሲሆን፣ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዙር የፈጸሟቸው ስህተቶች አማካይ 17.27 መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተጠኚዎቹ በሁለቱ የአንቀጽ መጻፍ ዙሮች ከጻፏቸው 78.78 አማካይ የቃላት ብዛት በአማካይ 34.53 የተለያዩ ስህተቶችን እንደፈጸሙ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ዙር ከተጠቀሙባቸው 46.31 አማካይ የቃላት ብዛት በአማካይ 18.53፣ በሁለተኛው ዙር ከተጠቀሙባቸው 41.28 አማካይ የቃላት ብዛት በአማካይ 16.0 ልዩ ልዩ ስህተቶችን ፈጽመው መገኘታቸውን መረጃው አመላክቷል፡፡

ከፍ ሲል በቀረበው ትንተና ተጠኚዎቹ በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የፈጸሟቸውን አጠቃላይ ስህተቶች ጠቅለል ያለ ገጽታ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ቀጥሎ ለትንተና የቀረበው ተጠኚዎቹ በሁለቱ የአንቀጽ ዙሮች የፈጸሟቸው የስህተት አይነቶች ስርጭትን ነው፡፡ በአንቀጾቹ ውስጥ በብዛት የታዩት ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ስዋስዋዊ አገባብ ያልጠበቁና የስነ-ድምጽ አጻጻፍ ስህተቶች ናቸው፡፡ በዋናዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠረውን የስህተት መጠን ዝርዝር መረጃ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 2 ለማስፈር ተሞክሯል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡- በሁለቱ አንቀጾች ውስጥ የስህተት አይነት ምድቦችና የስህተት ስርጭት**

| | አንቀጽ አንድ | | አንቀጽ ሁለት | |
|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | መቶኛ | በቁጥር | መቶኛ |
| 1) ስዋስዋዊ ስህተቶች | 918 | 37.53 | 806 | 38.16 |
| 2) የስነድምጽ (ፊደላት) | 609 | 24.89 | 543 | 25.71 |
| 3) የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ስህተት | 401 | 16.39 | 361 | 17.09 |
| 4) የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተት | 321 | 13.12 | 248 | 11.74 |
| 5) የሀሳብ አንድነት | 163 | 6.66 | 132 | 6.25 |
| 6) ከ1–5 ምድቦች ውጪ | 34 | 1.9 | 22 | 1.04 |
| ጠቅላላ ድምር | 2446 | 100.00 | 2112 | 100.00 |

ከላይ በሰንጠረዥ ሁለት በቀረበው መረጃ መሰረት በሁለቱም አንቀጾች ከተመደቡት የስህተት አይነቶች ከፍተኛ ስህተት የተቆጠረው በቋንቋ አጠቃቀም /ስዋስዋዊ ስርአት ያልጠበቁ/ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ በአንቀጽ አንድ የተቆጠሩ የተለያዩ የስህተት አይነቶች አጠቃላይ ብዛት 918 (37.53%) ሲሆን በተቀራራቢ መልኩ በአንቀጽ ሁለት የተቆጠሩ ሰዋስዋዊ ስርአት ያልጠበቁ የተለያዩ ስህተቶች አጠቃላይ ብዛት 806 (38.16%) ነው፡፡ በእርግጥ ተጠኚዎቹ በዚያው በመጀመሪያው የአንቀጽ መጻፊያ ርእስ በድጋሚ በመጻፋቸው በሁለተኛው አንቀጽ መጠነኛ የስህተት ቅነሳ ያደረጉ መሆናቸው ቢስተዋልም፣ በስህተት ምድቡ የፈጸሟቸው ስዋስዋዊ ስርአት ያልጠበቁ የተለያዩ ስህተቶች ከሌሎች የስህተት ምድቦች መጠን በትይዩ ከፍ ያለ መሆኑ ታይቷል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ትምህርት ካልተማሩ ሀገር መምራት አይችልም
- ጎበዝ ተማሪ በጠዋት ተነስተው…ትምህርቱን ተከታትለው
- በተለይ ሴት ልጅ ካልተማረች ኑሮ ይከብዶዋል
- አነሱም ለትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት አሏት
- ካልተማረች ንብረቱን እንኳን መቆጣጠር አይችልም

እና የመሳሰሉ ጉልህ የሰዋስው አገባብ ስህተቶች ተፈጽመዋል፡፡

ሌላው ተጠኚዎቹ ክብደት የተሰጠው ስህተት ፈጽመው የተገኙት በስነ-ድምጽ አጻጻፍ የአናባቢና ተነባቢ ድምጾች ቅየራ ስህተት ነው፡፡ በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ ቃላቱ የተገነቡባቸውን ድምጾች የሚወክሉ ፊደላትን አስተካክሎ ካለመጻፍ የተነሳ ስዋስዋዊ አገባብ ካልጠበቁ ስህተቶች ቀጥሎ በርካታ ስህተቶች የፈጸሙ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡ የሆሄያትን ቅርጽ በትክክል በተገቢ ቦታቸው ባለመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች በአንቀጽ አንድ 609 (24.89%) ሲሆን በተመሳሳይ በአንቀጽ ሁለት 543 (25.71%) ያህሉን ስህተቶች የሸፈነው የስነ-ድምጽ አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ትምህርት በሽታ ከሰው ወደ ሰው እንደምያልፍ ያስተምርናል
- ትምህርት የተሸለ እውቀት ለማገኘት ይጠቅማል

- ከአስተማር ጋር አለመጣላት
- የክፍል ስራ ሰርቶ ማሳርም
- ዛፍ የዱር አራዊቶች መጠልያ ነው
- ሰው ከልተማረነ ከለወቀ
- ትምህርት ሜማር አለብን
- የሰው ልጅ ተሚሮ

ተማሪዎቹ ከፈፀሟቸው የድምጽ ለውጥ ስህተቶች እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

| **የድምጽ ለውጥ የታየባቸው ቃላት** | **በትክክል ሲጻፍ** |
|---|---|
| እንደምያልፍ | እንደሚያልፍ |
| ያስተምርናል | ያስተምረናል |
| የተሸለ | የተሻለ |
| ለማገኘት | ለማግኘት |
| አታደርግ | አታድርግ |
| መጠልያ | መጠለያ |
| ከልተማረ | ካልተማረ |
| ሜማር | መማር |
| ተሚሮ | ተምሮ |

በእርማት ከተለዩት የተማሪዎቹ የተነባቢ ድምጽ ለውጥ ስህተቶች መካከል የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

| **ተማሪዎች የጻፉት** | **ትክክለኛው አገላለጽ** |
|---|---|
| -ጊዜወን በአጊባቡ ሂጠቀማል | -ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል |
| -ተንክሮ መማር ያስፈልጋል | -ጠንክሮ መማር ያስፈልጋል |

| | |
|---|---|
| -በአማርኛ መጻፍ ህከብደኛል | -በአማርኛ መጻፍ ይከብደኛል |
| -ዛፍ ለእንስሳትም ይጠክማል | -ዛፍ ለእንስሳትም ይጠቅማል |
| -ንፅህናን መተበቅ | -ንፅህናን መጠበቅ |
| -ፈተናም እሰራለው | -ፈተናም እሰራለሁ |
| -ዛፍ የአየር ለውጥ ያመታል | -ዛፍ የአየር ለውጥ ያመጣል |
| -እይቶቻችንና ወንድሞቻችን | -እህቶቻችንና ወንድሞቻችን |

ከተጠኚዎቹ የአንቀጽ ጽህፈት ስህተት ከቋንቋ አጠቃቀም እና የስነድምጽ አጠቃቀም ቀጥሎ ከፍተኛ የስህተት መጠን የተገኘበት ምድብ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 401 (16.39%)፣ እንዲሁም በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 361 (17.09%) ያህሉን ስህተቶች የሸፈነው የቃላትና የሀሳብ ስህተት መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡
በሌላ በኩል ከቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የጉልህነት ደረጃ የያዘ ስህተት ነው፡፡ በሁለቱ ዙር ከተጻፉት አንቀጾች ውስጥ የተገኘው ስህተት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 321 (13.12%)፣ እንዲሁም በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 248 (11.74%) ያህሉን ስህተቶች የሸፈነው የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

የሀሳብ አንድነት የሌላቸው ቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተነገሮችን በመጠቀም ረገድ የታዩ የተለያዩ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 163 (6.66%)፣ እንዲሁም በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 132 (6.25%) መሆናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡ የሀሳብ አንድነት የሌላቸው ስህተቶች ድግግሞሹ በመጀመሪያው ዙር በጻፉት አንቀጽ በአማካይ በየ10.04፣ እንዲሁም በሁለተኛው ዙር በጻፉት አንቀጽ በአማካይ በየ9.97 ቃላት መካከል አንድ የሀሳብ አንድነት የሌላቸው አረፍተነገሮች እንደሚገኙ ለመገመት የሚያስችል ይሆናል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተጠኚዎቹ ከሚፈጽሟቸው የአንቀጽ ስህተቶች መካከል የመጨረሻውን ደረጃ የያዘው የሀሳብ አንድነት የሌላቸው የተለያዩ ስህተቶች ላይ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ትኩረት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱት የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ ምን አይነት ስህተቶችን በድግግሞሽ እንደሚፈጽሙ በዝርዝር ማጤን ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጥሎ ጥናቱ የቃኘው በዋናዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ ተጠኚዎቹ ምን አይነት ዝርዝር ስህተቶችን በድግግሞሽ እንደፈጸሙ የቀረበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ትንተና ማቅረብ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከላይ በሰንጠረዥ 2 በቀረቡት ዋና ዋና ስህተቶች ማለትም በቋንቋ አጠቃቀም /ስዋስዋዊ ስርአት ያልጠበቁ/፣ በስነድምጽ (ፊደላት አጻጻፍ፣ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም፣ እንዲሁም የሀሳብ አንድነት የሌላቸው የተለያዩ ስህተቶች ገጽታ ምን እንደሚመስል ጥናቱ ፈትሿል፡፡ በዚሁ መሰረት በሰንጠረዥ 3 ስዋስዋዊ አገባብ ያልጠበቁ የአንቀጽ ስህተቶች ትንተና ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡- ስዋስዋዊ አገባብ ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች**

| ስዋስዋዊ አገባብ ያልጠበቁ ስህተቶች ምድብ | አንቀጽ አንድ | | | አንቀጽ ሁለት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት |
| ባለቤትና ተሳቢ | 266 | 28.98 | 2.02 | 253 | 31.39 | 1.92 |
| መደብ | 257 | 27.99 | 1.95 | 232 | 28.78 | 1.76 |
| ቁጥርና ጾታ | 239 | 26.03 | 1.81 | 184 | 22.83 | 1.41 |
| መስተዋድዶች | 156 | 16.99 | 1.18 | 137 | 16.99 | 1.04 |
| ድምር | 918 | 100 | | 806 | 100 | |

ከላይ በሰንጠረዥ 3 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ተጠኚዎቹ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ የፈጸሙት ስዋስዋዊ አገባብ ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች አጠቃላይ ብዛት 918 ሲሆን በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ የፈጸሙት ስዋስዋዊ አገባብ ባለመጠበቅ የተፈጸሙ የባለቤትና ተሳቢ ስህተቶች አጠቃላይ ብዛት 806፣ በሁለቱ ዙሮች በአጠቃላይ ስዋስዋዊ አገባብ ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች 1724 መሆናቸው ታውቋል፡፡ ተጠኚዎቹ በሁለቱም ዙሮች አንቀጽ ሲጽፉ የፈጸሟቸው ስዋስዋዊ አገባብ ካለመጠበቅ ጋር ከተያያዙ ስህተቶች መካከል በላጩን ድርሻ በመያዝ ጉልህ ሆነው የተመዘገቡት የባለቤትና ተሳቢ አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው፡፡ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ ከፈጸሟቸው የስዋስዋዊ አገባብ ስህተቶች መካከል 266 (28.98%) እንዲሁም በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ ከፈጸሟቸው የስዋስዋዊ

አገባብ ስህተቶች መካከል 253 (31.39%) የስህተት ድርሻ የተመዘገበው በባለቤትና ተሳቢ አጠቃቀም ነው፡፡ በባለቤትና ተሳቢ አጠቃቀም ተጠኚዎቹ የፈጸሟቸው አማካይ ስዋስዋዊ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 2.02 ሲሆን በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 1.92 ሆኖ ተሰልቷል፡፡

ከባለቤትና ተሳቢ ስህተቶች ለምሳሌ፡- **የተማሪዎቹ ስህተቶች**

- መማር የሰው ልጆች የተለያዩ ታላላቅ ቦታዎች ላይ በመድረስ ደረጃ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ትልቅ የህይወት መንገድ ነው፡፡
- ትምህርት ቤቱ የእድገት መሰላል የሆነችው ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለብዙሆች ሆና የተረፈችም ናት፡፡ ትምህርት ቤቱ ባትኖር ሰዎችም ሆኑ እኔ የት ልምር ነበር ትምህርት ቤቱ የእውቀት መሸመቻችን የእድገት መሰላሊም ናት

- ጥቅሙ ለማያውቁ (ጥቅሙን ለማያውቁ)

- ካልተማረ ቤተሰቡ እንኳን አይመራም (ካልተማረ ቤተሰቡን እንኳን አይመራም)

ተማሪዎቹ ከፈጸሟቸው ስህተቶች ምሳሌ ወስደን እንዳየነው ቤተሰቡ፣ አዕምሮው፣ ጥቅሙ… የሚሉት ቃላት ላይ ተሳቢ "ን" ባላመግባቷ ስህተት ተፈጥሯል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገር፣ ሰዎቹ፣ ነዷ ጊቤ… የሚሉት ቃላት ላይ ተሳቢ "ን" መግባት ሳይጠበቅባት በመግባቷ ስህተት ተፈጽሟል፡፡ ተማሪዎቹ በንግግር የለመዱትን ወደ ጽህፈት ሲለዉጡ እንዳለ ስለሚጽፉ የተፈጠረ ስህተት ሊሆን ይችላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የስዋስዋዊ አገባብ ስህተት የተመዘገበው በመደብ አገላለጽ ነው፡፡ በመደብ አገላለጽ ተጠኚዎቹ በመጀመሪያ ዙር አንቀጽ የፈጸሟቸው ስህተቶች አጠቃላይ ብዛት 257 (27.99%) ሲሆን፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ የፈጸሟቸው የመደብ ስህተቶች አጠቃላይ ብዛት 232 (28.78%)፣ በአጠቃላይ ስዋስዋዊ አገባብ ባለመጠበቅ የተፈጸሙ የመደብ ስህተቶች 489 መሆናቸው ታውቋል፡፡ በመደብ አገላለጽ ተጠኚዎቹ የፈጸሟቸው አማካይ ስዋስዋዊ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 1.95 ሲሆን በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 1.76 ሆኖ ተሰልቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው እያንዳንዱ ተማሪ ከጠቅላላው የምድቡ ስህተት ያበረከተውን ግለሰባዊ የስህተት ድርሻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- **የተማሪዎች አጻጻፍ**

- ቤተሰብ ማለት አባት፣ እናት፣ ልጆችና … ሲሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡

ቤተሰብ ልጆችንና በቤተሰብ የሚገኙትን ማንኛውንም የቤተሰብ አባል ይመግባል፤ ያለብሳል፤ በበሽታ የተያዙትን ያሳክማል፤ የተጎዱትን ይንከባከባል፡፡ በአግባቡ በተገቢው መንገድ ማሳደግ ነው፡፡

- ላም ከቤት እንሰሳ ውስጥ አንዱ ስትሆን ጥቅሙ ብዙ ነው የነሱም ጥቅም ለማግኘት እነሱ መንኬባኬብን አለብን፡፡
- ላም ከቤት እንሰሳ አንዱ ናት፡፡ የላም ተመራጭ ምግብ ሳር ሲሆን ወተት ትሰጣለች፡፡
- በተለይ ሴት ልጅ ካልተማረች ኑሮ ይከብዶዋል
- አነሱም ለትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት አሏት
- ካልተማረች ንብረቱን እንኳን መቆጣጠር አይችልም
- ትምህርት ቤቴ ለኔ ብዙ ጥቅም ነት የሚሉና የመሳሰሉ ስህተቶች ታይተዋል፡፡ ከሰዋስዋዊ አገባብ ስህተቶች መካከል ሦስተኛው የስህተት መጠን የተመዘገበው የቁጥርና ጾታ አገላለጽ ስህተት ነው፡፡ በዚህ ስህተት አይነት የተቆጠሩ ስህተቶች አጠቃላይ የቁጥርና የጾታ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር 239 (26.03%)፣ በሁለተኛው ዙር 184 (22.83%) በአጠቃላይ በሁለቱ የአንቀጽ መጻፍ ዙሮች የተፈጸሙ 423 የቁጥርና ጾታ አለመስማማት ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ በቁጥርና ጾታ አለመስማማት ተጠኚዎቹ የፈጸሟቸው አማካይ ስዋስዋዊ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 1.81 ሲሆን በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 1.41 መሆኑ ተሰልቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው እያንዳንዱ ተማሪ ከጠቅላላው የምድቡ ስህተት ያበረከተውን ግለሰባዊ የስህተት ድርሻ ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፡- **የተማሪዎች አጻጻፍ**

- ላም ቢዙ ጥቅም አላቻሁ (ላሞች ብዙ ጥቅም አላቸው)
- ዛፎች የተለያዩ አገልግሎት ላይ ሊውል ይችላል (ዛፎች ለተለያዩ አገልግሎቶች ላይ ሊውሉ ይችላሉ)
- ትምህርት ካልተማሩ ሀገር መምራት አይችልም (ትምህርት ካልተማሩ ሀገር መምራት አይችሉም)

- ጎበዝ ተማሪ በጠዋት ተነስተው…ትምህርቱን ተከታትለው (ጎበዝ ተማሪ በጠዋት ተነስቶ ትምህርቱን ተከታትሎ…)
- ወደ ቤት ሲገባም ምሳውን በልተው… (ወደ ቤት ሲገባም ምሳውን በልቶ…)
- ዛፎች የተለያዩ አገላግሎት አለ (ዛፎች የተለያዩ አገልግሎቶች አሏቸው)
- ዛፎች ከሌለ እንስሳት ሊኖር አይችልም (ዛፎች ከሌሉ እንስሳት ሊኖሩ አይችሉም)

*(በቅንፍ የተጻፉት ትክክለኛ አገላለጾች ናቸው፡፡)

ከትንታኔው መረዳት እንደምንችለው በባለቤትነት የሚያገለግለው ነጠላ ቁጥር በብዙ ቁጥር ሲፈፀምና በብዙ ቁጥር ተጀምሮ በነጠላ ቁጥር ሲያልቅ ተስተውሏል፡፡

በሰዋስዋዊ አገባብ የስህተት ምድብ ከተፈጸሙ ስህተቶች አንጻራዊ ዝቅተኛ ስህተት የተፈጸመው በመስተዋድዶች አለመስማማት ሲሆን፣ በአጠቃላይ ከፈጸሙት 293 ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 156 (16.99%) በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 137 (16.99%) የመስተዋድዶች አለመስማማት ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ በመስተዋድዶች አለመስማማት ተጠኚዎቹ የፈጸሟቸው አማካይ ስዋስዋዊ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽሰ 1.18 ሲሆን በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 1.04 መሆኑ ተሰልቷል፡፡ ከነዚህ ስህተቶችም የተወሰኑትን እንደሚከተለው በምሳሌነት እንመልከት፡፡

**የተማሪዎች አጻጻፍ**

- የላም ከቤት እንስሳ አንዱአ ናት (ላም ከቤት እንስሳት አንዷ ናት)
- የትምህርት ጥቅሞች ጥቂቶቹ (ከትምህርት ጥቅሞች ጥቂቶቹ)
- ለትምህርቱ ሚያስፈልጉ ነገሮች (ለትምህርቱ የሚያስፈልጉ ነገሮች)
- ትምህርትን አግባቡ መማር አለብን (ትምህርትን በአግባቡ መማር አለብን)
- አባቴ የስራ ምክንያት ወደ ሶኮሩ ሄደ (አባቴ በስራ ምክንያት ወደ ሶኮሩ ሄደ)
- ማንነታችንን ምናውቀው (ማንነታችንን የምናውቀው)
- ትምህርት ጥቅም ብዙ ነው (የትምህርት ጥቅም ብዙ ነው)
- ለሰው ላይ ትምህርት ሲያገኝ (ከሰው ላይ ትምህርት ሲያገኝ)
- ከብቶች ሚበሉት እንዳያጡ (ከብቶች የሚበሉት እንዳያጡ)

*(በቅንፍ የተጻፉት ትክክለኛ አገላለጾች ናቸው፡፡)

ከዚህ ትንታኔ መረዳት እንደሚቻለው ተተኳሪ ተማሪዎቹ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚገቡትን የመስተዋድድ ምዕላዶችን በስህተት ተጠቅመዋል፡፡ የተፈጠሩ ስህተቶችም መስተዋድድ መግባት ያለበት ቦታ ባለማስገባታቸው እና መግባት በሌለበት ቦታ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ስህተታቸው በውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት ሊፈጠር እንደሚችል ይገመታል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ የፈጸሟቸው ስህተቶች ትክክለኛ መስተዋድድ መግባት ባለበት ቦታ ባለማስገባታቸውና መግባት በሌለበት ቦታ በማስገባታቸው ስለሆነ የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት በትክክል አለመረዳት እንደተከሰተ ተስተውሏል፡፡

ጥናቱ ቀጥሎ የፈተሸው በስነድምጽ (ፊደላት) አጻጻፍ የስህተት ምድብ ተጠኚዎቹ የፈጸሟቸውን አጠቃላይ ስህተቶች ነው፡፡ በፊደላት አጻጻፍ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ የፈጸሙት ስህተት 809 ስህተት ሲሆን በሁለተኛው ዙር ደግሞ 782 በድምሩ 1591 የፊደላት አጻጻፍ ስህተቶችን መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ሰንጠረዥ 4 የፊደላት አጻጻፍ የስህተት አይነቶችን በመለየት አቅርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- የስነድምጽ (ሆሄያት) አጻጻፍን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች**

| የስነድምጽ /ሆሄያት/ ስህተት ምድብ | አንቀጽ አንድ | | | አንቀጽ ሁለት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት |
| ሆሄያትን በሌላ ሆሄ መተካት | 209 | 34.31 | 1.58 | 168 | 30.94 | 1.27 |
| የሆሄያት ቅነሳ | 164 | 26.93 | 1.24 | 152 | 27.99 | 1.15 |
| የሆሄያት ጭመራ | 123 | 20.19 | 0.93 | 119 | 21.92 | 0.90 |
| የሆሄያት ቦታ ቅየራ | 113 | 18.56 | 0.86 | 104 | 19.15 | 0.79 |
| ድምር | 609 | 100 | | 543 | 100 | |

በፊደላት አጻጻፍ የተፈጸሙ ስህተቶች ከአጠቃላዩ የአንቀጽ ስህተት ሁለተኛውን የስህተት ደረጃ የያዙ ናቸው፡፡ ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ የታዩ የፊደላት አጻጻፍ ስህተቶች ብዛት 609 ሲሆን በሁለተኛው ዙር

ድርሰት መጻፍ የታዩ የፊደላት አጻጻፍ ስህተቶች ብዛት 543 በአጠቃላይ የፊደላት /ሆሄያት/ ስህተቶች 1152 መሆናቸው አስቀድሞ ተገልጿል፡፡

በዝርዝር ሲታይ በተጠኚዎቹ አንቀጾች ውስጥ የፊደላት አጻጻፍን በሚመለከት ከተፈጸሙ ስህተቶች መካከል በላጬን እጅ የያዙ ስህተቶች የተፈጸሙተ ሆሄያትን በሌላ ሆሄ በመተካት ነው፡፡ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ ሆሄያትን በሌላ ሆሄ በመተካት የፈጸሟቸው ስህተቶች 209 (34.31%) በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ሲጽፉ ሆሄያትን በሌላ ሆሄ በመተካት የፈጸሟቸው ስህተቶች 168 (30.94%) ትይዩ በሆነ መንገድ ከሌሎች የዚህ ምድብ ስህተቶች በላጭ የስህተት ድርሻ አላቸው፡፡ የፊደላት /ሆሄያት/ አጻጻፍ በእያንዳንዱ ተጠኚ በመጀመሪያውና ሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ በአማካይ 1.58 እና 1.27 መሆኑ ተሰልቷል፡፡ ይህም የሚያመለክተው እያንዳንዱ ተጠኚ የፊደላት /ሆሄያት/ አጻጻፍ የስህተት ድግግሞሽ በመጀመሪያውና ሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ ያበረከተውን ሆሄያትን በሌላ ሆሄ የመተካት የስህተት ድርሻ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- **የተማሪዎቹ ስህተት**

- የሰው ልጅ ከተማሬ ከራሱ አልፌ… ግን ካልተማሬ… (የሰው ልጅ ከተማረ ከራሱ አልፎ … ግን ካልተማረ…)
- ዛፍ መትከል ለሰው ልጀ አስፈለጉ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው (ዛፍ መትከል ለሰው ልጅ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው)
- ዛፍ ለእንስሳትም ይጠክማል (ዛፍ ለእንስሳትም ይጠቅማል)
- ንፅህናን መተበቅ (ንፅህናን መጠበቅ)
- ፈተናም እሰራለው (ፈተናም እሰራለሁ)
- ዛፍ የአየር ለውጥ ያመታል (ዛፍ የአየር ለውጥ ያመጣል)
- እይቶቻችንና ወንድሞቸችን (እህቶቻችንና ወንድሞቻችን)
- ለሀገርም ለራሳቸሁም (ለሀገርም ለራሳቸውም)
- ሳልፈተን ቀራው (ሳልፈተን ቀረሁ)
- የትምህርት መረጃ መያኀ (የትምህርት መረጃ መያዝ)
- ማዕበረሰብ ካልተማረ (ማህበረሰብ ካልተማረ)
- ያልተማረ እዝብ በመኖሩ (ያልተማረ ህዝብ በመኖሩ)
- እኔ ትምህርት ቤት ይወዳሎ (እኔ ትምህርት ቤት እወዳለሁ)
- አንድ ሰው አብት አለኝ ሚለው (አንድ ሰው ሀብት አለኝ የሚለው)
- ኑሮ እከብዳል (ኑሮ ይከብዳል)
- የተሻለ ኑሮ እኖራል (የተሻለ ኑሮ ይኖራል)

- ተምሮ ሊለወጥ እችላል (ተምሮ ሊለወጥ ይችላል)
- ሀገር ህንለውጣለን (ሀገር እንለውጣለን)
- ራሳችን ማሳደግ ህንችላለን (ራሳችንን ማሳደግ እንችላለን)

*(በቅንፍ የተጻፉት ትክክለኛ አገላለጾች ናቸው፡፡)

ከዚህ ትንታኔ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ የፈፀሟቸው የተነባቢ ድምጽ ለውጥ ስህተት በቃላት መጀመሪያ፣ በቃላት መሃከልና በመጨረሻ ላይም ታይቷል፡፡ እነዚህ ሰዋስዋዊ ስህተቶችም ተተኳሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ሆሄያት ቅርፅ በደንብ ለይተው ካለመገንዘብ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

በፊደላት አጻጻፍ የስህተቶች ምድብ ተጠኚዎቹ የፈጸሙት ሁለተኛው የስህተት አይነት የሆሄያት ቅነሳ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ ውስጥ 164 (26.93%) በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 152 (27.99%) የሆሄያት ቅነሳ ስህተት ፈጽመው መገኘታቸውን መረጃው አመላክቷል፡፡ አማካይ የሆሄያት ቅነሳ ስህተት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 1.24፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 1.15 ሲሆን ይህም በእያንዳንዱ ተጠኚ አንቀጽ ውስጥ የተፈጸሙ የፊደላት ቅነሳ ስህተቶች ድርሻን የሚያመለክት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- **የተማሪዎቹ ስህተቶች እና ትክክለኞቹ አገላለጾች**

- የሰው ልጅ ያለ ትምርት ምንም ነገር ማሬግ አይችልም (የሰው ልጅ ያለ ትምህርት ምንም ነገር ማድረግ አይችልም
- ዛፍ ንፁ አየር ያመጣል (ዛፍ ንፁህ አየር ያመጣል)
- ትምርት አስፈላጊ ነው (ትምህርት አስፈላጊ ነው)
- እኔ የተወለድኩ በ1997 ዓ.ም-- (እኔ የተወለድኩት በ1997 ዓ.ም--)
- በህወት ለመቆየት (በህይወት ለመቆየት)
- ስለዚ ትምርት ይጠቅማል (ስለዚህ ትምህርት ይጠቅማል)
- ንፅናን መተበቅ (ንፅህናን መጠበቅ)
- ከዛ ደሞ (ከዚያ ደግሞ)
- በትምህርቴ ብዙም አደለሁም (በትምህርቴ ብዙም አይደለሁም)
- አንድ ሰው መጥፎ ባህር ካለው (አንድ ሰው መጥፎ ባህርይ ካለው)
- የባርዛፍ ጥቅም (የባህርዛፍ ጥቅም)

ሶስተኛው የፊደላት አጻጻፍ የስህተት አይነት የሆሄያት ጭመራ ሲሆን ይህ የስህተት አይነት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ ውስጥ 123 (20.19%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ውስጥ 119 (21.92%) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእያንዳንዱ ተጠኚ የተፈጸመው የፊደል ጭመራ ስህተት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 0.93፣ በሁለተኛው ዙር የተፈጸመው የፊደላት ጭመራ ስህተት 0.90 ነው፡፡ ይህም እያንዳንዱ ተጠኚ በቃላት ጭመራ በተፈጸመ የአጻጻፍ ስህተት በመጀመሪያውና በሁለተኛው አንቀጾች ውስጥ ያበረከተውን የስህተት ድርሻ ይጠቁማል፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን አስረጂ እንመልከት፡፡

ለምሳሌ፡- **የተማሪዎቹ ስህተቶች  እና ትክክለኞቹ አገላለጾች**

- እኛ ተምህረን (እኛ ተምረን)
- ዛፍ የአፈር የመሸርሸር ይከለክላል (ዛፍ የአፈር መሸርሸር ይከላከላል)
- የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያለንው (የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያለን)
- በልጅኝነት ጊዜ (በልጅነት ጊዜ)
- ብዙ ጥቅም አለውህ (ብዙ ጥቅም አለው)
- በባህይላችን መሠረት (በባህላችን መሠረት)
- ከመጥይፎ ነገር (ከመጥፎ ነገር)
- በውስጡው የያዘው (በውስጡ የያዘው)

*(በቅንፍ የተጻፉት ትክክለኛ አገላለጾች ናቸው፡፡)

ከምሳሌዎቹ መመልከት እንደሚቻለው በቃላት መጀመሪያ፣ ቃላት መካከልና በመጨረሻ ላይ የተጨመሩ አላስፈላጊ ሆሄያት መተላለፍ የነረበት መልዕክት እንዳይተላለፍ እንቅፋት ሆነዋል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በለመዱት መሠረት በታላሚው ቋንቋም ሲጽፉ የተፈጠረ ስህተት ስለሆነ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት ሊፈጸም ይችላል፡፡

ሌላው በፊደላት አጻጻፍ የስህተት ምድብ የታየው የስህተት አይነት ተገቢ ያልሆኑ የፊደላት /ሆሄያት/ ቦታ ቅየራ ስህተት ነው፡፡ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ የፊደላት የቦታ ቅየራ ስህተት 113 (18.56%) በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ተገቢ ያልሆኑ የፊደላት የቦታ ቅየራ  ስህተት 104 (19.5%) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በቦታ ቅየራ ስህተት ረገድ እያንዳንዱ ተጠኚ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.86 እና በሁለተኛው ዙር

አንቀጽ በአማካይ 0.79 ስህተቶችን ፈጽሞ እንደተገኘ መረጃው ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን አስረጂ እንመልከት፡፡

- ዛፍ ይህወት ላላቸው ነገሮች (ዛፍ ህይወት ላላቸው ነገሮች)
- ማቆያ የእዋልኩ ነበር (ማቆያ እየዋልኩ ነበር)
- ያልተማረ ህብዝ (ያልተማረ ህዝብ)
- ትህምርት የሌለው (ትምህርት የሌለው)
- መህምራችን (መምህራችን)

*(በቅንፍ የተጻፉት ትክክለኛ አገላለጾች ናቸው፡፡)

በጥናቱ ቀጥሎ የተቃኘው የስህተት ምድብ የቃላትና የሀሳብ ምርጫና አጠቃቀም ስህተቶችን ስርጭት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ተጠኚዎቹ በቃላትና ሀሳብ ምርጫና አጠቃቀም የፈጸሟቸው ስህተቶች ልኬት በሰንጠረዥ 5 ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### ሰንጠረዥ 5፡- በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የተፈጸሙ ስህተቶች

| የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ስህተቶች ምድብ | አንቀጽ አንድ | | | አንቀጽ ሁለት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት |
| የቃላት ምርጫ | 123 | 30.67 | 0.93 | 112 | 31.02 | 0.85 |
| የቃላት ድግግሞሽ | 116 | 28.93 | 0.88 | 105 | 29.09 | 0.79 |
| ቃላትን መተው | 88 | 21.95 | 0.67 | 74 | 20.49 | 0.56 |
| ቃላትን ያለቦታቸው ማስገባት | 74 | 18.45 | 0.56 | 70 | 19.39 | 0.53 |
| ድምር | 401 | 100 | | 361 | 100 | |

ከፍ ሲል የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ከጠቅላላው የአንቀጽ ስህተት ተጠኚዎቹ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 401፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 361 ሲሆኑ በአጠቃላይ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የፈጸሟቸው ስህተቶች 762 ናቸው፡፡

በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ተጠኚዎቹ የፈጸሟቸው ስህተተቶች በቀረቡት የስህተት ተላውጦዎች አንጻር በዝርዝር ሲጤኑ፣ ከፍተኛ ስህተት ፈጽመው የተገኙት በቃላት ምርጫ ነው፡፡ በዚህ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ተላውጠ የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 123 (30.67%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 112 (31.02%) መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡ ተጠኚዎቹ በቃላት ምርጫ

በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.93 ስህተት የፈጸሙ ሲሆን በቃላት ምርጫ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.85 ስህተት መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም እያንዳንዱ ተጠኚ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ በቃላት ምርጫ የፈጸመውን ስህተት አማካይ ስሌት ያሳያል፡፡

ለምሳሌ፡- የሚከተሉትን አስረጂዎች መመልከት ይቻላል፡-

- ላም ቢዙ ጥቅም አላቻሁ--ለኢጠናም የኢጠናኪቺ (?) ሳይሀና የጥቅም ለወተት ኢጠናሀ (?) ሊትድግ ይግለግላል፡፡ ቲሊቅ ሰውቻሀም ኢደዚሁም አናሱም ቅቤሁን ይቅበሉ፡፡
- ዛፍ መትከል ለብዙ ይገግለናል ከሁሉም በላይ ንጹ አየር ለማግኘት፣ የአፈርን ግጥበት ለመከላከል፣ ለመኖርያ ቤት መስሪያ እናለቤት ውስጥ፣ መገላገያ ቁሳቁስ ወዘተ ለጥቅምን ይችላል፡፡
- አፈርም ታጥቦ በጎርፍ እንዳይሄድ መከላከል ማለት ነው፡፡
- አብሮኝ የለቀቁ ተወዳጅ እና አንድ አዲስ ጓደኞች አሉኝ፡፡

ቀጥሎ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ተጠኚዎቹ ከፍተኛ ስህተት ፈጽመው የተገኙት በቃላት ድግግሞሽ ነው፡፡ በዚህ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ተላውጦ የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 116 (28.93%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 105 (29.09%) መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡ ተጠኚዎቹ በቃላት ድግግሞሽ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.88 ስህተት የፈጸሙ ሲሆን በቃላት ድግግሞሽ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.79 ስህተቶች መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም እያንዳንዱ ተጠኚ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዙር መጻፍ በቃላት ምርጫ የፈጸመውን ስህተት አማካይ ስሌት ያሳያል፡፡

ለምሳሌ፡- **ተማሪዎቹ የጻፏቸው**

- ከላም ብዙና ብዙ ጥቅም ይገኛል፡፡ (ከላም ብዙ ጥቅም ይገኛል፡፡)
- የተማረ ሰው የሌሎቹን መብት አክብሮ ያከብራል (የተማረ ሰው የሌሎችን መብት ያከብራል)
- ጠቀመታ ላይ መጠቀም አለበት (ጠቀሜታ ላይ መዋል አለበት)
- በስራ ጊዜ ስራ ስንሰራ በደብ መስራት አለበት (ስራ ስንሰራ በደንብ መስራት አለብን /ወይም/ ስራ በሚገባ መሰራት አለበት)

*(በቅንፍ የተጻፉት ትክክለኛ አገላለጾች ናቸው፡፡)

በሶስተኛ ደረጃ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ተጠኚዎቹ ስህተት ፈጽመው የተገኙት በአንቀጹ ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ቃላት በመተው ነው፡፡ በዚህ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 88 (21.95%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 74 (20.49%) መሆናቸውን መረጃው ይጠቁማል፡፡ ተጠኚዎቹ ተገቢ ቃላትን በመተው በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.67 ስህተት የፈጸሙ ሲሆን ተገቢ በሶስተኛ ደረጃ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ተጠኚዎቹ ስህተት ፈጽመው የተገኙት በአንቀጹ ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ቃላት በመተው ነው፡፡ በዚህ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 88 (21.95%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 74 (20.49%) መሆናቸውን መረጃው ይጠቁማል፡፡ ተጠኚዎቹ ተገቢ ቃላትን በመተው በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.67 ስህተት የፈጸሙ ሲሆን ተገቢ ቃላትን በመተው በሁለተኛው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.56 ስህተቶች መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም እያንዳንዱ ተጠኚ ለስህተት ምድቡ ያለውን ድርሻ አመላካች ነው፡፡

ለምሳሌ፡- **የተማሪዎቹ ስህተቶች እና ትክክለኞቹ አገላለጾች**

- ትምህርት ቤቴ ለኔ ብዙ ጥቅም ነት፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቴ የውቀት ምንጭ ናት ሌላ ደግሞ ትምህርት ቤት ለኔ ብዙ ታሪኬ ናት፡፡ (ትምህርት ቤቴ ለኔ ብዙ ጥቅም አላት፡፡ ~~ስለዚህ~~ ትምህርት ቤቴ የውቀት ምንጭ ናት፡፡ ~~ሌላ ደግሞ~~ በሌላም በኩል ትምህርት ቤት ለኔ ~~ብዙ~~ የታሪኬ መነሻ ናት፡፡)
- ዛፎች ከሌለ እንስሳት አይችልም (ዛፎች ከሌሉ እንስሳት መኖር አይችሉም፡፡)
- ትምርት ሰው ይለውጣል አይጎዳም (ትምህርት ሰው ይለውጣል እንጅ አይጎዳም

*(በቅንፍ የተጻፉት ትክክለኛ አገላለጾች ናቸው፡፡)

በአራተኛ ደረጃ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ተጠኚዎቹ ስህተት ፈጽመው የተገኙት በአንቀጹ ውስጥ ቃላትን ያለቦታቸው በማስገባት ነው፡፡ በዚህ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ተላውጦ የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 74 (18.45%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 70 (19.39%) መሆኑን መረጃው ይጠቁማል፡፡ ተጠኚዎቹ ቃላትን ያለቦታቸው በማስገባት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.56 ስህተት የፈጸሙ ሲሆን ቃላትን ያለቦታቸው በማስገባት በሁለተኛው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.53 ስህተቶች መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም እያንዳንዱ ተጠኚ

ለስህተት ተላውጠው ያለውን ድርሻ የጉልህነቱ ደረጃ አንጻራዊ ዝቅተኛነት አመላካች ነው፡፡

**ምሳሌ፡- ተማሪዎች የፈፀሟቸው ስህተቶች**

- ከዚ ከተማ ለቀን ዲምቱ ስንመጣ (ከዚያ ከተማ ለቀን ዲምቱ ስንመጣ)
- በዚህ ግዜ የአሰምስተኛ ክፍል ተማሪ ነቡረኩ (በዚያ ጊዜ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ)
- ዛፎች ለሰው ልጅ ጠቃመ ናት/ዘፍ ለሰው ልጆች ጠቃሚ ነው፡፡/
- የሰው ልጅ በሙሉ ቤተሰብ አሎ፡፡ ቤተሰብ ማለት እናቱ አባቱ እህቲ ዋዲም ወዘተ ማለት እቺላለን፡፡ እጊዲ የኡቀት መጀመራ ቤተሰብ ናው፡፡

ከዚህ አስረጂ ማየት እንደሚቻለው በያንዳንዱ ዓረፍተ-ነገሮች መነሻ ላይ ሩቅ አመልካች ቃላት መጠቀም ሲገባቸው  በዚህ፣ ከዚህ እና ይቺ የሚሉ ቅርብ አመልካች ቃላት በመጠቀም ስለጻፉ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የጠቋሚ አመልካች ስህተት ተፈጥሯል፡፡ በሌላም በኩል በትክክል ያልተዋቀሩ ቃላትና አረፍተነገሮችን ለማያያዝ አላግባብ የገባ እጊዲ (እንግዲህ ለማለት) ቃል ይገኛል፡፡ በተማሪዎቹ የአንቀጽ ጽሁፎች ውስጥ እንዲህ ያሉ ስህተቶች እጅግ በርካታ ናቸው፡፡

በቅደም ተከተል በዋና ዋና የስህተት ተላውጠዎቹ በተመዘገበው የአንቀጽ ስህተት ስታቲስቲካዊ ውጤት መሰረት ቀጥሎ የተተነተነው የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ምድብ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ሰንጠረዥ 6 የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶችን ገጽታ አቅርቧል፡፡

### ሰንጠረዥ 6፡- በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የተፈጸሙ ስህተቶች

| የስርአተ-ነጥቦች ስህተቶች ምድብ | አንቀጽ አንድ | | | አንቀጽ ሁለት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት |
| አራት ነጥብ | 125 | 38.94 | 0.95 | 107 | 43.15 | 0.81 |
| ነጠላ ሰረዝ | 86 | 26.79 | 0.65 | 68 | 27.41 | 0.51 |
| ስርአተ-ነጥቦችን መደባለቅ | 63 | 19.63 | 0.47 | 45 | 18.15 | 0.34 |
| የእንግሊዝኛ ኮማ ማስገባት | 47 | 14.64 | 0.36 | 28 | 11.29 | 0.21 |
| ድምር | 321 | 100 | | 248 | 100 | |

በዚህ ጥናት በስህተትነት ከታዩት አበይት የስህተት ምድቦች ውስጥ በሁለቱ የአንቀጽ መጻፍ ዙሮች በጠቅላላው በቁጥር 569 ያህሉ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የስህተት ስርጭት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 321 ሲሆን በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 248 ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ ተጠኚዎቹ በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ረገድ በላጩን ስፍራ ይዘው የተገኙት በቅደም ተከተል የአራት ነጥብና የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ሲሆኑ ስርአተ-ነጥቦችን በመደባለቅ፣ የእንግሊዝኛውን ‹comma› እና ትእምርተ-አንክሮ /ቃለ አጋኖ/ን በነጠላ ሰረዝና በአራት ነጥብ ተክቶ መጠቀምም በአንዳንድ አንቀጾች ውስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ናቸው፡፡

በተጠኚዎቹ አንቀጾች ውስጥ በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ከታዩ ስህተቶች መካከል በይበልጥ የተፈጸመው የስህተት አይነት የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 125 (38.94%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 107 (43.15%) የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ በአራት ነጥብ አጠቃቀም የተፈጸመው ስህተት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.95 ሲሆን፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 0.81 ነው፡፡ ይህም ተጠኚዎቹ በአንቀጾቻቸው ውስጥ የፈጸሟቸውን አማካይ የአራት ነጥብ ስህተቶች መጠን ይጠቁማል፡፡

ለምሳሌ የሚከተሉትን አስረጂዎች እንመልከት፡-

- ደን መትከል ለብዙ ነገር ይጠክማል እና ደን ለቤት መስሪያ የቤት ውስጥ ቁሳቁሳት እንደ ሶፋ በርጩማ ክንቶርስ ለውቤት የአካባቢው ንጹ ንፋስ … ለቱርሶች መስቢ የተለያዩ ድንቄዬና ቢርቄዬ የአራዊት መኖሪያ…
- የኔ ቤተሰብ እንደማንኛውም ቤተሰብ ነው ቤተሰቦቼን በጣም እወዳቸዋለሁ ለምን ካላቹ ለምሳሌ ደብተር ቀለም ቦርሳ እና ወዘተ እነሱም ይወዱኛል ለምን ካላቹ ቀላል ስራዎችን በመስራት አግዛቸዋለሁ

ከላይ በቀረቡት የአንቀጾቹ ቅንጫቢዎች ውስጥ የአራት ነጥብ ስህተት ብቻ ሳይሆን፣ የነጠላ ሰረዝ እና የሆሄያት ስህተቶችም አብረው ይገኛሉ፡፡ ይህም ኦሮምኛ አፍ ፈት ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ በርከት ያሉ ስህተቶችን መስመር በመስመር እንደሚፈጽሙ ለማጤን የሚያስችል ነው፡፡

በተጠኚዎቹ አንቀጾች ውስጥ በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ከታዩ ስህተቶች መካከል ሁለተኛው አንጻራዊ ጉልህ የስህተት አይነት የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 86 (26.79%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 68 (27.41%) የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ በነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም የተፈጸመው ስህተት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.65 ሲሆን፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 0.51 ነው፡፡ ይህም እያንዳንዱ ተጠኚ በአንቀጾቹ ውስጥ የፈጸማቸውን የነጠላ ሰረዝ ስህተቶች አማካይ ስርጭትን ያመለክታል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ላም ለወተት ለስጋ ለገንዘቡ ጥጃ ለእርባታ እና ለተለያየ ነገር ትጠቅማለች (ከዚህ አስረጂ በግልጽ እንደምንመለከተው የአንቀጹ ጸሃፊ ተማሪ ምንም የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስርአትን ሳይከተል በርከት ያሉ ስሞችን ዘርዝሮ እናገኛለን፡፡ በርከት ያሉ የዚህ አይነት ስህተቶች በተማሪዎቹ አንቀጾች ውስጥ ይገኛሉ፡፡)

በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ከታዩ ስህተቶች መካከል ሶስተኛው አንጻራዊ ዝቅተኛ የስህተት አይነት ስርአተ-ነጥቦችን የመደባለቅ ስህተት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 63 (19.63%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽሽ 45 (18.15%) ስርአተ-ነጥቦችን የመደባለቅ ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ ስርአተ-ነጥቦችን በመደባለቅ የተፈጸመው ስህተት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.47 ሲሆን፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 0.34

ነው፡፡ ይህም ተጠኚዎቹ በአንቀጾቻቸው ውስጥ የፈጸሚቸውን የነጠላ ሰረዝ ስህተቶች የአማካይ ስርጭት አንጻራዊ ዝቅተኛነትን ይጠቁማል፡፡

**ለምሳሌ** የሚከተለውን አስረጂ እንመልከት፡-

- መማር ብዙ ጥቅም አለው፤፡፡ ከነዚም ውስጥ ጠቀስ ለማድረግ ያህል፤ በመጀመሪያም በእውቀት አእምሬችን እንዲካብት ያደርገናል፡፡፤ ሲቀጥል ባገኘነው እውቀት የአከባቢያችን ችግሬች እንድፈታ ያግዘናል፡፡፤ በሌላ በኩል ህይወታችን እንድቀየር ይረዳናል፤

ከፍ ሲል ከቀረበው አስረጂ እንደምንመለከተው የአንቀጹ ጸሀፊ ተማሪ አንድ ቦታ ላይ ድርብ ሰረዝን ከአራት ነጥብ ጋር ደርቦ መጠቀሙ ጉልህ የስርአተ ነጥብ ስህተት ከመሆኑም በላይ በአንቀጹ መጨረሻ ላይ በአራት ነጥብ ፋንታ ድርብ ሰረዝን አስገብቶ ይገኛል፡፡

በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ከታዩ ስህተቶች መካከል አራተኛው በዝቅተኛ መጠን የታየ ስህተት የእንግሊዝኛ ኮማን ያለአውዱ የማስገባት ስህተት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 47 (14.64%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 28 (11.29%) የእንግሊዝኛ ኮማን ያለአውዱ የማስገባት ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ የእንግሊዝኛ ኮማን ያለአውዱ በማስገባት የተፈጸመው ስህተት በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ በአማካይ 0.36 ሲሆን፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 0.21 ነው፡፡ ይህም ተጠኚዎቹ በአንቀጾቻቸው ውስጥ የፈጸሚቸውን የእንግሊዝኛ ኮማን ያለአውዱ የማስገባት ስህተቶች የአማካይ ስርጭት ዝቅተኛነትን ይጠቁማል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ላም ቅቤ አይብ አሬራ ትሰጣለች(,)
- ዘፍ ካለ እንስሳት ሰዎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ይኖራሉ (,)
- የኢቲዮፒያ ህዝቢ ዛፍ ይተክላል እንስሳት ያረባል ይመስላል (,)

በቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች ስር ከተመደቡት የስህተት አይነቶች መካከል በቁጥር አናሳ ስህተቶች የተቆጠሩበት የሀሳብ አንድነትን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች ምድብ መሆኑ ቀደመ ሲል ተጠቁሟል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ የተፈጸሙ ዝርዝር ስህተቶች በሰንጠረዥ 7 እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 7፡- የሀሳብ አንድነትን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች

| የሀሳብ አንድነትን ያለመጠበቅ ስህተቶች ምድብ | አንቀጽ አንድ | | | አንቀጽ ሁለት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት | የስህተት ብዛት | መቶኛ ስሌት | አማካይ ስህተት |
| አያያዥ ቃላትን በአግባቡ አለመጠቀም | 92 | 56.44 | 0.70 | 87 | 65.91 | 0.66 |
| የሃሳብ መዛነፍ | 51 | 31.29 | 0.39 | 31 | 23.48 | 0.23 |
| የተሳሳተ አደራደር መከተል | 20 | 12.27 | 0.15 | 14 | 10.61 | 0.11 |
| ድምር | 163 | 100 | | 132 | 100 | |

ከላይ በቀረበው የሀሳብ አንድነትን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች ምድብ ውስጥ ሦስት የስህተት አይነቶች ተለይተዋል፡፡ በምድቡ ውስጥ የታዩት አጠቃላይ ስህተቶች 295 ሲሆኑ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 163 እንዲሁም በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 132 የሀሳብ አንድነትን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡
በዝርዝር ሲታይ አያያዥ ቃላትን በአግባቡ አለመጠቀም የስህተት ምድቡ በላጭ የስህተት መጠን ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 92 (56.44%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 87 (65.91%) ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ አያያዥ ቃላትን በአግባቡ አለመጠቀም በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ዙር አንቀጾች

የተፈጸሙ አማካይ ስህተቶች በየአንጻራቸው 0.70 እና 0.66 የሚያሳዩት በስህተት አይነቱ የእያንዳንዱን ተጠኚ አማካይ የስህተት ድርሻ ነው፡፡

**ምሳሌ፡- የአያያዥ ሰህተት የታየበት**

- ስለዚህ ትምህርት ለሰው ባጠቃላይ በጣም አስፈላጊ ነው (ስለዚህ ትምህርት ለሰው በጣም አስፈላጊ ነው/ ባጠቃላይ ትምህርት ለሰው በጣም አስፈላጊ ነው)
- ቁምነገር ና እውቀት እናገኛለን (ቁምነገር እና እውቀት እናገኛለን)

- ትምርት ሰው ይለውጣል እጅ አይጎዳም (ትምህርት ሰውን ይለውጣል እንጅ አይጎዳም)

በቅደም ተከተል የሃሳብ መዛነፍ ስህተት መጠነኛ የስህተት መጠን የተመዘገበበት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 51 (31.29%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 31 (23.48%) ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ የሃሳብ መዛነፍ ስህተት በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ዙር አንቀጾች የተፈጸሙ አማካይ ስህተቶች በየአንጻራቸው 0.39 እና 0.23 የሚያመላክቱት በሃሳብ መዛነፍ ስህተት የእያንዳንዱን ተጠኚ አማካይ የስህተት ድርሻን ነው፡፡

- በህይወቴ በተሰቦች መቸም የማይረሳኝ ነገር .......
- እናም እኔ አንድ ዜጋ እስከመሆኔ መጠን የህገሬን አስጠያፊ ነገር...
- ኢትዮፒያ ምድር ዛፍ ስላለው ነው..................

ቀጥሎ የተሳሳተ አደራደር በመከተል ዝቅተኛ የስህተት መጠን የታየ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 20 (12.27%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 14 (10.61%) ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ የተሳሳተ አደራደር በመከተል በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ዙር ድርሰቶች በተጠኚዎቹ የተፈጸሙ አማካይ ስህተቶች በየአንጻራቸው 0.15 እና 0.11 የሚያሳዩት የተሳሳተ አደራደር በመከተል የእያንዳንዱን ተጠኚ አማካይ የስህተት ድርሻን አንጻራዊ ዝቅተኛነት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-**

- ...ያኔ የህጻንነት ተምህርት ቤት ያኔ ያኔ ድሮ የልጅነት የጨቅላነት እድሜ ውብ አስደሳች ጊዜ ውል ሲል በአይኔ ወደ ዋላ ሃሳቤን ሰድጄ ሳስብ ሳሰላሲል የልጅነት ጊዜዬን ጭንቀት የሌለበት ያ ውብ ጊዜ ሲጫወት ሲቦርቅ በዳገት በሜዳው በሽንተረሩ በጫካው ... በተለይ አመት ባል የመጣ ጊዜ በተለይ ትዝ ይላል...

በአጠቃላይ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ በርካታ የስህተት አይነቶችን ደጋግመው የሚፈጽሙ መሆናቸው ተስተውሏል፡፡ በተጠኚዎቹ ተደጋግመው ከተጻፉ አንቀጾች በውል ማጤን እንደተቻለው ከሁሉም የስህተት አይነቶች በላጩና በበርካታ ተማሪዎች ተደጋግመው የሚፈጸሙት ስህተቶች ሰዋስዋዊ ስህተቶች (ባለቤትና ተሳቢን በአግባቡ አለመጠቀም፣ የመደብ ስህተት፣ የቁጥርና ጾታ አለመስማማት፣ የመስተዋድድ አጠቃቀም ስህተቶች) ጎልተው ተስተውለዋል፡፡ ቀጥሎም በተጠኚዎቹ አንቀጾች ውስጥ ተደጋግሞው የተጤኑት የስህተት አይነቶች የስነድምጽ አጠቃቀም ስህተቶች ሲሆኑ በዚህ የስህተት ምድብ ሆሂያትን በሌላ ሆሄ መተካት፣ የሆሄያት ቅነሳ፣ የሆሄያት ጭመራ እና የሆሄያት ቦታ ቅየራ ስህተቶች

በጉልህ ታይተዋል፡፡ በሌላ በኩል በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ተማሪዎቹ የተሳሳተ የቃላት ምርጫ፣ የቃላት ድግግሞሽ፣ ቃላትን መተው፣ ቃላትን ያለቦታቸው መስገባት የመሳሰሉ ስህተቶች በተማሪዎቹ አንቀጾች ውስጥ ጎልተው መስተዋላቸውን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡ በስርአተ ነጥብ (አራት ነጥብና ነጠላ ሰረዝ) እንዲሁም አያያዥ ቃላትን በአግባቡ ባለመጠቀም ረገድም የተፈጸሙ ስህተቶች የሰዋስው እና ስነድምጽ ስህተቶች ያህል ባይበረክቱም በበርካታ ተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶች መሆናቸው ተጢኗል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋንኛ ምክንያቶቹ ምንድናቸው?›› የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ በጽሁፍ መጠይቅ ከተጠኚዎቹ በተሰበሰቡ መረጃዎች በመደገፍ ትንተና ቀርቧል፡፡ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 8፣ 9 እና 10 በየአንጻራቸው ከተማሪዎቹ ስነልቦናዊ ችግሮች፣ ከመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተገናኙ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ችግሮችን መሰረት በማድረግ መረጃዎቹ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 8፡- በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በመጻፍ ረገድ ከተማሪዎቹ የተያያዙ ችግሮች**

| ተ.ቁ | አንቀጽ ለመጻፍ የተማሪዎቹ ስነልቦናዊ ችግሮች አመላካቾች | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | የሰዋስው አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስ በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ የማያጋጥመኝ ችግር ነው፡፡ | 3.94 | .844 |
| 2 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ሃሳብ የማመንጨት ችግር | 3.88 | .832 |
| 3 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ስለሚጻፍበት ርእሰጉዳይ የተሟላ ግንዛቤ የሌለኝ መሆኑ የስጨንቀኛል፡፡ | 3.73 | .811 |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ የቋንቋ አጠቃቀም ግንዛቤ | 3.71 | .707 |
| 5 | ዝቅተኛ የሆነ የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ችግር ፈጥሮብኛል፡፡ | 3.55 | .788 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ ውጤት | 3.76 | 0.796 |

ከላይ በሰንጠረዥ 8 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ተጠኚዎቹ የአንቀጽ መጻፍ ግንዛቤ ማነስ /ስነልቦናዊ/ ችግሮች አሉባቸው፡፡ በአጠቃላይ ለአብይ ተላውጠው የተማሪዎቹ ምላሽ አጠቃላይ አማካይ ውጤት 3.76 ከመደበኛ ልይይት 0.796 ጋር ተሰልቷል፡፡ አጠቃላይ አማካዩ የሚያመለክተው ተጠኚዎቹ በአንቀጽ መጻፍ የግንዛቤ

ማነስ ችግሮች የሚታይባቸውን አጠቃላይ ክፍተት ነው፡፡ መደበኛ ልይይቱ (0.796) የሚጠቁመው የእያንዳንዱ ተጠኚ ምላሽ ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት በመጠኑ ሰፊ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ማለት ተጠኚዎቹ ለጽሁፍ መጠይቁ የሰጧቸው ምላሾች በመጠኑ የተራራቁ ናቸው፡፡

ተጠኚዎቹ ካሉባቸው አንቀጽ የመጻፍ የግንዛቤ ችግሮች መካከል አንጻራዊ ጉልህነት ያላቸው የሰዋሰው አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስ (አማካይ ውጤት 3.94 ከመደበኛ ልይይት 0.844 ጋር)፣ በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ሃሳብ የማመንጨት ችግር (አማካይ ውጤት 3.88 ከመደበኛ ልይይት 0.832 ጋር)፣ በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ስለሚጻፍበት ርእሰጉዳይ የተሟላ ግንዛቤ አለመኖር (አማካይ ውጤት 3.73 ከመደበኛ ልይይት 0.811 ጋር) እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ የቋንቋ አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስ (አማካይ ውጤት 3.71 ከመደበኛ ልይይት 0.707 ጋር) መፍትሄ የሚሹና አንቀጽ መጻፍን ትኩረት ሰጥቶ በማለማመድና በማበረታታት ሊቃለሉ የሚችሉ ችግሮች ናቸው፡፡

## ሰንጠረዥ 9፡- የመጻፍ ክሂልን ለመማር ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተገናኙ ችግሮች መረጃ ትንተና

| ተ.ቁ | የመጻፍ ክሂልን ከማስተማሪያ ዘዴና ማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ጋር የተገናኙ ችግሮች አመላካቾች | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | የመጻፍ ክሂልን በበቂ ሁኔታ አለመለማመድ የአንቀጽ አጻጻፍ ግንዛቤ እንዳላዳብር አድርጎኛል፡፡ | 3.93 | .734 |
| 2 | ዘጠነኛ ክፍል ከመግባቴ በፊት በቂ የመጻፍ ልምምድ አለማድረጌ በአሁኑ ወቅት አንቀጽ ስጽፍ ያሳደረብኝ አሉታዊ ተጽእኖ ጉልህ | 3.93 | .846 |
| 3 | ለመጻፍ ክሂል መዳበር የሚጠቅሙ የተለያዩ ጽሁፎች በየጊዜው አይቀርቡልኝም፡፡ | 3.85 | .701 |
| 4 | የአንቀጽ አጻጻፍ መርሆዎች ምን እንደሆኑ አለማወቄ አንቀጽ ከመጻፍ አግዶኛል፡፡ | 3.81 | .747 |
| 5 | በጽሁፍ የሚቀርቡ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርአቶችን አለማወቁ ስህተት እንድፈጽም ያደርገኛል፡፡ | 3.79 | .651 |
| 6 | የጽሁፍ ቋንቋ አጠቃቀም ደንብን አለማወቅ አንቀጽ ከመጻፍ እንድቆጠብ ምክንያት ነው፡፡ | 3.73 | .627 |
| 7 | በአማርኛ ቋንቋ ስጽፍ ትክክል ላልሆን እችላለሁ እያልኩ ሁልጊዜ እጠራጠራለሁ፡፡ | 3.71 | .728 |
| 8 | የጽሁፍ ስህተት ፍርሃት በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ከመጻፍ እንድቆጠብ ምክንያት ነው፡፡ | 3.68 | .821 |
| 9 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ የአጻጻፍ ብልሃቶች ግንዛቤ እጥረት | 3.68 | .663 |
| 10 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ሳስብ ሀሳብ ይጠፉብኛል ወይም ሀሳቤ እየተዘበራረቀ ያስቸግረኛል፡፡ | 3.64 | .622 |
| | አጠቃላይ አማካይ | 3.78 | 0.714 |

በተመሳሳይ መልኩ በሰንጠረዥ 9 ለቀረቡላቸው ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተገናኙ ችግሮች አመላካቾች የሰጧቸው ምላሾች መረጃ አጠቃላይ አማካይ 3.78 ከመደበኛ ልይይት 0.714 ጋር የሚያሳየው ተጠኚዎቹ የመጻፍ ክሂልን ለመማር ያሉባቸውን ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር ለተገናኙ ችግሮች ያሳዩትን ስምምነት መጠን ነው፡፡ መደበኛ ልይይቱ (0.714) የእያንዳንዱ ተጠኚ ምላሽ አማካይ ከአጠቃላይ አማካዩ ያለው ርቀት በመጠኑ ሰፊ መሆኑን ነው፡፡

ተጠኚዎቹ ያሉባቸው ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተዛመዱ ችግሮች በቅደም ተከተል የመጻፍ ክሂልን በበቂ ሁኔታ አለመለማመድ (አማካይ ውጤት 3.93 ከመደበኛ ልይይት 0.734 ጋር) እንዲሁም ዘጠነኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት በቂ የመጻፍ ልምምድ አለማድረጋቸው (አማካይ ውጤት 3.93 ከመደበኛ ልይይት 0.846 ጋር) ተመሳሳይ ክብደት ተሰጥቷቸው የቀረቡ ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተገናኙ ችግሮች ናቸው፡፡ ለመጻፍ ክሂል መዳበር የሚጠቅሙ የተለያዩ ጽሁፎች በየጊዜው አለመቅረባቸው በተቀራራቢ ክብደት የተጠኚዎቹን የመጻፍ ተጋልጦ የገቱ መሆናቸው (አማካይ ውጤት 3.85 ከመደበኛ ልይይት 0.701 ጋር) የተጠቀመ ከመስተማሪያ ዘዴ ጋር የተገናኘ ችግር መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ የአንቀጽ አጻጻፍ መርሆዎች ምን እንደሆኑ አለማወቅ (አማካይ ውጤት 3.81 ከመደበኛ ልይይት 0.747 ጋር)፣ በጽሁፍ የሚቀርቡ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርአቶችን አለመገንዘብ (አማካይ ውጤት 3.79 ከመደበኛ ልይይት 0.651 ጋር)፣ የጽሁፍ ቋንቋ አጠቃቀም ደንብን አለመረዳት (አማካይ ውጤት 3.73 ከመደበኛ ልይይት 0.627 ጋር) እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ ትክክል ላልሆን እችላለሁ እያሉ መጠራጠር (አማካይ ውጤት 3.71 ከመደበኛ ልይይት 0.728 ጋር) ተጠኚዎቹ በአንጻራዊ ተቀራራቢ የስምምነት ምላሽ ከማስተማሪያ ዘዴ የተዋረሱ አንቀጽ የመጻፍ ችግሮቻቸውን መጠቆማቸውን መረጃው አመላክቷል፡፡

ቀጥሎም የጽሁፍ ስህተት ፍርሃት በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ከመጻፍ እንዲቆጠቡ ያለው አስተዋጽኦ (አማካይ ውጤት 3.68 ከመደበኛ ልይይት 0.821 ጋር) እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ የአጻጻፍ ብልሃቶች ግንዛቤ እጥረት (አማካይ ውጤት 3.68 ከመደበኛ ልይይት 0.663 ጋር) በተመሳሳይ የስምምነት ደረጃ የተጠቀሙ ሲሆኑ በመጨረሻም በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ሲያስቡ ሀሳብ የሚጠፋባቸው ወይም ሀሳቡ እየተዘበራረቀ የሚያስቸግራቸው መሆኑ (አማካይ ውጤት 3.64 ከመደበኛ ልይይት 0.662 ጋር) የተጠቀመ የተጠኚዎቹ ችግር መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

## ሰንጠረዥ 10፡- በአንቀጽ መጻፍ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች መረጃ ትንተና

| | ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች አመላካቾች | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | አንቀጽ ስጽፍ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ጣልቃ እየገባ [illegible] | 4.65 | .552 |
| 2 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ስጽፍ የኦሮምኛ ቋንቋ የአረፍተነገር ስርአት (ስልት)ን መከተል ይቀናኛል፡፡ | 4.52 | .457 |
| 3 | በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፌ ውስጥ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን በአግባቡ መጠቀም ያዳግተኛል፡፡ | 4.26 | .506 |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ስጽፍ ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ ተነባቢ ድምጾች በትክክል ማስቀመጥ ያስቸግረኛል፡፡ | 4.06 | .414 |
| 5 | በጽሁፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለመለየት እቸገራለሁ፡፡ | 3.97 | .447 |
| | አጠቃላይ አማካይ | 4.29 | 0.475 |

ሰንጠረዥ 11 ከሌሎቹ ተላውጦዎች በበለጠ ሁኔታ በአንቀጽ መጻፍ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮችን መረጃ ያሳያል፡፡ በዚሁ መሰረት ተጠኚዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተላውጦ አንቀጽ በመጻፍ ሂደት ያለውን ተጽእኖ ተጠኚዎቹ ያመላከቱበት መጠን በሌሎች በጽሁፍ መጠይቅ ከሰጧቸው ምላሾች አንጻር ከፍ ያለ ስምምነታቸው የታየበት መሆኑን የቀረበው መረጃ ያሳያል፡፡ ይህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተላውጦ አንቀጽ ለመጻፍ ተጠኚዎቹ ካሉባቸው ችግሮች ከሁሉም የበለጠ ተጽእኖ ማሳደሩን ያስገነዝባል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተላውጦ ተጽእኖ በአጠቃላይ አማካይ 4.29 እና በመደበኛ ልይይት 0.475 ተሰልቷል፡፡ መደበኛ ልይይቱ (0.475) የሚያመለክተው እያንዳንዱ ተጠኚ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር ለተያያዙ ችግሮች የሰጠው አማካይ ምላሽ ከአጠቃላይ አማካዩ ያልራቀ ወይም ተቀራራቢ መሆኑን ጠቋሚ ነው፡፡

በቅደም ተከተል አንቀጽ ሲጽፉ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ እየገባ የሚያስቸግራቸው መሆኑን የጠቀሙበት መጠን ከሁሉም የተላውጦ ምድቦች የበለጠ መሆኑን (አማካይ ውጤት 4.65 ከመደበኛ ልይይት 0.552 ጋር) ያመለክታል፡፡ ከዚህ የውስጠ-ቋንቋ ተጽእኖ ቀጥሎ በተጠኚዎቹ የተጠቀመው ጉልህ የውስጠ-ቋንቋ ችግር በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የኦሮምኛ ቋንቋ የአረፍተነገር ስርአት (ስልት)ን መከተል (አማካይ ውጤት 4.52 ከመደበኛ ልይይት 0.457 ጋር) ሲሆን፣ ቀጥሎም በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፋቸው ውስጥ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን በአግባቡ አለመጠቀም (አማካይ ውጤት 4.26 ከመደበኛ ልይይት 0.662 ጋር) የውስጠ-ቋንቋ ተጽእኖ መሆኑ ታውቋል፡፡ በፊደላት አጻጻፍ ላይ ያሉባቸው ችግሮች በአንቀጽ ጽሁፋቸው ውስጥ በቃላት ስህተትነት በተገለጸው ትንተና ውስጥም ጉልህ ሆነው መገኘታቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡ ሌላው የውስጠ-ቋንቋ ችግር በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ ተነባቢ ድምጾች በትክክል ማስቀመጥ መቸገራቸው (አማካይ ውጤት 4.06 ከመደበኛ ልይይት 0.414 ጋር) ተጠቁሟል፡፡ በመጨረሻም በጽሁፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለመለየት መቸገራቸው (አማካይ ውጤት 3.97 ከመደበኛ ልይይት 0.447 ጋር) ተጠቁሟል፡፡ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለመለየት መቸገራቸውን ተጠኚዎቹ ያመላከቱበት የአማካይ ውጤት ልኬት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተላውጦ ምድቡ የመጨረሻው አንጻራዊ ዝቅተኛ ምላሽ የታየበት ቢሆንም ለጽህፈት ስህተት የሚያበረክተው ድርሻ ጉልህ ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል በተማሪዎቹ ድርሰቶች በስዋስው ስህተቶች ትንተና የቁጥርና ጾታ ንኡስ ዘርፍ ከቀረበው ትንተና ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ይዞ ለተነሳቸው ሁለት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች በጥናቱ መረጃ ትንተና ክፍል በተለያዩ መጠናዊ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ትንተና ቀርቧል፡፡ በአጠቃላይ የተተነተኑት መረጃዎች ተዛማጅነት ባለው መልኩ የተጠኚዎቹን የአንቀጽ ጽህፈት የተለያዩ ስህተቶችን ለመተንተንና አንቀጽ ለመጻፍ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመመዘን ረድተዋል፡፡ በትንተናው የተደረሰባቸው ውጤቶች እርስ በእርስ የሚደጋገፉ መሆናቸውንም ጥናቱ ተመልክቷል፡፡

በዚህ መሰረት የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ ምን አይነት ስዋስዋዊ ስህተቶችን ይፈጽማሉ?›› የሚል ሲሆን፣ ለዚህ ጥያቄ በቂ ምላሽ ለማግኘት ለተጠኚዎቹ ከቀረቡት

የአንቀጽ መጻፊያ ርእሶች ላይ በመረጡት በአንዱ ርእስ ብቻ ሁለት ጊዜ በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የፈጸሟቸው ስህተቶች ተለይተው የተገኘው መረጃ በገላጭ ስታቲስቲክስ ተተንትኗል፡፡ የቀረበው መረጃ እንዳመለከተው በአንቀጽ አንድና ሁለት በተጠኚዎቹ አንቀጾች ውስጥ የቀረቡ አጠቃላይ ቃላት ብዛት 10398 ሲሆኑ፣ በአንቀጽ አንድ 5282 በአንቀጽ ሁለት 5116 ቃላት ተጠቅመው አንቀጾቻቸውን ጽፈዋል፡፡ በትንተናው የተገኙት የአንቀጽ ጽህፈት ስህተቶች በአምስት ዋና ዋና የአንቀጽ ጽህፈት ስህተቶች ተፈርጀዋል፡፡ እነዚህ የስህተት ምድቦች በስህተቶች ጉልህነት አንጻር በቅደም ተከተል ሰዋሰዋዊ አገባብ አለመጠበቅ፣ የፊደላት አጻጻፍ ስህተት፣ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ስህተት፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት፣ የሀሳብ አንድነት ያለመጠበቅ ስህተትና በጣም ጥቂት ከስህተት ምድቦቹ የተለዩ ስህተቶች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

በዋናዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ ተጠኚዎቹ ምን አይነት ዝርዝር ስህተቶችን በድግግሞሽ እንደፈጸሙ የቀረበውን አጠቃላይ የስህተት መረጃ መሰረት በማድረግ ዝርዝር ትንተና ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት ስዋስዋዊ አገባብን ባለመጠበቅ በተፈጸሙ ስህተቶች የድግግሞሽ መረጃ እንዳመለከተው የባለቤትና ተሳቢ አጠቃቀም ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (266) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (253) በድምሩ 519 (30.1%) ስህተቶችን ደጋግመዋል፡፡ ቀጥሎ የመደብ አገላለጽ ስህተቶች የድግግሞሽ መረጃ እንዳመለከተው ስህተቶቹ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (257) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (232) በድምሩ 489 (28.36%) ስህተቶችን ደጋግመዋል፡፡ በቁጥርና ጾታ አለመስማማት የተፈጸሙ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (239) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (184) በድምሩ 423 (24.54%) ስህተቶች መደጋገማቸውን ትንተናው ተመልክቷል፡፡ ስዋስዋዊ አገባብን ባለመጠበቅ ከተፈጸሙ ስህተቶች በድግግሞሽ ከሁሉም ዝቅ ያለው የመስተዋድዶች አለመስማማት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (156) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (137) በድምሩ 293 (16.99%) ስህተቶችን ደጋግመዋል፡፡ በአጠቃላይ ተጠኚዎቹ ስዋስዋዊ አገባብን ባለመጠበቅ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (918) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (806) በድምሩ 1724 (37.82%) ስህተቶችን በሁለቱ ዙር አንቀጾቻቸው ውስጥ በድግግሞሽ ፈጽመው መገኘታቸውን የትንተናው ውጤት አመላክቷል፡፡

በስነ-ድምጽ አጻጻፍ የተፈጸሙ ስህተቶች ከአጠቃላዩ የአንቀጽ ስህተት ሁለተኛውን የስህተት ደረጃ የያዙ ናቸው፡፡ በዚህ የአንቀጽ ስህተት ተላውጦ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ የታዩ የፊደላት አጻጻፍ ስህተቶች ብዛት 609 ሲሆን በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ የታዩ የፊደላት አጻጻፍ ስህተቶች ብዛት 543 በአጠቃላይ የስነ-ድምጽ ስህተቶች 1152 (25.27%) መሆናቸውን የትንተናው ውጤት አመላክቷል፡፡ በዚህ የአንቀጽ መጻፍ ስህተት በተጠኚዎቹ ከተፈጸሙ ስህተቶች መካከል ከሁሉም ጉልህ ድግግሞሽ የታየበት ሆሄያትን በሌላ ሆሄ የመተካት ስህተት ሲሆን ተጠኚዎቹ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (209) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (168) በድምሩ 377 (32.73%) ስህተቶችን መደጋገማቸው ተረጋግጧል፡፡ ቀጥሎ የሆሄያት ቅነሳ ስህተቶችን በመደጋገም በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (164) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (152) በድምሩ 316 (27.43%) የሆሄያት ቅነሳ ስህተቶችን መፈጸማቸው ታውቋል፡፡ ከዚህ በሚነጻጸር መልኩ በሆሄያት ጭመራ ተጠኚዎቹ የፈጸሟቸው ስህተቶች ድግግሞሽ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (123) እና በሁለተኛው ዙር ድርሰት (119) በድምሩ 242 (21.01%) መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ሌላው የሆሄያት ቦታ ቅየራ መከተል ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ (113) እና በሁለተኛው ዙር አንቀጽ (104) በድምሩ 217 (18.84%) ስህተቶችን የሆሄያት ቦታ ቅየራ

በመከተል ደጋግመው ፈጽመው ተገኝተዋል፡፡ በአጠቃላይ በስነ-ድምጽ አጻጻፍ ረገድ ተጠኚዎቹ ሆሄያትን በሌላ ሆሄ መተካት፣ የሆሄያት ቅነሳ፣ የሆሄያት ጭመራ እና የሆሄያት ቦታ ቅየራ ስህተቶች በተጠኚዎቹ የአንቀጽ ጽሁፎች ውስጥ ጎልተው ተስተውለዋል፡፡

ከጠቅላላው የአንቀጽ ስህተት ተጠኚዎቹ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 401፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 361 ሲሆኑ በአጠቃላይ በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የፈጸሟቸው ስህተቶች 762 (16.72%) ናቸው፡፡ ተጠኚዎቹ በቃላትና አመራረጥና አጠቃቀም ከፈጸሟቸው ስህተቶች በስህተት ድግግሞሽ የመጀመሪያውን ስፍራ የያዘው በቃላት ምርጫ የፈጸሟቸው ስህተተቶች ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ተገቢ የቃላት ምርጫን ባለመከተል የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 123 (30.67%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 112 (31.02%) በድምሩ 235 (30.84%) ስህተቶችን ደጋግመዋል፡፡ ተጠኚዎቹ ቃላትን በመደጋገም የፈጸሟቸው ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ

መጻፍ 116 (28.92%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 105 (29.09%) በድምሩ 221 (29.0%) ስህተቶችን በድግግሞሽ መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡

ሌላው በቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ተጠኚዎቹ የፈጸሙት የስህተት ድግግሞሽ አስፈላጊ ቃላትን በመተው የተፈጸሙ ስህተቶችን የሚመለከት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 88 (21.94%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 74 (20.498%) በድምሩ 162 (21.26%) አስፈላጊ ቃላትን የመተው ስህተቶችን ደጋግመዋል፡፡ ቀጥሎ ቃላትን ያለቦታቸው በማስገባት ተጠኚዎች የፈጸሟቸው ስህተቶች ደግሞ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 74 (18.45%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 70 (19.39%) በድምሩ 144 (18.89%) ስህተቶችን ደጋግመዋል፡፡ በአጠቃላይ ተገቢ የቃላት ምርጫን ባለመከተል፣ አስፈላጊ ቃላትን በመተውና ቃላትን ያለቦታቸው በማስገባት የተፈጸሙ ስህተቶች ተስተውለዋል፡፡

በመጨረሻ የሀሳብ አንድነትን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች ምድብ ውስጥ ሶስት የስህተት አይነቶች ተለይተዋል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ የተገኙ ስህተቶች በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ በአጠቃላይ 163 (6.63%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 132 (6.25%) በድምሩ 295 (6.47%) ስህተቶችን በመደጋገም መፈጸማቸው ተመልክቷል፡፡ ከምድቡ የመጀመሪያው ጉልህ የስህተት ድግግሞሽ አያያዥ ቃላትን በአግባቡ ባለመጠቀም የተፈጸመ ስህተት ሲሆን በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 92 (56.44%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 87 (65.91%) በድምሩ 179 (60.68%) ስህተቶችን በመደጋገም መፈጸማቸው በትንተናው ተረጋግጧል፡፡ ቀጥሎም የሃሳብ መዛነፍ የስህተት አይነት በድግግሞሽ የተፈጸመ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 51 (31.29%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 31 (23.48%) በድምሩ 82 (27.39%) የሀሳብ መዛነፍ ስህተቶችን በመደጋገም መፈጸማቸውን ትንተናው ቃኝቷል፡፡ ሌላው በዚህ የስህተት ምድብ የታየው የስህተት አይነት የተሳሳተ አደረደር መከተል ሲሆን፣ በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ መጻፍ 20 (12.27%)፣ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ መጻፍ 14 (10.61%) በድምሩ 34 (11.53%) የተሳሳተ አደረደር መከተል በድግግሞሽ ተፈጽሟል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ በአጠቃላይ አያያዥ ቃላትን በአግባቡ ባለመጠቀም፣ የሃሳብ መዛነፍ እና የተሳሳተ አደረደር መከተል ስህተቶች በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ መታየታቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱ ዙሮች አንቀጽ መጻፍ አበይት የስህተት ምድቦች የስህተት አይነቶቹ የስርጭት መጠን አንጻራዊ ትይዩነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ የመረጃ ትንተናው በተዋረድ እንዳመላከተው በንጽጽር ከመጀመሪያው ዙር የአንቀጽ ስህተት መጠን በየስህተት ምድቦቹ በሁለተኛው ዙር አንቀጽ ስህተት መጠን ጉልህነቱ ወጥነት ባለው መልኩ የቀነሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ተጠኚዎቹ በአንድ አይነት የአንቀጽ ርእስ ደግመው የመጻፍ እድል ያገኙ በመሆናቸው የተፈጠረ መሻሻል ሊሆን እንደሚችል ከመረጃ ትንተናው በመነሳት አጥኚዋ የራሷን ግምት ወስዳለች፡፡

በሌላ በኩል በሁለቱ የአንቀጽ መጻፍ ዙሮች በእያንዳንዱ የስህተት ምድብ በተተነተኑት የስህተት አይነቶች የስህተቶቹ የድግሞሽ መጠን ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ይህም የሚያመለክተው በተተነተኑት የስህተት አይነቶች ሁሉ ተጠኚዎቹ በሁለቱ ዙሮች አንቀጾቻቸው ውስጥ ደግመው የፈጸሙት በትክክል ስህተቶችን እንጂ በመጣደፍ ወይም ባለመረጋጋት ሊፈጸሙ የሚችሉ ግድፈቶችን አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት ተገኝ (2000)፣ ሁሴን (2009) ከደረሱበት የጥናት ውጤት ጋር በተለይ የጽህፈት ስህተቶችና ችግሮችን በተመለከተ፣ በታላሚው ቋንቋ የሚያዘጋጁት የጽሁፍ ስራ ውጤት መጠን ማነስ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ ተግባቦታዊ የክፍል አያያዝ እና የግብረ-መልስ ስልት ባለመኖር ምክንያት እና የቋንቋ ትምህርቱ ህግጋት ትግበራ ተከታታይነት ማጣት እንደሆኑ ካረጋገጡት ጋር በከፊል ይገናዘባል፡፡ ይሁንና የአንቀጽ ስህተት መንስኤዎች በዚህ ጥናት የተቃኙበት መንገድ የስህተት ምንጮችን ለማጥናት ታልሞ ሳይሆን የተጠኚዎቹን ድርሰት በመፈተሽ መንገድ የተነሱ መሆናቸው ከተገኝ (2000) እና ሁሴን (2009) የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሌላው የአምላክሥራ (2000)፣ ከቃኘችው የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና ጋርም በከፊል ተመሳስሎ አለው፡፡ የአምላክሥራ ጥናት ውጤት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የስህተት መረጃዎችን ለማግኘት በተጠኚ ተማሪዎቹ በሁለት ዙር 157 ድርሰቶች እንዲጽፉ አድርጋ በነዚህ ድርሰቶች መሰረት ተማሪዎቹ በጽሑፋቸው ለይ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመለየት ችላለች፡፡ በተማሪዎች እና በመምህራን ከተሞሉ መጠይቆች በተገኙ መረጃዎች መሰረት የስህተቶቹ ምንጮች የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት፣ የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት እና የስነልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ መሆናቸውን አቅርባለች፡፡ ይሁን እንጂ የአምላክሥራ በአማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች ላይ

ስታተኩር ይህ ጥናት በአማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ የአምላክሥራ ድርሰት መጻፍ ላይ ስታተኩር ይህ ጥናት በአንቀጽ ስህተት ላይ መወሰኑ፣ የአምላክሥራ የስህተት ምንጭ ትንተናን በጥናቷ አካትታ ያቀረበች ሲሆን ይህ ጥናት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ላይ ያሉባቸው ችግሮች ለጽሁፍ ስህተት ጉልህነት ያለውን አስተዋጽኦ በመመርመር የተወሰነ በመሆኑ የጥናት ውጤቶቻችን በከፊል እንዲለያዩ አድርጓል፡፡

የተካቡ ጥናት አማርኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሙት ሰዋሰዋዊ ስህተትን የሚያሳይ ነው፡፡በአንቀጽ ትንተና ላይ መካሄዱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ በሚካሄደው ቋንቋና በሚካሄድበት ቦታ ይለያያሉ፡፡

መሰረት2003) አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲፅፉ የፈጸሟቸው ስነ ልሳናዊ ስህተቶች በሚል ርዕስ ካካሄደችው የጥናት የውጤት ጋርም በከፊል ይመሳሰላል፡፡መሰረት በውጤቷ ስነ-ልሳናዊ ስህተቶች ማለትም፣ ስነ ድምፃዊ፣ የቋንቋ አጠቃቀም ፣የቋንቋ አወቃቀር፣የስርዓተነጥብና ያልተለዩ ስህተቶች መሆናቸውን የገለጸች ሲሆን መሰረት በድርሰት መፃፍ በመሆኑ ይለያያሉ፡፡ተገኝ (2000) አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል ርዕስ ባካሄደው ጥናት ከደረሰበት ውጤት ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ከፊል ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ በአጠቃላይ ተገኝ (2000) አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ በፈቱ ቋንቋ በፈቱ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑ እንዲሁም ከፍ ሲል ከቀረቡት ጥናቶች በተለየ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የአንቀጽ መጻፍ ስህተቶችና በአንቀጽ መጻፍ የገጠሟቸውን ችግሮች ለጽሁፍ ስህተት ጉልህነት ያለውን አስተዋጽኦ የቃኘ በመሆኑ የተለየ አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ በአንቀጽ ጽህፈት ስህተት ዙሪያ የተቃኙት ጉልህ ስህተቶች Brown (1994)፣ James (2001)፣ Darus & Subramaniam (2009) ካቀረቧቸው ገለጻዎች ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ምሁራኑ እንዳሉት፣ በሁለተኛ ቋንቋ መጻፍ አብዛኛውን ጊዜ በሁሉም የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች አዳጋችነት ያለበት ሲሆን፣ በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ሂደት የተማሪዎች የቋንቋ እውቀት ዳራ ዝቅተኛነት፣ የመጻፍ ተጋልጦ ማነስ፣ የስህተት ፍርሃት፣ ከማስተማሪያ ዘዴና ከማስተማሪያ መሳሪያ በተወረሱ ጉድለቶች እንዲሁም Presada & Badea (2014)፣ Heydari & Bagheri (2012)፣ በተማሪዎቹ የመጻፍ ተነሳሽነትና አመለካከት ጋር በተያያዙ ችግሮች የተነሳ ለበርካታ ተማሪዎች

አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል ሲሉ የገለጹትን ሃሳብ የሚያጠናክር ውጤት በዚህ ጥናት ተመልክቷል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተቶች ዋንኛ ምክንያቶቹ ምንድናቸው?›› የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ በጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ላይ የተመረከዘ ትንተና በመረጃ ትንተናው ክፍል ቀርቧል፡፡ የትንተናው ውጤት እንዳመለከተው የተጠኚዎቹ አንቀጽ የመጻፍ ችግሮች የግንዛቤ ማነስ /ስነልቦናዊ ችግሮች/፣ ከማስተማሪያ ዘዴ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ እና ውስጠ-ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዳሉባቸው ጥናቱ ቃኝቷል፡፡ ተጠኚዎቹ ከአንቀጽ መጻፍ ስነልቦናዊ ችግሮች ጋር አያይዘው ስምምነታቸውን ያሳዩባቸው በቅደም ተከተል፡-

- የሰዋሰው አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስ፣
- በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ለመጻፍ ሃሳብ የማመንጨት ችግር፣
- ስለሚጻፍበት ርእሰጉዳይ የተሟላ ግንዛቤ አለመኖር፣
- የቋንቋ አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስ

ችግሮች መሆናቸውን በጥናቱ ተዳስሷል፡፡ እነዚህ ችግሮች አነሰም በዛ ከሁለተኛ ቋንቋ ተጠኚዎቹ አጠቃላይ ስነልቦናዊ ዝግጁነቶች የሚገናኙ ናቸው፡፡

መጻፍ በመደበኛ መንገድ የምንማረው፣ የራሱ ህግና ሥርዓት ያለው መግባቢያ ነው፡፡ የቋንቋውን የጽሕፈት ህግ (የፊደላት አጠቃቀም) በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል፡፡ የቋንቋው የጽሕፈት ህግ ብቻ ሳይሆን ሀሳባችንን በጽሑፍ እንዴት መግለጽ እንዳለብንና ከአንባቢያችን ጋር ያለምንም ችግር እንዴት መግባባት እንደምንችል ማወቅ ያስፈልጋል ሲሉ የመጻፍን ክሂል አስቸጋሪ የሚያደርገውን ምክንያት እነ Presada & Badea (2014)፣ Heydari & Bagheri (2012)፣ Kavaliauskiene (2009) ከገለጹት ጋር የሚገናዘቡ ችግሮች በሁለተኛ ቋንቋ ተጠኚዎቹ ተንጸባርቀዋል፡፡

ኢ-አፍፈት የቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ከሚዳረጉባቸው ምክንያቶች አንዱ ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጁት ማስተማሪያ መሳሪያዎችና የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እንደሆኑ በክለሳ ድርሳን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በአጠቃላይ በተጠኚዎቹ የተጠቆሙ ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተገናኙ ችግሮችን ተጠኚዎቹ የጠቆሙት በአንጻራዊ ተቀራራቢ አማካይ ውጤቶች መሆኑን የመረጃ ትንተናው ያመለክታል፡፡ ይህም የሚያሳየው ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተያያዙት ችግሮች በኦሮምኛ ቋንቋ

አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ በተመሳሳይ የክብደት ደረጃ የሚያጋጥሟቸው የሁሉም ተጠኚዎች ችግሮች መሆናቸውን መገመት ያስችላል፡፡ ተጠኚዎቹ ያመለከቷቸው ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተዛመዱ ዋና ዋና ችግሮች በተቀራራቢ የምላሽ አማካይ ውጤቶቻቸው መሰረት በቅደም ተከተል፡-

- ዘጠነኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት በቂ የመጻፍ ልምምድ እድል አለማግኘት፣
- ለመጻፍ ክሂል መዳበር የሚጠቅሙ የተለያዩ ጽሁፎች ጋር በየጊዜው አለመተዋወቅ፣
- የአንቀጽ አጻጻፍ መርሆዎች ምን እንደሆኑ ጠንቅቆ አለማወቅ፣
- በጽሁፍ የሚቀርቡ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርአቶችን አለመገንዘብ፣
- የጽሁፍ ቋንቋ አጠቃቀም ደንብን አለመረዳት፣
- የጽሁፍ ስህተት ፍርሃት እንደሆኑ ተጠቁመዋል፡፡

## 4.3. የጥናቱ ግኝት

በርካታ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋቸው ውስጥ ያሉ የቃላት፣ የሰዋሰው ህግጋትን ጠንቅቀው ባለመረዳትና እነዚህን ህግጋትና ደንቦች በጽሁፍ ለመጠቀም ሰፊ ተጋልጦና ቀጣይነት ያለው የልምምድ እድል ማግኘት ባለመቻላቸው የሚከሰት ችግር መሆኑን እነ Khansir (2012)፣ Sarfraz (2011) የገለጹትን ያመለከተ ነው፡፡ ከፍ ሲል የተጠቆሙት ምሁራን አክለው እንደገለጹት አብዛኛውን ጊዜ በርከት ያሉ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላትን፣ ሃረጋትንና አረፍተ ነገሮችን ትርጉምና አገባብ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመፈለግ ይጠመዳሉ፡፡ በውጤቱም የሚያቀርቧቸው ጽሁፎች በቃላት፣ በሰዋሰው፣ አገባብና የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች የተመሉ ይሆናሉ፡፡ የቋንቋ መምህራን ትልቁ ችግርም ከመጻፍ ክሂል ጋር ለሚታገሉ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የሚረዱ ትርጉም ያላቸው የማስተማሪያ ስልቶችንና ግብአቶችን በመጠቀም ለተሻለ የጽህፈት ክንዋኔ ማነሳሳት፣ ብሎም የተማሪዎቻቸውን ብቃት በማሳደግ ረገድ የተለመዱ የጽህፈት ስህተቶችን እንዳይፈጽሙ ማድረግ አለመቻል ነው፡፡

በአጠቃላይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ተላውጦ ተጠኚዎቹ ለቀረቡላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት ከተተነተኑት የአንቀጽ መጻፍ ችግሮች ሁሉ የአማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃው ከፍ ያለ መሆኑን የመረጃ ትንተናው አመላክቷል፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ

ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋንኛ ምክንያቶቹ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ የሚነሱ መሆናቸውን በጉልህ ያሳያል፡፡

የተጠኚዎቹ ጉልህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተላውጦ ተጽእኖ በቅደም ተከተል፡-

- የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ እየገባ የሚያስቸግራቸው መሆኑ፣
- አንቀጽ ሲጽፉ የኦሮምኛ ቋንቋ የአረፍተነገር ስርአት (ስልት)ን መከተል፣
- በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፋቸው ውስጥ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን በአግባቡ አለመጠቀም፣
- በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ ተነባቢ ድምጾች በትክክል ለማስቀመጥ መቸገር፣ እና
- በጽሁፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን አለመለየት

መሆናቸው በጉልህ የስምምነት ደረጃ የተጠኚዎቹ ችግሮች መሆናቸውን ለማጤን ተችሏል፡፡ ከዚህም ጋር ተጠኚዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት /የውስጠ-ቋንቋ ተጽእኖ/ ተላውጦ ያሉባቸው ችግሮች ጉልህነት ቀደም ሲል በአንቀጽ መጻፍ ፈተና ከተመዘገቡት ስህተቶች ጋር የሚገናዘብ ነው፡፡ በፊደላት አጻጻፍ ላይ ያሉባቸው ችግሮች በአንቀጽ ጽሁፋቸው ውስጥ በቃላት ስህተትነት በተገለጸው ትንተና ውስጥም ጉልህ ሆነው መገኘታቸውን ለማጤን ተችሏል፡፡ ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ ተነባቢ ድምጾች በትክክል ማስቀመጥ መቸገራቸውን የጠቆሙበት ልኬት ቀደም ሲል የአንቀጽ ጽሁፍ ትንተና በተካሄደበት የትንተና ክፍል በፊደላት ስህተት ትንተና ወቅት ከታዩባቸው ስህተቶች ጉልህነት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ በሌላም በኩል ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለመለየት መቸገራቸውን ተጠኚዎቹ ያመላከቱበት የአማካይ ውጤት ልኬት ቀደም ሲል በተማሪዎቹ አንቀጾች በሰዋስው ስህተቶች ትንተና የቁጥርና ጾታ ንኡስ ዘርፍ ከቀረበው ትንተና ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የጥናቱ ማጠቃለ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች ጥቆማ

### 5.1.የጥናቱ ማጠቃለያ

በምእራፍ አራት የቀረበውን የመረጃ ትንተና እና የውጤት ትርጎማ መሰረት በማድረግ ጥናቱ ከሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ደርሷል፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት  ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ በርካታ ስህተቶችን የሚፈጽሙ መሆናቸውን የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ተጠኚዎቹ በሁለቱ ዙሮች ከፈጸሟቸው 4558 ስህተቶች መካከል በመጀመሪያው ዙር አንቀጽ 2446 (53.66%) በሁለተኛው ዙር አንቀጽ 2112 (46.34%) ስህተቶች ተመዝግበዋል፡፡ በሁለተኛው ዙር በጻፏቸው አንቀጾች የፈጸሙት ስህተት ብዛት በመጀመሪያው ዙር በጻፏቸው አንቀጾች ከፈጸሙት ስህተት ብዛት በጥቂቱ ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ በስህተት ድግግሞሽ ትንተናው እንደተቃኘው በሁለቱ ዙር አንቀጾች የታዩ ስህተቶች ንጽጽር ተቀራራቢነት /ትይዩነት ጎልቶ የሚታይባቸው በመሆናቸው ተጠኚዎቹ የተለያዩ ስህተቶችን ደግመው መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ በድግግሞሽ የሚፈጽሟቸው የጽሁፍ ስህተቶችን በተመለከተ የተጠኚዎቹ የአንቀጽ ስህተቶች በአምስት ዋና ዋና የስህተት ምድቦች የስህተት ድግግሞሽ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በስህተቶች ጉልህነት አንጻር በቅደም ተከተል ሰዋሰዋዊ አገባብ አለመጠበቅ፣ የስነድምጽ (ፊደላት) አጻጻፍ ስህተት፣ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ስህተት፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት እና የሀሳብ አንድነት ያለመጠበቅ ስህተት መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋንኛ ምክንያቶች የግንዛቤ ማነስ /ስነልቦናዊ ችግሮች/፣ ከማስተማሪያ ዘዴ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ እና ውስጠ-ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዳሉባቸው ጥናቱ ቃኝቷል፡፡ ተማሪዎቹ በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ አጣርተው ሊመጡ የሚገባቸው ስህተት

ትኩረት ሳይሰጠው እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ መዝለቃቸው ሌላው የስህተት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቹን በአንቀጽ ጽህፈት ተደጋጋሚ እድል በመስጠት በቂ የመጻፍ ተጋልጦ እንዲኖራቸው የሚደረግ ድጋፍ፣ ማበረታቻ እንዲሁም ስህተቶችን በየጊዜው በምጋቤ ምላሽ ስልቶች እያረሙ ስህተቶቻቸውን እንዲያሻሽሉ የሚሰጡት ትኩረት ውስን መሆኑ ለተማሪዎቹ የአንቀጽ መጻፍ ችግሮች አለመቃለል የበኩሉ ድርሻ ከፍ ያለ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡

## 5.2.መደምደሚያ

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዲምቱ ቁጥር አንድ እና ዲምቱ ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ በርካታ ስህተቶችን የሚፈጽሙ መሆናቸውን በጥናቱ ውጤት መሰረት ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- ተማሪዎቹ በድግግሞሽ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ጉልህነት አንጻር በቅደም ተከተል ሰዋሰዋዊ አገባብ አለመጠበቅ፣ የፊደላት አጻጻፍ ስህተት፣ የቃላትና የሀሳብ አመራረጥና አጠቃቀም ስህተት፣ የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተትና የሀሳብ አንድነት ያለመጠበቅ ስህተት መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

- ተማሪዎቹ አንቀጽ ሲጽፉ ለሚያጋጥሟቸው ስህተቶች ዋንኛ ምክንያቶች የግንዛቤ ማነስ /ስነልቦናዊ ችግሮች/፣ ከማስተማሪያ ዘዴ እና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዳሉባቸው ቃኝቷል፡፡ በመጨረሻም የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ስህተት ለመቀነስ የሚረዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመው ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ

**ሀ) የተማሪዎቹን የአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ስህተት ለመቀነስ የሚረዱ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የእርማትና የግብረ-መልስ ስልቶችን መቀየስና ሥራ ላይ ማዋል፡-** ተማሪዎቹ በዚህ የክፍል ደረጃ ላሉባቸው ውስብስብ የመጻፍ ክንዋኔ ችግሮች ከታች እድሜ ጀምሮ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል የተሰጠው ትኩረት ማነስ በዋንኛነት የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ ተማሪዎቹ የፊደላትን ትክክለኛ ቅርፆች ጠብቆ ካለመጻፍ አንስቶ በርከት ያሉ ስህተቶችን የሚፈጽሙበት ዋንኛ መንስኤ ተማሪዎቹ

ለሚማሩት ቋንቋ ያላቸው የተጋልጦ ሁኔታ እና በታላሚው ቋንቋ የሚያዘጋጁት የጽሁፍ ስራ ውጤት መጠን ማነስ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ እያሉ የፊደላት ቅርጽን፣ የቃላት አመሰራረትን እንዲሁም የሥርዓተነጥብ አጠቃቀምን ለይተው እንዲመጡ የሚያግዝ የማስተማሪያ ዘዴና የማስተማሪያ ቁሳቁስ በሚመለከተው አካል ቢዘጋጅ መልካም ነው፡፡

**ለ) የመምህራን የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎችን የሚያሳትፍ እና ቋንቋቸውን እንዲወዱ የሚያደርግ ቢሆን፡-** መጠናቸው ይነስም ይብዛ፣ የቋንቋውን ህግጋትና ደንቦች አጥርቶ ባለማወቅ የሚፈጸም ስህተት (ባልተሟላ መልኩ ወይም አዛብቶ መጠቀም)፣ የስዋስው ህግጋት ተከታታይነት ማጣት፣ ትምህርቱን ሂደታዊና ተግባቦታዊ ካለማድረግ ጋር የተያያዙ ስህተቶች ለተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል ስህተቶች ምክንያት ናቸው፡፡ እንዲህ ያሉት የስህተት ምክንያቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማስተማሪያ ስልት የተዋረሱ በመሆናቸው መምህራን የመጻፍ ክሂልን የሚያስተምሩበትን ስልት ማሻሻል፣ በተቻለ መጠን ቀጣይነት ባለው መልኩ ከቀላል ወደ ውስብስብ የሚጓዙ የመጻፍ ክሂል ግብአቶችን በማቅረብ ማስተማር ቢችሉ መልካም ይሆናል፡

# ዋቢዎች

ሁሴን አህመድ፡፡ (2009 ፡፡‹‹በጋምቤላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አማርኛ
ትምህርት ክፍል የሚማሩ አማርኛ አፍ-ፈትና ኢ-አፍ-ፈት የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽር፡፡›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)

ተገኘ አህመድ፡፡ (2000) ፡፡ ‹‹አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት
ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡
(ያልታተመ)

ደብሬ ተሰማ:: (1990 ዓ.ም )፡፡ “በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

መሰረት ጣፋ (2003)፡፡ “የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ተካቡ ታደሰ፡፡ (2011 ዓ.ም)፡፡ “የአማርኛ አፈ -ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋሰዋዊ ሰህተቶች ትንተና::”የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፣ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

አሰጋሽ ተሰማ፡፡(2013)፡፡ በሸክኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች፡፡ የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ መሚያ ጥናት፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

የአምላክሥራ ሕይወት (2008):: ‹‹የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ
የሚፈፅሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጭ ትንተና፤ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡
(ያልታተመ)

ባየ ይማም፡፡ (1987)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

ደመላሽ አለሙ እና ሳህሉ አክሊሉ፡፡ (2004)፡፡ አማርኛ የተማሪው መጽሐፍ፣ 9ኛ ክፍል፡፡ 1ኛ እትም፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የአል-ጉረር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ (1990)፡፡ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አዲስ አበባ የንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Abi-Samra, N. (2003). An analysis of errors in Arabic speakers' English writing. In Mourtaga, K. (Ed.), *Investigating writing problems among Palestinian students studying English as a foreign language.* Unpublished doctoral dissertation.

Alhaisoni, M. (2012). An Analysis of Article Errors among Saudi Female EFL Students: A Case Study, *Asian Social Science- Canadian Center of Science and Education*, 8(12), 55-66.

Abiy Y. (2013). "High School Students' Writing Skills and their English Language Proficiency as Predictors of their English Language Writing Performance". Bahir Dar University Faculty of Humanities, Department of English. J. Educ. & Sc. Vol. 9 No. 1 Sept. 2013.

Brown, H. (1994). *Principles of Language Learning and Teaching*. New Jersey: Prentice-Hall Inc.

Chen, M. and Huang, S. (2003). Individual Ability to Learn Independently. In *Journal of Educatiion*, vol.3, No2, pp.8-15.

Cheng, S. (2001). *Teaching and Resources in Teaching Grammar*, Oxford: Oxford University Press.

Colins, L. (2002). *Language Transfer in language Learning*. MA: Newbury House Publishers, Inc.

Crystal, M. (1999). Strengthening Student Writing Skills. Thesis (M.A). Saint Xavier University and Skylight Professional development Field-Based masters Program.

Darus, S. and Subramaniam, K. (2009). Error Analysis of the Written English Essays of Secondary School Students in Malaysia: A Case Study. *European Journal of Social Sciences*, 8(3), 483-495.

Davis, W. and Widowsen, R. (2004). Theory and Practice of Writing. London: Longman.

Dulay et al. (2002). *Language Two*. New York: Oxford University Press.

Ellis, R. (2003). *Language learners and their errors*. London: The Macmillan Press.

Ellis, R. and Barkhuizen, G. (2005). *Analysing Learner Language*. China: Oxford University Press.

Erdogan V. (2005). “Contribution of Error Analysis To Foreign Language Teaching”. Mersin: *Journal of the Faculty of Education*, 2 (26) 1-270.

Fang, X and Jiang X. (2007). Error Analysis and the EFL Classroom Teaching. *US-China Education Review*. 4(9), 10-14.

Harmer, R. (1991). *Understanding Second Language Acquisition*. 5th ed. Oxford: Oxford University Press.

Heydari, P. & Bagheri, M. S. (2012). Error analysis: Sources of L2 learners’ errors. *Theory and Practice in Language Studies, 2*(8), 1583-1589. https://doi.org/10.4303/tpls.2.8.1583-1589.

James, P. (2001). Learner language and the consideration of idiosyncracies by students of English as a second or foreign language in the context of Brunei Darulsalam. In A.M.

Kavaliauskiene, G. (2009). Role of the Mother Tongue in Learning English for Specific Purposes. *ESP World*, Issue 1(22), Vol.8. [Online ]Available:http://www.esp-world.info/Articles.

Khansir, M. (2012). *Error analysis and second language strategies*. In New frontiers in second language learning., Mass.: Newbury House.

Linnea-Ehri, S. (2000). The Role of Orthographic Images in Learning Printed Words," in *Orthography, Reading, and Dyslexia*, ed. James Kavanaugh and R. L. Venezky. Baltimore: University Park Press.

Littlewood, W. (2006). *Foreign and Second Language Learning*. Cambridge: Cambridge University Press.

Lott D. (2003). “Analyzing and Countering Interference Error”. *ELT*. 37 (13) 256-261

Norrish, J. (1993). *Language learners and their errors*. London: The Macmillan Press.

Nonkukhetkhong, K. (2013). *Grammatical error analysis of the first year English major students, Udon Thani Rajabhat University*. Paper presented at the Asian Conference on Language 2013, Osaka, Japan.

Presada, D., & Badea, M. (2014). The effectiveness of error analysis in translation classes. A pilot study. *Porta Linguarum, 22*, 49-59.

Raimes, A. (2003). *Techniques in Teaching Writing*. Oxford: Oxford University Press.

Richards, J. C. (1990). The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J. and Ranandya, P. (2002). The study of learner English. *Dissertation Abstracts International*, 47, 3415A.

Ridha, H. A. (2012). An investigation of syntactic and semantic errors in the written composition of Arab EFL learners (Doctoral dissertation, University of Illinois, *Dissertation Abstracts International*, 47, 3415A.

Sarfraz, S. (2011). Error Analysis of the Written English Essays of Pakistani Undergraduate Students: A Case Study, *Asian Transactions on Basic & Applied Sciences. 1(3), 29-5.*

Selinker L. (2000). *Interlingual in J.C. (Ed). Error Analysis*. Longman Group Ltd.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

### የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ

**የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች**

1. ትምህርት ቤቴ
2. የላም ጥቅም
3. ዛፍ መትከል
4. የእኔ ቤተሰብ
5. የመማር ጥቅም

**ርዕስ፡- -------------------------------------------------------**

የተጠኚው/ዋ/ ኮድ፡- -------------------------

አንቀጹ የተጻፈው፡- ሀ) በመጀመሪያ ዙር ----------- ለ) ሁለተኛ ዙር -----------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

# አባሪ ሁለት

## ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች!

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በነዲ ጊቤ ወረዳ ዲምቱ ቁጥር 1 እና ዲምቱ ቁጥር 2 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ጥናት ለማካሄድ ነው፡ በዚሁ መሰረት የጽሁፍ መጠይቁ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድ የመጻፍ ክሂልን ለመማር በሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ ያተኮሩ 20 ጥያቄዎች አሉት፡፡ ጥያቄዎቹ ‹‹ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ››፣ ‹‹እስማማለሁ››፣ ‹‹አቋም የለኝም››፣ ‹‹አልስማማም›› እና ‹‹ፈጽሞ አልስማማም›› ባለአምስት ነጥብ የመልስ አማራጮችን ይዘው የቀረቡ ናቸው፡፡

በእያንዳንዱ ጥያቄ አንጻር ለአንተ/ቺ/ ትክክል ነው ብለህ/ሽ/ የምታምንበትን/ የምታምኚበትን በመምረጥ በጥያቄዎቹ ትይዩ መልሱን በያዘው ሳጥን ውስጥ የ‹‹X›› ምልክት በመጻፍ መልስ/ሺ/፡፡ በመረጃ አሰጣጡ ተሳታፊ በመሆን ስላሳያችሁኝ ቀና ትብብር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

**ማስታወሻ፡-**

- ፈጽሞ አልስማማም……1 ነጥብ
- አልስማማም……………2 ነጥብ
- አቋም አልያዝኩም……..3 ነጥብ
- እስማማለሁ…………….4 ነጥብ

በጣም እስማማለሁ……..5 ነጥብ ይይዛሉ፡፡

| 4 | የመጻፍ ክሂልን ለመማር የሚያጋጥሙ ችግሮች | 1 | 2 | 3 | | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ሃሳብ የማመንጨት ችግር ያጋጥመኛል፡፡ | | | | | |
| 2 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ የቋንቋ አጠቃቀም ግንዛቤ ያንሰኛል፡፡ | | | | | |
| 3 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ስለሚጻፍበት ርእሰጉዳይ የተሟላ ግንዛቤ የሌለኝ መሆኑ | | | | | |
| 4 | ዝቅተኛ የሆነ የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ችግር ፈጥሮብኛል፡፡ | | | | | |
| 5 | የሰዋሰው አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስ በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ የሚያጋጥመኝ ችግር ነው፡፡ | | | | | |
| 6 | የጽሁፍ ቋንቋ አጠቃቀምና አወቃቀር ደንብን አለማወቅ አንቀጽ ከመጻፍ እንድቆጠብ ምክንያት | | | | | |
| 7 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ የመጻፍ ብልሃቶች ግንዛቤ እጥረት ያጋጥመኛል፡፡ | | | | | |
| 8 | በአማርኛ ቋንቋ ስጽፍ ትክክል ላልሆን እችላለሁ እያልኩ ሁልጊዜ እጠራጠራለሁ፡፡ | | | | | |
| 9 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ለመጻፍ ሳስብ ሀሳብ ይጠፋብኛል ወይም ሀሳቤ እየተዘበራረቀ | | | | | |
| 10 | የጽሁፍ ስህተት ፍርሃት በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ከመጻፍ እንድቆጠብ ምክንያት ነው፡፡ | | | | | |
| 11 | የመጻፍ ክሂልን በበቂ ሁኔታ አለመለማመድ የአንቀጽ አጻጻፍ ግንዛቤ እንዳላዳብር አድርጎኛል፡፡ | | | | | |
| 12 | የአንቀጽ አጻጻፍ መርሆዎች ምን እንደሆኑ አለማወቄ አንቀጽ ከመጻፍ አግዶኛል፡፡ | | | | | |
| 13 | በጽሁፍ የሚቀርቡ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርአቶችን አለማወቄ ስህተት እንድፈጽም | | | | | |
| 14 | ለመጻፍ ክሂል መዳበር የሚጠቅሙ የተለያዩ ጽሁፎች በየጊዜው አይቀርቡልኝም፡፡ | | | | | |
| 15 | ዘጠነኛ ክፍል ከመግባቴ በፊት በቂ የመጻፍ ልምምድ አለማድረጌ በአሁኑ ወቅት አንቀጽ ስጽፍ ያሳደረብኝ አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | አንቀጽ ስጽፍ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ጣልቃ እየገባ ያስቸግረኛል፡፡ | | | | | |
| 17 | በአማርኛ ቋንቋ አረፍተነገሮችን ስጽፍ የኦሮምኛ ቋንቋ የአረፍተነገር ስርአት (ስልት)ን መከተል ይቀናኛል፡፡ | | | | | |
| 18 | በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፌ ውስጥ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን በአግባቡ መጠቀም ያዳግተኛል፡፡ | | | | | |
| 19 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ስጽፍ ሁሉንም ተነባቢ ድምጾች በትክክለ ማስቀመጥ ያስቸግረኛል፡፡ | | | | | |
| 20 | በጽሁፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን | | | | | |

# አባሪ ሶስት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
ሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ቁጥር፡- ኢ/ቋ/ሥ/አማ/793/15

ቀን፡- 12/07/2015 ዓ.ም.

**ለሚመለከተው ሁሉ**

ተማሪ ቡልቱ አበየዚድ በጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ 2ኛ ዓመት የድህረ-ምረቃ ተማሪ ስትሆን፤ በአሁኑ ሰዓት የኮርስ ስራዋን አጠናቃ "የኦሮምኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና" በሚል ርዕስ የመመረቂያ ጥናታዊ ፅሑፏን በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ በመሆኑም መረጃ ለመሰብሰብ በምታደርገው ሂደት አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር ታደርጉላት ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
አማርኛ ቋንቋና ስነ-ዕሁፍ ት/ክፍል
Department of Amharic
Jimma University

ከሠላምታ ጋር

W/ra Bam.G/Jimmaa A/Nadhii Gibeetti
M/Barumsaa Diimtuu Sad.2ffaa Lakk.1
በጅማ ዞ ነጌ ጊቤ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ዲምቱ 2ኛ ደረጃ ቁጥር.1 ትምህርት ቤት

ቁጥር 164/01-15/35
ቀን 20/08/2015

ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

ጅማ

ጉዳዩ፡- ስለ ተማሪ ቡልቱ አበየዚድ መረጃ መስጠትን ይመለከታል፡፡

ከለይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ተማሪ ቡልቱ አበየዚድ በዲምቱ ቀጥር አንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመገኘት « በኦሮምኛ አፊ-ፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽቸው ስህቶች ትንተና » በሚል ርእስ ከተማሪዎች መረጃ የሰበሰበች መሆኗን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

Silashi Lameessaa
ስለሺ ለሜሳ
Durabu'aa M.Barumsichaa
ርዕሠ መምህር

Wira Barn.G/Jimmaa A/Nadhii Gibeetti
M/Barumsaa Diimtuu Sad .2ffaa Lakk.2
በ ጅማ ዞን ነጂ ጊቤ ወረዳ
ትምህርት ጽ/ቤት ዲምቱ ቁ.፪ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ቁጥር 130/04/35
ቀን 20/08/2015

ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

ጅማ

ጉዳዩ፡- ስለ ተማሪ ቡልቱ አበየዚድ መረጃ መስጠትን ይመለከታል፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ተማሪ ቡልቱ አበየዚድ በዲምቱ ቀጥር 2 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመገኘት « በኦሮምኛ አፊ-ፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽቸው ስህቶች ትንተና » በሚል ርእስ ከተማሪዎች መረጃ የሰበሰበች መሆኗን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

Tolasaa Dabalee Dabalii
ቶለሳ ደበሌ ደበሊ

Dura Bu'aa Mana Barumsichaa
የት/ቤቱ ርእሰ መምህር

ቁ.1

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ ፈተና

የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ

የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች

1. ትምህርት ቤቴ
2. የሳሙና ጥቅም
3. ዛፍ መትከል
4. የእኔ ቤተሰብ
5. የመማር ጥቅም

ርዕስ፡- የሳሙና ጥቅም

የተጠኚው/ዋ/ ኮድ፡- 4

አንቀጹ የተጻፈው፡- ሀ) በመጀመሪያ ዙር ---------- ለ) ሁለተኛ ዙር ✓

[illegible]

የቃላት ብዛት=59 የፊደል ግድፈት ስህተቶች

[illegible] =26

የተንዛዛ ስህተቶች =8

አጠቃላይ [illegible] =35 ስህተቶች

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ -ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ ፈተና

**የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ**

**የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች**

1. ትምህርት ቤቴ
2. የላም ጥቅም
3. ዛፍ መትከል
4. የእኔ ቤተሰብ
5. የመማር ጥቅም

ርዕስ፡- ዛፍ መትከል

የተጠኚው/ዋ/ ኮድ፡- 102

አንቀጹ የተጻፈው፡- ሀ) በመጀመሪያ ዙር ✓ ለ) ሁለተኛ ዙር ---------

ዛፍ መትከል [illegible] ነው።

[illegible]

የቃላት ብዛት =54

የአጻጻፍ ስህተት (የሆሄያት ግድፈት)=11

ቀ-2

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ ፈተና

የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ

የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች

1. ትምህርት ቤቴ
2. የሳም ጥቅም
3. ዛፍ መትከል
4. የእኔ ቤተሰብ
5. የመማር ጥቅም

ርዕስ፡- ትምህርት ቤቴ

የተጠኚው/ዋ/ ኮድ፡- 19

አንቀጹ የተጻፈው፡- ሀ) በመጀመሪያ ዙር ✓ ለ) ሁለተኛ ዙር

[illegible]

[illegible]

ቀ.ፈ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ ፈተና

**የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ**

**የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች**

1. ትምህርት ቤቴ
2. የላም ጥቅም
3. ዛፍ መትከል
4. የእኔ ቤተሰብ
5. የመማር ጥቅም

ርዕስ፡- የመማር ጥቅም

የተጠኚው/ዋ/ ኮድ፡- 22

አንቀጹ የተጻፈው፡- ሀ) በመጀመሪያ ዙር ---------- ለ) ሁለተኛ ዙር x

መማር ብዙ ጥቅሞች አሉት። የሰው ልጅ ያለ ትምህርት
ምንም ነገር መስራት አይችልም። የሰው ልጅ ቢተማረ ብዙ ስራ
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] ጥቅም [illegible]።

የቃላት ግድፈት = 4/
የሰዋሰው ስህተት (ሥርዓተ ነጥብ) = 2
የአጻጻፍ [illegible] ስህተት = 2

8 ስህተቶች

1

ቀ-2

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ -ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ ፈተና

የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ

**የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች**

1. ትምህርት ቤቴ
2. የላም ጥቅም
3. ዛፍ መትከል
4. የእኔ ቤተሰብ
5. የመማር ጥቅም

ርዕስ፡- የላም ጥቅም

የተጠኚው/ዋ/ ኮድ፡- 22

አንቀጽ የተጻፈው፡- ሀ) በመጀመሪያ ዙር X ለ) ሁለተኛ ዙር ----------

[illegible]

[illegible]

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ ፈተና

የአንቀጽ መጻፊያ ቅጽ

የአንቀጽ መጻፊያ ርዕሶች

1. ትምህርት ቤቱ
2. የላም ጥቅም
3. ዛፍ መትከል
4. የእኔ ቤተሰብ
5. የመማር ጥቅም

ርዕስ፡- የላም ጥቅም

የተጠኚው/ዋ/ ኮድ፡- 29

አንቀጹ የተጻፈው፡- ሀ) በመጀመሪያ ዙር ---------- ለ) ሁለተኛ ዙር ✓

[illegible]

1. [illegible]
2. [illegible]
3. [illegible]

[illegible] =86

[illegible] =2

[illegible] =2

[illegible] =5

[illegible]